# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 82ኛ ዓመት ቁጥር 043 ጥቅምት 13 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


# ኢትዮጵያውያን የውጭ ጣልቃ ገብነትን በሰልፍ አወገዙ



ፎቶ፡- ሔኖክ አበርሃ

## ያልተገባ ጣልቃ ገብነትን የሚያወግዙ እና ሠራዊቱን የሚደግፉ ሕዝባዊ ሰልፎች ተካሄዱ

ዘሳስም ግዛው

አዲስ አበባ፡- "ለኢትዮጵያ እቆማለሁ፤ ድምጼን አሰማለሁ" በሚል መሪ ሃሳብ የአሸባሪውን ትሕነግ ድርጊት የሚያወግዝ፣ የአንዳንድ ምዕራባውያንን ያልተገባ ጣልቃ ገብነት የሚያወግዝ እና ሠራዊቱን የሚደግፉ ሕዝባዊ ሰልፎች ትናንት በተለያዩ ክልሎች ተካሄዱ።

በተካሄዱት ሰልፎች ኢትዮጵያውያን ለአገር ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት መጠበቅ መስዋዕትነት እየከፈለ ለሚገኘው የአገር መከላከያ ሠራዊት ያላቸውን አክብሮት፣ ድጋፍና አጋርነት በመግለጽ፤ ለሠራዊቱ ምስጋና አቅርበዋል።

የውጭ ሃይሎች በኢትዮጵያ ላይ ጫና ለመፍጠር የሚያደርጉትን ጫና እንዲያቆሙም ሰልፈኞቹ አሳስበዋል፡፡ አሸባሪው ትሕነግ በንጹሃን፣ በሴቶችና አረጋውያን ላይ እያደረገ ያለውን የሽብር ድርጊትንም አውግዘዋል፡፡

በሶማሌ ክልል የጅግጅጋ ከተማ ሰልፈኞች ባነገቡት እና በድምፃቸው ባሰሙት መልዕክት ኢትዮጵያ ከብዙ ሺህ ዓመታት ጀምሮ ፀንታ የቆመች፣ ታላቅ እና ሉዓላዊት አገር መሆኗን አንጸባርቀዋል።

ያልተገባ ጣልቃ ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል







የኢትዮጵያ የግንባታ ግብዓቶች አቅራቢ ኃ/የተ/የግል ኩባንያ
ETHIOPIAN CONSTRUCTION COMMODITIES SUPPLY PLC.
የአርማታ ብረት እና ሌሎች ብረታብረቶች አከፋፋይ



Mob. 0911 225057/ 0989 343434
አድራሻ፡ ከሜክሲኮ አደባባይ ወደ መርካቶ በሚወስደው መንገድ ከዲ-አፍሪክ ሆቴል ፊት ለፊት




ፎቶ፡- በእዮብ ተፈራ

## ‹‹በአሸባሪው ሕወሓት ፕሮፓጋንዳ የተወሰዳችሁ ተሳስታችኋልና ተመለሱ››

ጃንጥራር አባይ
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ

ውብሸት ሰንደቁ

አዲስ አበባ፡- በተሳሳተው የሽብር ቡድን ሕወሓት ፕሮፓጋንዳ የተወሰዳችሁ ተሳስታችኋልና ተመለሱ ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ አቶ ጃንጥራር ዓባይ አሳሰቡ፡፡

"ለኢትዮጵያ እቆማለሁ ድምጼን አሰማለሁ" በሚል መሪ ሃሳብ የአሸባሪውን ሕወሓት ቡድን የሚያወግዝ እና የውጭ ኃይሎች በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ

‹‹በአሸባሪው ሕወሓት ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል


አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY
ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር




0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565


"የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የተጀመሩ ስራዎችን በማጠናከር ትውልድ ለመገንባት ይሰራል"

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ



ገጽ 2

# “የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የተጀመሩ ስራዎችን በማጠናከር ትውልድ ለመገንባት ይሰራል”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ የተጀመሩ ስራዎችን በማጠናከር ያሉንን ጸጋዎች ለልማት የሚያውል ትውልድ ለመገንባት እየተሰራ ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ገለጹ። የቀዳማዊት እመቤት ጽህፈት ቤት በኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን አኮ ከተማ ያስገነባውን የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድና ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው መርቀው ከፍተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቀዳማዊ እመቤት ጽህፈት ቤት በኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን አኮ ከተማ የተገነባው ኢፋ አኮ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትናንት መርቀው ሲከፍቱ እንደገለጹት፤ ትምህርት የአርሶ አደሩን ችግር በዘላቂነት የምንፈታበት ቁልፍ መሳሪያ ነው። በመሆኑም በቀጣይ የትምህርት ጥራትን ለማስጠበቅ የተጀመሩ ስራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ።

ኢትዮጵያ የበርካታ ጸጋዎች ባለቤት መሆኗን ጠቅሰው፣ ያሉንን ፀጋዎች በመጠቀም ኢትዮጵያን በሁሉም መስክ ማልማት ይገባል ብለዋል። የቀዳማዊ እመቤት ጽህፈት ቤት የትምህርት ተደራሽነትን ለማስፋት የጀመረውን ስራ አጠናክሮ እንዲቀጥልም ጥሪ አቅርበዋል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን በበኩላቸው የትምህርት ጥራትና ተደራሽነት ለማስፋት የተጀመሩ ስራዎች ልዩ ትኩረት እንደሚሰጣቸው ተናግረዋል። ድህነትን በዘላቂነት ለመቅረፍ ትምህርት ቁልፍ መሆኑን ጠቅሰው እየተከናወኑ ያሉ ስራዎች የሚፈለገውን አገራዊ ልማት ለማረጋገጥ መሰረት የሚጥሉ መሆናቸውን ገልጸዋል።

ትምህርት ቤቱ የተገነባው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከመደመር መጽሃፍ ሽያጭ ያገኙትን ገቢ ለትምህርት ቤት ማሰሪያ እንዲሆን ለቀዳማዊት እመቤት ጽህፈት ቤት ባደረጉት ድጋፍ አማካኝነት ነው።



ለምረቃ የበቃው ትምህርት ቤት 18 መማሪያ ክፍሎችን ጨምሮ የላይበራሪና የላቦራቶሪ ማዕከላትን የያዘ ነው። የትምህርት ቤቱን ግንባታ ለማጠናቀቅ ስምንት ወራትን እንደወሰደም ተገልጿል። ይህ ትምህርት ቤት በቀዳማዊ እመቤት ጽህፈት ቤት አማካኝነት ተገንብተው ከተመረቁት መካከል 25ኛ መሆኑ ተጠቅሷል።

ጽህፈት ቤቱ በሁለተኛ ዙር ስድስት ትምህርት ቤቶችን ያስገነባ ሲሆን፣ ተጨማሪ አንድ ትምህርት ቤት በግንባታ ሂደት ላይ ይገኛል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ከመደመር መጽሃፍ ያገኙትን ከ 110 ሚሊዮን ብር በላይ ለገጠር ትምህርት ቤቶች ማሰሪያ ይሆን ዘንድ ለቀዳማዊ እመቤት ጽህፈት ቤት ድጋፍ ማድረጋቸው ይታወሳል።

በምረቃ መርሃ ግብሩ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን፣ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚዳንት ሽመልስ አብዲሳና የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ እንዲሁም ሌሎች ከፍተኛ የመንግሥት የስራ ሃላፊዎች መገኘታቸውን የዘገበው ኢዜአ ነው።

# ስድስተኛው የአፍሪካ ሚኒስትሮች የሲቪል ምዝገባ ጉባኤ ነገ በአዲስ አበባ ይጀመራል

አዲሱ ገረመው

አዲስ አበባ፡- ለሲቪል ምዝገባ ኃላፊነት ያለው ስድስተኛው የአፍሪካ ሚኒስትሮችና የባለሙያዎች ቡድን ጉባዔ ከነገ ከጥቅምት 14 እስከ 18 ቀን በአዲስ አበባ እንደሚካሄድ ተገልጿል።

የጉባዔውን መካሄድ አስመልክተው መግለጫ የሰጡት የኢሚግሬሽን ዜግነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ብሩህተስፋ ሙሉጌታ እንዳሉት፤ ጉባዔው የአፍሪካ መሪዎች ጉባዔ ከአስር ዓመታት በፊት ባስቀመጠው መመሪያ መሠረት የሚካሄድ ሲሆን፤ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ከመጠበቅ፣ የልማት ግቦችን ከማሳካትና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ሂደት ውስጥ ገንቢ ሃሳቦች የሚስተናገዱበት ነው።

ዋና ዳይሬክተሩ እንዳሉት፤ ጉባዔው ሁሉም ሰው የሚታወቅባት የኢትዮጵያን ገጽታ ለመገንባት ብሎም የነገዋን አፍሪካ ለመፍጠር በጋራ ለመቆም የሚያስችል አጋጣሚ ነው። በጉባዔው ሁሉም የአፍሪካ አገራት በዋናነት የወሳኝ ኩነትን፣ ስታትስቲክስንና ጤናን የሚመሩ ተቋማት ኃላፊዎች እንዲሁም ዓለም አቀፍ፣ አህጉር አቀፍና አገር ቤት ያሉ አጋር አካላትን ጨምሮ ከስድስት መቶ በላይ ሰዎች ተሳታፊ ይሆናል።

የሲቪል ምዝገባ ቫይታል ስታትስቲክስ በአፍሪካ ደረጃ ጉባዔውን ኢትዮጵያ እንድታስተናግድ ጥያቄ አቅርቦ በአጭር ጊዜ ውስጥ ፍቃደኝነቱ ተገልጾ እንዲካሄድ መወሰኑን የጠቆሙት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ኢትዮጵያ ይህንን ጉባዔ ስታዘጋጅ ለሁለተኛ ጊዜ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

ወሳኝ ኩነትና ቫይታል ስታትስቲክስ ለሕግ፣ ለአስተዳደርና ለስታቲስቲካል ጉዳዮች ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑን የጠቀሱት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ከዚህ አንጻር ዜጎችም ሆኑ ማንኛውም በአገሪቱ ግዛት ውስጥ የሚኖር የሰው ዘር በሙሉ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቹን ለማስጠበቅ ጉባዔው መሠረት የሚጥል መሆኑን ገልጸዋል።

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ የጉባዔው መካሄድ በተለይም መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ከዚህ ሥርዓት የሚገኙ መረጃዎች ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። ለስትራቴጂካዊ እቅዶችና ፖሊሲዎች በግብዓትነት የሚጠቅሙ የሥነ ሕዝብ መረጃዎችን ከማደራጀት አንጻርም የጎላ ሚና አለው።

ጉባዔው እንደ አፍሪካ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ከመጠበቅ፣ የልማት ግቦችን ከማሳካትና መልካም አስተዳደርን በማስፈን ሂደት ውስጥ ገንቢ ሃሳቦች የሚስተናገዱበት እንደሆነ ጠቁመዋል። ሁሉም የሚታወቅባትን አፍሪካን ከመፍጠር አንጻር የሲቪል ምዝገባ ያለውና ማንም የተረሳ ሰው እንዳይኖር የማድረግ መሠረትን የሚጥል እንደሆነ አመላክተዋል።

የአፍሪካ የስታስቲክስ ማዕከል ዳይሬክተር ኦሊቨር ቺንጋንያ በበኩላቸው፤ በአፍሪካ ውስጥና ከውጭ ልምድ ያላቸው ተወያዮች የሚሳተፉበት ይህ ጉባዔ በቀጣዮቹ ዓመታት በአፍሪካ የሲቪል ምዝገባና የወሳኝ ስታቲስቲክስ ሥርዓት እድገትን የሚያፋጥኑ የትኩረት ስትራቴጂካዊ ተግባራትን ለመለየት ያግዛል ብለዋል።

እንደ አፍሪካ ያሉ ተግዳሮቶችንና መልካም ተሞክሮዎችን መጋራት የጉባዔው አንዱ አካል እንደሆነ ገልጸው፤ አፍሪካን ለማገዝ የሚመጡ አጋር አካላትንም ለበጎ ዓላማ እንዲሰለፉ ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል። የ2030 ዘላቂ የልማት ግብ እንዲሁም “የምንፈልጋት አፍሪካ” ለሚለው 2063 አጀንዳ ጋር ትስስር ያላቸው ሃሳቦች ተንጸባርቀው ቀጣይ አቅጣጫዎች የሚቀመጡበት ጉባዔ እንደሚሆንም አስታውቀዋል።

# የውጭ ሃይሉች በኢትዮጵያ ተሳሳኪ መንግሥት ለማቋቋም የሚያደርጉትን ጫና አንቀበልም

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- የውጭ ሃይሎች የኢትዮጵያን መንግሥት ፍላጎታቸውን እንዲፈፅም አሊያም እሱን አስወግደው ተላላኪ መንግሥት ለማቋቋምት የሚያደርጉትን ጫና አንቀበልም ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶች ገለጹ።

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ወጣት ካባ ጋዲሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጸው፤ የውጭ ሃይሎች በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርጉትን ተደጋጋሚ ጫና አሁን በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት የእነሱን ፍላጎት ስላልፈጸመላቸው የመጣ ነው።

ዓላማቸውም ጫና በማሳደር መንግሥትን ወደ ሚፈልጉት መስመር ማምጣት አልያም ይህ ካልተሳካም እሱን አስወግዶ በሌላ ታዛዥና ተላላኪ ኃይል ለመተካት ነው ብሏል።


የውጭ ሃይሎች ያልተገደበ ጫና የሚያሳድሩት የራሳቸውን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር መሆኑን ያመለከተው ወጣት ካባ ፤ ኢትዮጵያም ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስጠበቅ ከግንብና ከድንጋይ ጋር በቀጥታ መጋጨት ሳይሆን ብልሃት በታከለበት የዲፕሎማሲ ሥራዎች ማከናወን እንዳለባት ተናግሯል።

ወጣት ተሾመ ዳቢሳ በበኩሉ፤ እያንዳንዱ ሀገር የራሱን ብሔራዊ ጥቅም ለማስከበር ተኝቶ አያድርም። የወጭ ሃይሎች ደግሞ ፍላጎታቸውን ለማሳካት እንደኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት ላይ የተለያዩ ጫናዎችን ያሳድራሉ።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ጨምሮ ትላልቅ ዓለም አቀፍ ተቋማት ለአንዳንድ ምዕራባውያን ሀገራት ጉዳይ አስፈጻሚ ሆነዋል ሲሉም ተናግረዋል።




ወጣት ካባ ጋዲሳ




ወጣት ተሾመ ዳቢሳ



ወጣት ቤዛዊት ተክሉ

ስለሆነም ኢትዮጵያን ማንም እንደፈለገ ጠምዝዞ የራሱን ብሔራዊ ፍላጎት ፈፃሚ ሊያደርጋት አይችልም። እንደ አገር ብሔራዊ ጥቅማችንን አስጠብቀን ለማስቀጠልና ተንበርካኪ መንግሥት ላለመሆን የኢትዮጵያን የመደራደርና የተደማጭነት አቅም ማሳደግ ይገባል ብሏል። ለዚህም የዲፕሎማሲ፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና ጠንካራ ሠራዊት ግንባታ ሥራዎችን ማጎልበት እንደሚያስፈልግ ጠቁሟል።

ኢትዮጵያ ወደተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሚሄዱ ጉዳዮችን በአፍሪካ ሕብረት እንዲቋጩ ተፅዕኖ ለማሳደር አሁንም በርካታ ሥራዎች እንደሚጠብቃት የገለጸችው ደግሞ ወጣት ቤዛዊት ተክሉ ናት።

እንደ ወጣት ቤዛዊት ገለጻ፤ የአፍሪካ ሀገራት እንደ ኢትዮጵያ የውጭ ሃይሎችን ጫና ሲመጣባቸው ለመቀልበስ የራሳቸውን ጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራና አፍሪካዊ አንድነትን ማጠናከር አለባቸው።

የኢትዮጵያ መንግሥትም የአፍሪካ ሕብረትና ሌሎች ክፍለ አህጉራዊ ተቋማትን በመጠቀም መብቷንና ጥቅሟን ለማስጠበቅ ይብልጥ መስራት እንዳለባት አሳስባለች።

በእነዚህ ተቋማት ላይ ተጨባጭ የዲፕሎማሲ ሥራ በማከናወን የታላቁ የኢትዮጵያ የህዳሴ ግድብ ድርድርን ጨምሮ ሌሎች ጉዳዮች ጭምር ቢቻል በኢጋድ ባይቻል በአፍሪካ ሕብረት መፍትሄ እንዲያገኙ በማስረዳት፤ በመከራከርና በማስገንዘብ ጥቅማችንን ማስጠበቅ እንችላለን ብላለች።

ሀገራት ሽኩቻ ከሚያደርጉባቸው ቦታዎች መካከል አንዱ የምስራቅ አፍሪካ ቀጠናና የቀይ ባህር መስመር መሆኑን ገልጻ፤ ይህን ቦታ ለመቆጣጠር የሚችሉት በምስራቅ አፍሪካ አገሮች በተለይም በኢትዮጵያ ላይ ተፅዕኖ ማሳደር ሲችሉ እንደሆነ ተናግራለች።

የውጭ ሃይሎች ኢትዮጵያ ላይ ተደጋጋሚ ጫና የሚያሳድሩት አገሪቱ በምስራቅ አፍሪካ ብሎም በአፍሪካ አህጉር ባላት ተፅዕኖ ፈጣሪነትና የሕዝብ ቁጥሯ ከፍተኛ በመሆኑ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ያለው መንግሥት የአገሩን ጥቅም ለማስከበር ያለውን ቁርጠኝነት ለውጭ ሃይሎች በግልጽ በማንጸባረቁ ምክንያት ጫናቸውን አበርትተዋል ብላለች።

# ርዕሰ አንቀፅ

## “እጃችሁን ከኢትዮጵያ ላይ አንሱ” የሚለው የሕዝብ ድምጽ ሲደመጥም ሲከበርም ይገባል!

ኢትዮጵያውያን የጋራ ቤታቸው የሆነችውን ኢትዮጵያን ለመጠበቅ፣ ስለ አገራቸው ክፉ ሃሳብ ይዞ፣ እኩይ ምግባሩን ገልጦ ለሚመጣ ማንኛውም የውስጥም ሆነ የውጪ ኃይል እንደ አመጣጡ ምላሽ ለመስጠት፣ የአገራቸውን ሉዓላዊነትና ክብር ለተፈታተነ የትኛውም አካል የሚሸነፍ ስብዕና ያላቸው አይደሉም፡፡ ይሄንኑም ከፍ ያለ ልዕልናን የተጎናጸፈ ስብዕናቸውን ማየት ለፈለገ የኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያውያንን ጉዞ የዘመን ጅረት ተከትሎ ወደፊትና ወደኋላ እያለ መመልከቱ በቂው ነው፡፡ ካልሆነው የቀደሙቱን የቅኝ ገዢነት አባዜ ተጠናውቷቸው ወደ ኢትዮጵያ አማትረው የነበሩ አያት ቅድመ አያቶቹን ድርሳናት ማገላበጡ ከበቂ በላይ ስለ እነዚህ ኢትዮጵያውያን እንዲገነዘብ ያደርገዋል፡፡

ይህ የኢትዮጵያውያን ከፍ ያለ ሰብዕናና ልእልና ለተደጋጋሚ ሽንፈትና ውርደት የዳረጋቸው ኢትዮጵያ ጠል የሆኑ የውስጥና የውጪ ኃይሎች፣ በተለይም አንዳንድ የምዕራቡ ዓለም አገራት፣ ኢትዮጵያን አዳክሞ፣ ኢትዮጵያውያንንም ከፋፍሎ አቅማቸውን በመስለብ ለማንበርከክ ከትናንት እስከዛሬ እያካሄዱት ያለው እኩይ ሴራ አልተቋረጠም፡፡ ለዚህ እኩይ ተግባራቸው ደግሞ በቀጥታ ያደረጉት የወራሪነት ፍላጎታቸው ተደጋጋሚ ሽንፈትን ካከናነባቸው በኋላ፣ የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ ይሉትን ብሂል ለመተግበር እንቅልፍ አጥተው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡

ለዚህ ውጥናቸው መሳካትም እንደ አሸባሪው ትህነግና መሰል ኢትዮጵያን ጠል ኃይሎች ከውስጥ በመመልመል እና፣ በስንቅም፣ በትጥቅም፣ በፋይናንስም፣ በሚዲያና ኮሙኒኬሽን ፕሮፖጋንዳም፣ በዲፕሎማሲና ሌሎችም መልኩ የሚገለጽ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ በማድረግ ኢትዮጵያውያንን ረፍት የለሽ ጦርነት ውስጥ ለመክተት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ቀውስን መፍጠር ዋና ግባቸው አድርገው እየተጓዙ ይገኛሉ፡፡

በአሸባሪው ትህነግ ፊት አውራሪነት የሚዘወረውና በእነዚህ አንዳንድ አገራት ሙሉ ድጋፍ የሚደረግለት የኢትዮጵያ የሰሜኑ ጦርነትም የዚህ አንዱና ዋናው ማሳያ ሲሆን፣ በጦርነቱ የሽብር ቡድኑ ቢችል አሸንፎ እንዲወጣ፣ ባይችል ደግሞ የተራዘመ ጦርነት ውስጥ ኢትዮጵያን እንዲያቆይ ታስቦ በእጅ አዙር እየተካሄደ ያለ ነው ሲል ሕዝቡ በትናንቱ ሰልፍ ላይ በሚገባ ገልጿል፡፡

ይሄን ሲያደርጉም በጦር መሳሪያና ቴክኖሎጂ ብቻ ሳይሆን፣ በእነዚህ አገራት ሚዲያዎች፣ አፈ ቀላጤዎች፣ ተቋማትና ሌሎችም ለቡድኑ እንዲሰሩ በየአውዱ የተሰገሰጉ ቅጥረኛ ግለሰቦች አማካኝነት የኢትዮጵያንና የመከላከያ ሰራዊቷን ስም ማጠልሸት፣ የሃሰት ክስ መመስረትና ዓለማቀፍ ጫና እንዲሁም ማዕቀብ እንዲጣልባት፣ ከተቻለም ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት እንዲፈቀድላቸውና የሽብር ቡድኑን በቀጥታ ማገዝ የሚችሉበትን እድል ለማመቻቸት እንቅልፍ አጥተው እየጣሩ ይገኛሉ፡፡

ይሄን የተረዱት ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ መንግስት ታዲያ፣ በአንድ በኩል የሽብር ቡድኑን ቅስም በመስበር ዳግም የአገር ሸክም እንዳይሆን የመከላከል ተግባራቸውን በብቃት እየፈጸሙ ይገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል ስለ ሰላም የተዘረጋውን እጅ ሳያጥፉ ለአገርና ሕዝብ ሲባል ለሰላም ውይይት ተግተው እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በሽብር ቡድኑ አፈና ውስጥ የነበረው ወንድም የትግራይ ክልል ሕዝብ ከደረሰበት ኢኮኖሚያዊ፣ ሰብዓዊና ስነልቡናዊ ስብራት እንዲጠገን የሚያስችለውን ስራ በማከናወን ከወገን የሚጠበቀውን ሁሉ እያደረጉለት ይገኛሉ፡፡

ይሄ የሰብዓዊነት ከፍታን የሚያሳየው የኢትዮጵያውያን እና መንግስታቸው መልካም ተግባር አልዋጥ ያላቸው አንዳንድ አገራት፣ ተቋማትና ሚዲያዎቻቸው ግን፣ ከእውነቱ በራቀና ለራሳቸው ሴራ በሚመች መልኩ የሃሰት ድርሰትና ተረካቸውን ከማስተጋባት አልተቆጠቡም፡፡ ኢትዮጵያ፣ ኢትዮጵያውያንና መከላከያ ሰራዊታቸው እንዲሁም መንግስታቸው ላይ ያነጣጠረ ስም ማጥፋትና ውንጀላቸውን በተናበበ መልኩ እየተቀባበሉት ይገኛሉ፡፡ ይሄ አካሄድ ደግሞ ዓላማና ግቡ ምን እንደሆነ ለሁሉም ግልጽ ነው፡፡ ከውጪ ሆኑ በኢትዮጵያ ላይ ጫና መፍጠር እና እጅ መጫን ነው፡፡ ለዚህም ነው እንደ ትናንቱ ሁሉ ዛሬም ኢትዮጵያውያን “እጃችሁን ከኢትዮጵያ ላይ አንሱ” ሲሉ በውስጥም በውጪም ሆነው ድምጻቸውን ማሰማት ስለ መቀጠላቸው ትናንት በአዲስ አበባ እና በብዙ የክልል ከተሞች የተሰሙት የኢትዮጵያውያን ድምጾችም ይሄንኑ የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡

"ለኢትዮጵያ እቆማለሁ ድምጼን አሰማለሁ" በሚል መሪ ሃሳብ በአንድ ተሳስረው በጋራ አደባባይ ወጥተው የእነዚህን ምዕራባውያንን ያልተገባ ጣልቃ ገብነት ሲቃወሙ ያረፈዱበት ይህ የተቃውሞ ሰልፍ፣ የሙያ ማህበራት፣ የሲቪክ ማህበራት እና የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ ያዘጋጁት ነበር፡፡ የሰልፉ ዋና ዓላማም ኢትዮጵያ ያለችበትን ወቅታዊ ሁኔታ ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለማሳወቅና ለአገሪቱ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት መከበር በሁሉም መስክ ከመንግስት ጎን መቆማቸውን ለማረጋገጥ ሲሆን፣ በዚህም በተለይ አሸባሪው ትህነግ እና ሰላም ፈጽሞ የማይዋደዱ ይልቁንም የተጣሉ መሆናቸውን ከማሳወቅ የዘለለ፣ ለሽብር ቡድኑ ህልውና ሲሉ በኢትዮጵያ ላይ ፍላጎታቸውን ለመጫን የሚሰሩ ምዕራባውያን አገራትና ተቋሞቻቸው ከዚህ ድርጊታቸው ሊታቀቡ እንደሚገባ ያሳሰቡበትም ነበር፡፡

በመሆኑም ሕዝቡ ፍላጎትና እውነቱን ሲናገር፣ የህዝብን ሳይሆን የፍላጎታቸውን ለመፈጸም የሚታትሩት አንዳንድ የውጭ ኃይሎች ጆሮ ሰጥተው እንዲያደምጡት እና ከዚህ ተግባራቸው እንዲታቀቡ በመሆኑ፣ እነዚህ አገራት ለህዝቡ ድምጽ ጆሮ መስጠትና ካልተገባ ጣልቃ ገብነታቸው ሊታቀቡ ይገባል፡፡ ዓለምአቀፉ ማኅበረብም ኢትዮጵያውያን በየደጁ የሚያደርሱትን ፍትሃዊ መልዕክት እና እውነት ሊገነዘብ፣ ጣልቃገብነትንና የሴራ ጉዞንም ሊያወግዝ ያስፈልጋል!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የተሰጥዖ ትምህርት ቤት ለአገር በቀል ዕውቀት

ሚሊዮን ሺበሺ

ባለፈው ሐሙስ ጥቅምት 10 ቀን 2015 ዓ.ም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር አብይ አህመድ በተገኙበት በቡራዩ ከተማ የልዩ ተሰጥዖ ኢንስቲትዩት ተመርቋል።የኢንስቲትዩቱ ምረቃ እንደ ቀላል መታየት ያለበት አይደለም።በአንድ አካባቢ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም (ዩኒቨርሲቲ) ተገንብቶ ተማሪዎችን መቀበል ሲጀምር ትልቅ ዜና እንደሚሆን ሁሉ ግንባታው ከዚያም በላይ ነው።ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደገለጹት ዕውቀት ወደ ተግባር የሚቀየርበት ተቋም ነው።

አስታውሳለሁ! በዘመነ ኢህአዴግ በየትኛውም ምሁር እና የፓርቲ አመራሮች በሥርዓተ ትምህርቱ ላይ ይነሳ የነበረው ቅሬታ፣ የተግባር ተማሪዎችን መፍጠር አልተቻለም የሚል ነበር።ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተማሪዎቻቸውን ባስመረቁ ቁጥር ይሰጥ የነበረው አስተያየት ‹‹የአውሮፓ ቲዎሪ ብቻ ተምሮ መመረቅ ምን ዋጋ አለው!›› የሚል ነበር።መንግሥት በአፉ ‹‹ተግባር ተኮር›› ቢልም መሬት ላይ ግን የታየ የተግባር ትምህርት አልነበረም፡፡

እነሆ አሁን እነዚያ ይነሱ የነበሩ ቅሬታዎች መልስ ሊያገኙ ይመስላል።የልዩ ተሰጥዖ ትምህርት ቤቱ እጅግ ሊደነቅና ሊመሰገን የሚገባ ሥራ ነው።ምክንያቱም ለብዙ ተማሪዎች እና በተለያየ ሙያ ውስጥ ላሉ ሰዎች መነሳሳትን ይፈጥራል።ባክነው የሚቀሩ የፈጠራ ሀሳቦች ዕውቅና እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

ከምንም በላይ ደግሞ የዚህ የልዩ ተሰጥዖ ኢንስቲትዩት ዋና ጠቀሜታው አገር በቀል ዕውቀት እንዲስፋፋ ያደርጋል።በተደጋጋሚ እንደሚባለው ኢትዮጵያ የብዙ ሥልጣኔዎች መነሻ ናት።በብዙ ዘርፍ ተሰጥዖ ያላቸው ሰዎች ያሉባት ናት፡፡

ዳሩ ግን በቅድመ አያቶቻችን ጥበብ በመፎከር ነበር የምንኖር።አክሱምና ላሊበላን በሰሩ አባቶቻችን ከመፎከር፣ ልክ እንደ እነርሱ አይነት የፈጠራ ሰዎች የሚወጡበትን ዕድል መስጠት ነው ታሪክ መሥራት ማለት።ሞፈርና ቀንበር ከእንጨት አዘጋጅተው እርሻ ባስጀመሩ አያቶቻችን እነሆ ሦስት ሺህ ዘመናት ተጠቀምን።ዛሬ ደግሞ እርሻን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የሚያስጀምሩ ሰዎች ያስፈልጉናል፣ ስለዚህ ይህ የሚጀመርበትን ዕድል መፍጠር ታሪክ መሥራት ነው።

ይህን የልዩ ተሰጥዖ ኢንስቲትዩት ማሰብ በራሱ ልዩ ተሰጥዖ ነው፣ ፈጠራ ነው።ምክንያቱም እስከዛሬ ያልነበረ ነው።ትኩረት ሳይሰጠው የኖረ ጉዳይ ነው።አገር በቀል ዕውቀቶችና ሀሳቦች ተዳፍነው ነበር የኖሩ፣ የእንዲህ አይነት የተቋም ግንባታ መጀመሩ መነቃቃትን ይፈጥራል።አዲስ የአስተሳሰብ አብዮት ያመጣል ነው፡፡

ተሰጥዖን በተመለከተ በየዘርፉ ካሉ ባለሙያዎች የምንሰማው አንድ ተደጋጋሚ ቅሬታ ነበር።ይሄውም ኢትዮጵያ ውስጥ ለልዩ ተሰጥዖ ትኩረት አይሰጥም የሚል ነበር።አንድ ተማሪ የተለመደውን የክፍል ውስጥ ትምህርት ማለፊያ ነጥብ አምጥቶ፣ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ ተመርቆ እስካልወጣ ድረስ እንደ ባለሙያ አይቆጠርም ነበር ፡፡

ለምሳሌ፣ ሰዓሊ ቢሆን እንደ ሰነፍ ተማሪ ነው የሚቆጠር።የሥዕል ሙያ ሳይንስም ጥበብም መሆኑ ልብ አይባልም።ሙዚቀኛ ቢሆን እንደ ሰነፍ ተማሪ ነው የሚቆጠር።ድምጽ እንደ ተሰጥዖ (እንደ መታደል) አይቆጠርም።የሙዚቃ መሳሪያዎችን መሥራት እንደ ችሎታ (ጥበብ) አይታይም።በአካባቢው የሚያስተውላቸውን ነገሮች (የመገልገያ ዕቃዎች፣ የጦር መሳሪያዎች፣ የባህል ቤቶች...) አስመስሎ የሚሰራ ተማሪ ትኩረት አይሰጠውም ነበር።

አሁን ግን የዚህ የልዩ ተሰጥዖ ኢንስቲትዩት መጀመር ለእነዚህ ሁሉ ትኩረት እንዲሰጥ ያደርጋል።አንድ ሰው በአንድ ነገር ደካማ ቢሆን ሌላ የሆነ ተሰጥዖ ይኖረዋል።የማህበራዊ ሳይንስ ትምህርቶች የማይገቡት ተማሪ ጎበዝ የሒሳብ ወይም የኬሚስትሪ ሊቅ ሊሆን ይችላል።ዳሩ ግን በእነዚያ ትምህርቶች ምክንያት ውጤት ካልመጣለት ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ወይም ወደ መሰናዶ ትምህርት ቤት ላይገባ ይችላል።እንዲህ አይነት የልዩ ተሰጥዖ ተቋማት ካሉ ግን ይህ ልጅ የሚሰራቸው የጂኦሜትሪ ሙያዎች አስተዋይ ያገኛሉ ማለት ነው፡፡

የተፈጥሮ ሳይንስ (ሒሳብ፣ ኬሚስትሪ፣ ፊዚክስ...) የማይችል ተማሪ የተዋጣለት ደራሲ፣ ድምጻዊ፣ ሠዓሊ፣ ተዋናይ... ሊሆን ይችላል።ዳሩ ግን በተፈጥሮ ሳይንሶች ምክንያት ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚያደርስ ውጤት ላያመጣ ይችላል።እንዲህ አይነት የልዩ ተሰጥዖ ተቋማት መኖራቸው ግን የዚህ ልጅ ተሰጥዖ ተዳፍኖ እንዳይቀር ያደርጋል ማለት ነው።

በቡራዩ የተጀመረው የልዩ ተሰጥዖ ኢንስቲትዩት ለጊዜው ጅማሮ ነው።በውስን የተሰጥዖ አይነቶች ላይ ይሁን በሁሉም የተሰጥዖ አይነቶች ለጊዜው ወሰኑ አልታወቀም።አንድ ሺህ ባለ ልዩ ተሰጥዖ ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር እንደሚችል ነው በዜናው የተገለጸው።ያም ሆነ ይህ ዋናው ቁም ነገሩ ግን ሰርቶ ማሳያ ሆኖ መጀመሩ ነው።ሌሎች አካባቢዎችም እንዲህ አይነት ተቋማ ሊገነቡ ይገባል፡፡

ተሰጥዖ በብዙ ሰዎች ውስጥ አለ።ምናልባት ብዙ የተለመደው በትምህርት ቤቶች ስለሆነ (የመታየት ዕድል ስላለው) ተማሪ ብቻ ይመስለናል እንጂ የትምህርት ዕድል ያላገኙ ብዙ ባለተሰጥዖዎች አሉ።መንግሥት ተቋማትን ሲገነባ እኛ ደግሞ ሕብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ባለተሰጥዖዎች ይህን ዕድል እንዲያገኙ መንገር አለብን።

በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች እንደየ አካባቢው ባህልና ልማድ የተለያየ ተሰጥዖ ያላቸው ሰዎች አሉ።ባህላዊ የመገልገያ ዕቃዎች የሚሰሩት በአካባቢው ጥበበኞች ነው።እነዚህ የመገልገያ ዕቃዎች በባህላዊ መንገድ ስለሚሰሩ ሳይንሳዊ ይዘት ያላቸው አይመስለንም።ብዙ ጊዜ የሳይንስ ውጤት የሚመስለን በማሽን የሚሰራ የፋብሪካ ዕቃ ብቻ ነው።

በባህላዊ መንገድ የሚሰሩ መኖሪያ ቤቶች የፊዚክስ ሳይንስ የተተገበረባቸው ናቸው።በባህላዊ መንገድ የሚሰሩ አልባሳት የቴክስታይል ውጤት ናቸው።በባህላዊ መንገድ የሚሰሩ ምግቦች ሰሪዎቹ አስበውት ባይሆንም የኬሚስትሪ ዕውቀት የተተገበረባቸው ናቸው።የባህል መጠጦች የኬሚስትሪ ውጤት ናቸው።

እነዚህን ነገሮች ወደ ሳይንሱ ማምጣት ነው ቴክኖሎጂ ማለት።መንግሥት እነዚህ የተሰጥዖ ባለቤቶች ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ጋር እንዲገናኙ የሚያደርግ ማዕከል መፍጠሩ ትልቅ ታሪካዊ አሻራ ነው።አገር በቀል ዕውቀቶች ወደ ሥርዓተ ትምህርቱ እንዲመጡ ያደርጋል።

ለሳይንስና ቴክኖሎጂው ግብዓት የሚሆኑ የፈጠራ ሥራዎች እንዳሉ ሁሉ ለማህበራዊ ሕይወት ግብዓት የሚሆኑ ብዙ የፈጠራ ጥበቦችም አሉ።የአብሮነት፣ የፍቅር፣ የእርስበርስ መተዋወቅ እና አንዱ ሌላውን እንዴት እንደሚያከብር የሚያሳዩ የባህል እና የጥበብ ሥራዎች አሉ።እነዚህም በእንዲህ አይነት የተሰጥዖ ማዕከላት ቦታ ትኩረት ያገኛሉ ማለት ነው፡፡

ይህ የልዩ ተሰጥዖ ትምህርት ቤት በተለይም የቴክኖሎጂ ግብዓቶች ተደራሽ ላልሆኑ የገጠር ተማሪዎች ጥሩ ዕድል ነው።‹‹የእጅ ሥራ›› የሚባል የትምህርት ክፍለ ጊዜ በነበረበት ወቅት (አሁን ይኑር አይኑር አላውቅም) ብዙ የፈጠራ ሥራዎች ባክነው ይቀሩ ነበር።ምንም እንኳን እኔ የእጅ ጥበበኛ ባልሆንም ብዙ የትምህርት ቤት ልጆች ግን አስገራሚ የሆኑ የእጅ ሥራዎችን ሰርተው እዚያው የትምህርት ቤቱ ማጠራቀሚያ ማዕከል ውስጥ ይቀመጥ ነበር፡፡

እንዲህ አይነት የተሰጥዖ ተቋማት ከተመሰረቱ ግን ባክኖ የሚቀር ተሰጥዖ አይኖርም ማለት ነው።መንግሥት ለሰራው ሥራ እያመሰገንን ተማሪዎች የዕድሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሁላችንም የድርሻችንን እንወጣ።

ዓባይ ባንክ
Abay Bank

# የዓባይ ባንክ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች አስራ ሦስተኛ መደበኛ እና ሰባተኛ አስቸኳይ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ የጥሪ ማስታወቂያ

የዓባይ ባንክ አ.ማ የባለአክሲዮኖች አስራ ሦስተኛ መደበኛ እና ሰባተኛው አስቸኳይ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሕዳር 10 ቀን 2015 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ጀምሮ በአዲስ አበባ ከተማ ኢንተር ሌግዠሪ(የቀድሞ ኢንተርኮንትኔንታል) ሆቴል ይካሄዳል፡፡ ስለሆነም የባንኩ ባለአክሲዮኖች በተጠቀሰው ቀንና ቦታ እንድትገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

1. <u>የአስራ ሦስተኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች፤</u>
   - 1.1 ድምጽ ቆጣሪዎች መሰየምና ማጽደቅ፣
   - 1.2 ምልዓተ ጉባዔ መሟላቱን ማረጋገጥ፣
   - 1.3 የጉባዔውን አጀንዳ ማጽደቅ፣
   - 1.4 የአዳዲስ አክሲዮኖች ሽያጭ እና የአክሲዮን ዝውውሮችን ማጽደቅ፣
   - 1.5 የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ፣
   - 1.6 የውጭ ኦዲተሮች ዓመታዊ ሪፖርት ማዳመጥ፣
   - 1.7 ከላይ በተራ ቁጥር 1.5 እና 1.6 በቀረቡ ሪፖርቶች ላይ ተወያይቶ መወሰን፣
   - 1.8 የዘመኑ የተጣራ ትርፍ አደላደል እና አከፋፈል ላይ ተወያይቶ መወሰን፣
   - 1.9 የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት አበልና የአገልግሎት ክፍያ መወሰን፣
   - 1.10 የውጭ ኦዲተር ሹመት ማጽደቅና ክፍያ መወሰን፣

2. <u>የሰባተኛው አስቸኳይ ድንገተኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች፤</u>
   - 2.1. ድምጽ ቆጣሪዎች መሰየምና ማጽደቅ፣
   - 2.2. ምልዓተ ጉባዔ መሟላቱን ማረጋገጥ፣
   - 2.3. የጉባኤውን ረቂቅ አጀንዳ ማጽደቅ፣
   - 2.4. የባንኩን ካፒታል ለማሳደግ ተወያይቶ መወሰን፤
   - 2.5. የባንኩን መመሥረቻና መተዳደሪያ ደንብ ማሻሻል፤

<u>ማሳሰቢያ</u>

ባለአክሲዮኖች የታደሰ መታወቂያ ካርድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒውን በመያዝ በግንባር በመገኘት ወይም የባለአክሲዮኖች ህጋዊ ተወካዮች አግባብነት ካለው የመንግስት አካል የተሠጠ ውክልና ሰነድ ዋናውንና ፎቶ ኮፒ እንዲሁም የወካይና ተወካይ የመታወቂያ ካርድ ዋናውንና ፎቶ ኮፒውን ይዛችሁ በጉባኤው ላይ መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡ በጉባኤው ላይ በግንባር መገኘት የማትችሉ ባለአክሲዮኖች ከስብሰባው ዕለት ሶስት ቀን ቀደም ብሎ ባንኩ ድረስ በመቅረብ የተዘጋጀውን የውክልና ቅጽ በመሙላት ተወካዮቻችሁን ማሳተፍ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን፡፡ በተጨማሪም ጆሞ ኬንያታ መንገድ፣ ዝቋላ ኮምፕሌክስ ህንጻ በሚገኘው የባንኩ ዋና መሥሪያ ቤት በግንባር በመቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር 0115549735 በመደወል ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡፡

**የዓባይ ባንክ አ.ማ. የዳይሬክተሮች ቦርድ**

ዓባይ - ታማኝ አገልጋይ!
Abay : The Trustworthy Bank !

+251 115 549 735
+251 115 549 731
info@abaybank.com.et
www.abaybank.com.et
Head Office: Zequala Complex, JomoKenyatta Avenue, Addis Ababa, Ethiopia

ዜና

# ከአሸባሪው ትሕነግ ጎን በመቆም የሀገርን ሉዓላዊነትን የሚዳፈሩ የውጭ ሃይሎች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ ተጠየቀ

ፍቃዱ ዴሪሳ

አዲስ አበባ፡- ከአሸባሪው ትሕነግ ጎን በመቆምና ቡድኑን እንደ መሣሪያ በመጠቀም የሀገራችንን ሉዓላዊነት የሚዳፈሩ የውጭ ሃይሎች ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ ነዋሪዎች ጠየቁ፡፡

‘ለኢትዮጵያ እቆማለሁ ድምጼን አሰማለሁ’ በሚል መሪ ቃል በአዲስ አበባ ከተማ በተደረገው ሰልፍ ላይ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ያነጋገራቸው የመዲናዋ ነዋሪዎች እንዳሉት የአባቶቻችን የነፃነት ድል በመድገም ኢትዮጵያ በውጭ ሃይሎች የሚደርስባትን ጫና በጋራ እንከላከላለን ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ለማስከበር መንግሥት የሚያከናውነው ተግባር የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የሚያስጠብቅ በመሆኑ በሽብርተኞች ላይ የሚወሰደው እርምጃ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

የውጭ ሀገራት ሉዓላዊ በሆነችው ሀገር ላይ የሚያደርጉት ጣልቃ ገብነትና የሚያደርሱትን ጫና እንደሚያወግዙ ግልፅ በሆነ መንገድ ለመላው ዓለም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

ምዕራባውያን በግልፅ ሀገርን ለመበታተን የተነሳን የሽብር ቡድን በመደገፍና ኢትዮጵያ ላይ ደግሞ የተለያዩ ዓለም አቀፋዊ ጫናዎችን ማሳደር በሀገሪቱ የውስጥ ጉዳዮች ላይ ጣልቃ በመግባት ሀገርን ከሚበታትን ድርጊት እጃቸውን እንዲያነሱ ጠይቀዋል፡፡

ለዘመናት ኢትዮጵያውያንን በዘርና በኃይማኖት በመከፋፈል ለሀገር ሰላም ነቀርሳ ሆኖ የቆየው የትህነግና ሌሎች ተላላኪ የሽብር ቡድኖች ኢትዮጵያን ለመበታተን የሚያሴሩትን ሴራ በጋራ በመሆን እየተቀለበሰ ሲሆን



ሃይልየሱስ ገረመው /ከቤንሻንጉል/



ዮርዳኖስ ማሞ



ዘውድ አደም

በዚህ ሂደትም የድርሻቸውን እንደሚወጡ ተናግረዋል፡፡

በኢትዮጵያ ላይ እጁን በሚያነሳ አካል ላይ ሁሉ በመዝመትና የተለያዩ ንቅናቄዎችን በማድረግ እንዲሁም የሚያስፈልውን ድጋፍ ሁሉ በማድረግ የውጭ ሃይሎች ከኢትዮጵያ ላይ እጃቸውን እንዲያነሱ ጠይቀዋል፡፡

ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት መከበር እያንዳንዱ ዜጋ ሚናው የጎላ በመሆኑ ዜጎች የሚጠበቅባቸውን ማንኛውንም ኃላፊነትና መስዋዕትነት በመክፈል መላው ኢትዮጵያውያን ከመንግሥት ጎን መቆም እንዳለባቸው ጠይቀዋል፡፡

ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያ ሉዓላዊነቷንና የግዛት አንድነቷን ለመድፈር የመጡ ታሪካዊ ጠላቶች ዛሬም በተዘዋዋሪ መንገድ ሀገሪቱን ለማንበርከክ ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ መሆኑን የተናገሩት ነዋሪዎቹ፤ ዛሬም እንደ ቀድሞ አባቶቻችን ጠላትን የመመከት አቅምና ድፍረት በመጠቀም ሀገራችንን ልንታደጋት ይገባል ብለዋል፡፡

በድርድር ሥም ሰቆቃችንና የሕወሓት እድሜን ማራዘም ይብቃ ፣ ሕወሓት የችግሩ ምንጭ ነው፣ የትግራይ ወጣቶች በሽብርተኛው ስም ሕይወቱን ሊገብር አይገባውም እና ሌሎች መፈክሮችን በመያዝ ድምጻቸውን አሰምተዋል።

ድህነታችንን ምክንያት በማድረግ በተለያዩ ረጂ ድርጅቶችና እርዳታ ስም እንዲሁም ሌሎች ምክንያቶችን በመጠቀም የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የሚዳፈር ተግባር ከምዕራባውን ሀገራት የሚስተዋል በመሆኑ ይህን የጣልቃ ገብነት ምክንያቶችን በማጥበብ የሀገራችንን ክብር ማስቀጠል ይጠበቅብናል ብለዋል፡፡

ሀገራችን በየወቅቱ የሚገጥማትን የጠላት ወረራና የህልውና ፈተና በጀግኖች አባቶቻችን እንዲሁም በአሁኑ ትውልድ የተባበረ ክንድ በጀግነት፣ በመስዋዕትነትና በአንድነት እየመከተች እንዲሁም እያሸነፈች ሉዓላዊነቷን አስጠብቃ የቆየችና ለወደፊቱም በዚሁ ልክ የምትቀጥል ሀገር እንደምትሆን ተናግረዋል፡፡

## ያልተገባ ጣልቃ ገብነትን የሚያወግዙ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጅግጅጋ ከተማን ጨምሮ በክልሉ በሚገኙ የተለያዩ ከተሞች በተካሄደው ሕዝባዊ ሰልፍ በያዟቸው መፈክሮች፤ የውጭ ሃይሎች በኢትዮጵያ ላይ ጫና ለመፍጠር የሚያደርጉት ጥረት በመላው ሕዝብ ተቀባይነት የለውም ብለዋል።

በሀገሪቱ እየተፈጠረ ለሚገኘው ችግር ምንጩ አሸባሪው ትሕነግ ነው፣ ምዕራባውያን ሉዓላዊነታችንን አክብሩ፣ በሉዓላዊነታችን አንደራደርም፣ በሰብዓዊ እርዳታ ስም ጣልቃ ገብነቱ ይቁም፣ አሸባሪው ወያኔ ቅጥረኛ ነው፣ የትግራይ ሕዝብ ወገናችን ነው የሚሉ መፈክሮች ተሰምተዋል፡፡

በድርድር ስም የአሸባሪው ሕወሓትን እድሜ ማርዘም ይብቃ፣ አሸባሪው ወያኔ ለአራተኛ ዙር ጥቃት ዕድል መስጠት አይገባም፣ ሁለት ሠራዊት በአንድ ሉዓላዊት ሀገር አይኖርም፣ ለዘላቂ ሰላም አሸባሪው ሕወሓት ትጥቅ ይፍታ የሚሉና ሌሎች የሰልፉን ዓላማ የሚያንጸባርቁ መልዕክቶችም ተላልፈዋል።

በአፋር ክልል ሠመራ ከተማ በተካሄደው ሰልፍም የሠመራና ሎግያ ከተማ ነዋሪዎች የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ተገኝተዋል። በሰልፉም የምዕራባውያን በሀገራችን የውስጥ ጉዳይ ያልተገባ ጣልቃ ገብነት ይቁም፣ አሸባሪው ትሕነግ የታሪካዊ ጥላቶቻችን ተላላኪና ቅጥረኛ ነው፣ የሀገራችንን ህልውና ለማስከበር ከመከላከያ ሠራዊታችንና መንግሥት ጎን እንቆማለን የሚሉ መፈክሮች ተሰምተዋል።

በተመሳሳይ የጋምቤላ ከተማና የአካባቢው ነዋሪዎች የውጭ ሃይሎች በኢትዮጵያ ላይ እያደረጉ ያለው ያልተገባ ጫናና የሕወሓት የሽብር ቡድን እኩይ ስራ የሚያወግዝ ሰልፍ አካሂደዋል።

ነዋሪዎች ሰላማዊ ሰልፉ ላይ ሉዓላዊነታችንን አክብሩ፣ የትግራይ ሕዝብ ወገናችን ነው፤ ጁንታው ጠላታችን ነው፣ በሉዓላዊነታችን አንደራደርም፣ ለዘላቂ ሠላም ሕወሓት ትጥቅ ይፍታ የሚሉትን መፈክሮች በስፋት አሰምተዋል።

በድሬዳዋ ከተማም አሸባሪ ቡድኑን እና የምዕራባውያን ጣልቃ ገብነትን የሚያወግዝ ሰልፍ በተመሳሳይ መልክ ተካሂዷል። በሰልፉ ላይ ከድሬዳዋ ከተማ እና ከ38ቱ የገጠር ቀበሌዎች የተውጣጡ በርካታ ነዋሪዎች ተገኝተዋል።

በሲዳማ ክልላዊ መንግሥት ሃዋሳ ከተማ በተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍም ሃዋሳን ጨምሮ በሶስት የሲዳማ ከተሞች ይርጋለም አለታወንዶ እና ዳየ ከተሞች ተካሂደዋል፡፡ ሰልፈኞቹ የተለያዩ መፈክሮችን ያነገቡ ሲሆን፤ “በድርድር ምክንያት ሰቆቃዎችንና የአሸባሪውን ቡድን እድሜ ማርዘም ይብቃ” የሚሉና ጀግናው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊትን የሚደግፉ መፈክሮችን የያዙ ሠልፈኞች ከፍተኛ ሞራልና ወኔ በተንጸባረቀበት ስሜት አሰምተዋል።

በተመሳሳይም በሐረሪ ክልል ሕዝባዊ ሰልፉ ተካሂዷል፡፡ በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርገው የውጭ ጫናን የሚቃወም እና የአሸባሪው ሕወሓት ተግባር የሚያወግዝ ሕዝባዊ ሰልፍ በሐረሪ ክልልም ተካሂዷል። ነዋሪዎቹ ሰልፉን ያካሄዱት በከተማው ዋና ዋና መንገዶች ላይ በመዟዟርና መፈክር በማሰማት ነው።

ሰልፈኞቹ ሕወሓት የችግር ምንጭ ነው፣ ሕወሓት ቅጥረኛ ነው፣ ሉዓላዊነታችንን አክብሩ የሚሉ መልዕክቶችን ባሰሙት መፈክር አስተላልፈዋል። አንድነታችንና ሰላማችንን ጠብቀን የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት እናስቀጥላለን፣ የሽብር ቡድኑ የከፈተብንን ጦርነት በጋራ እንመክታለን የሚሉ መፈክሮችንም አሰምተዋል።

በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ ከተማ የውጭ ጣልቃ ገብነትን ለመቃወም በተጠራው ሕዝባዊ ሰልፍ ላይ የተሰሙ መፈክሮች፤ “ኢትዮጵያ የሠላም እና የመረጋጋት ጊዜዋ ደርሷል፣ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እንድትቀጥል መስዋዕትነት ለሚከፍለው መከላከያ ሠራዊት ክብር ይገባዋል፣ የውጭም ሆነ የውስጥ ጠላቶቻችንን መመከት የምንችል ታላቅ ሕዝብ ነን!” የሚሉ ይገኙበታል፡፡

በሙቱ ከተማ ከሁሉም የኢሉአባቦር ዞን ወረዳዎች የመጡ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በሕዝባዊ ሰልፉ ተሳትፈዋል።

“አባቶቻችን በደማቸው ሉዓላዊነቷን አስከብረውና ጠብቀው ያቆዩአትን ሀገር በላባችን ደግፈን እናስቀጥላለን፣ ምዕራባውያን በሀገራችን ላይ የሚያደርጉትን ጣልቃ ገብነት እንቃወማለን፣ በሉዓላዊነታችን አንደራደርም፣ አሸባሪው ሕወሓትና ኦነግ ሸኔ መቼም ሊወዳጁን አይችሉም፣ የውስጥና የውጭ ትንኮሳን በአንድነታችን እንመክታለን!” የሚሉና ሌሎችም የሕዝባዊ ሰልፉን ዓላማ የሚያንጸባርቁ መፈክሮች ተስተጋብተዋል።

በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ ዞኖች የሚገኙ ነዋሪዎች ‘ለኢትዮጵያ እቆማለሁ፣ ድምጼን አሰማለሁ’ በሚል መሪ ቃል ሰላማዊ ሰልፍ አካሂደዋል።

የምዕራብ ወለጋ ዞን ነዋሪዎች በኢትዮጵያ ላይ እየተደረገ ያለው ጣልቃ ገብነትን በመቃወምና ለጀግናው መከላከያ ሠራዊት ያላቸውን ድጋፍ ጊምቢ ከተማ ባካሄዱት ሕዝባዊ ሰላማዊ ሰልፍ ገልጸዋል።

በሰልፉም የአሸባሪዎቹን ሕወሓትና ሸኔን አገር የማፍረስ የሽብር እንቅስቃሴን ተቃውመዋል።

ሰልፈኞቹ “አሸባረው ሕወሓትና ሻኔ ጠላታችን ናቸው፣ እኛ እያለን አገራችን አትፈርስም፣ አገራችን ላይ እየተደረገ ያለው የውጭ ጣልቃገብነት እንቀወማለን፣ ጀግናው መከላከያ ሠራዊታን የሀገራችን መከታ ነው” የሚሉ መፈክሮችን አሰምተዋል።

በተመሳሳይ በሰሜን ሸዋ ዞን ፍቼ ከተማም በአንዳንድ ምዕራባውያን በኩል እየተደረገ ያለውን ጣልቃ ገብነት የሚያወግዝ ሰልፍ ተደርጓል።

በሆሳዕና፣ በጂንካ እና ዲላ ከተሞችም በተካሄዱት ሕዝባዊ ሰልፎች የውጭ ሃይሎች ለአሸባሪው ቡድን እያሳዩት ያለውን ውግንና እንዲሁም በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርጉትን ያልተገባ ጫና እንዲያቆሙ በድምጽና በመፈክር ጠይቀዋል።

## ‹‹በአሸባሪው ሕወሓት ፕሮፓጋንዳ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የሚያደርጉትን ጣልቃ ገብነት የሚቃወም ሕዝባዊ ሰልፍ በትናንትናው ዕለት በአዲስ አበባ ከተማ በመስቀል አደባባይ ተካሂዷል።

በሰልፉ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ እና የሥራ፣ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጃንጥራር፤ ዛሬ በኢትዮጵያ ላይ ስለተከሰተው ጦርነት ሳይገባችሁ እና ሳትረዱ በተሳሳተው የሽብር ቡድን ሕወሓት ፕሮፖጋንዳ የተወሰዳችሁ እና ኢትዮጵያን ለመበተን ለተሸረበው አደጋ አውቃችሁም ሆነ ሳታውቁ እንቅስቃሴ የምታደርጉ ሁሉ ተሳስታችኋል እና ተመለሱ ሲሉ አሳስበዋል፡፡

“ተላላኪ በመሆን ኢትዮጵያን የምታስጠቁ ሁሉ አገር የሌለው ክብር የለውም፤ ኢትዮጵያን አታድሙ” ያሉት ምክትል ከንቲባው፤ ኢትዮጵያውያን የአገራቸውን ሉዓላዊነት መቼም አሳልፈው አይሰጡም፤ ሉዓላዊነታችንና የግዛት አንድነታችንን በጋራ ማስከበራችንን እንቀጥላለን ሲሉ አፅንኦት ሰጥተው ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ አይበግሬነት ተምሳሌትና የቅኝ ገዢዎችን ሕልም ያመከነች የነፃነት ተምሳሌት የሆነች አገር መሆኗን ሊዘነጋ እንደማይገባው ያስገነዘቡት ምክትል ከንቲባው፤ በሌላ በኩል ሀገሪቷ ሉዓላዊነቷን እንድታስከብር ከጎኗ የቆማችሁ ሁሉ ክብር ይገባችኋል ሲሉ አመስግነዋል።

አቶ ጃንጥራር እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያን አንገት ለማስደፋት የሚጥሩ አካላት ሁሉ እጆቻቸውን መሰብሰብ አለባቸው፡፡ ኢትዮጵያውያን ከዕለት ፍጆታ ይልቅ ለክብራቸው ቦታ ይሰጣሉ፡፡ ስለዚህም በአይበገሬ ክንዳቸው ሀገራቸውን ይከላከላሉ፡፡ አሸባሪው ሕወሓት ኢትዮጵያን ካልመራሁ ትፍረስ ብሎ ሦስተኛ ዙር ጦርነት መክፈቱን ገልጸው፤ ኢትዮጵያውያን በጋራ በመሆን አገራቸውን ለማዳን የሽብር ቡድኑን በመከላከል ላይ ይገኛሉ ሲሉ ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳዮች ጫና የምታደርጉ አንዳንድ የምዕራባውያን ሀገራት ነፃነትና ሥልጣኔን የምትወዱትን ያህል በእኛም ሀገር የልማት ተግባራትን ደግፉ እንጂ አሸባሪ እየደጎማችሁ አታባሉን እኛም በደም የቆመች ሀገራችንን አሳልፈን የምንሰጥ ሕዝቦች አይደለንም ሲሉ ገልጸዋል።

ለመላው የትግራይ ሕዝብም ከአሸባሪው ወያኔ ያተረፈው እንደሌለ በመጠቆም አንድነትን ከኢትዮጵያውያን ጋር በማድረግ ሰላምን ማረጋገጥ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

በውጭው ዓለም ያሉ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ስለሚያደርጉት አስተዋጽኦ ሁሉ ምሥጋና ያቀረቡት ምክትል ከንቲባው፤ አሸባሪው ትህነግ የከፈተውን ጦርነትና የምዕራቡን ዓለም ሳንካነት በማውገዛችሁ ክብር ይገባችኋል ሲሉ አመስግነዋል።

ስለኢትዮጵያ የምናደርገውን ተጋድሎ አጠናክረን እንቀጥላለን፤ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ድል የኛ ይሆናል ሲሉ የተናገሩት ምክትል ከንቲባ ጃንጥራር፤ የአዲስ አበባ ሕዝብ ለመከላከያ ሠራዊቱ ደጀንነቱን አጠናክሮ ይቀጥላል ብለው ሕዝቡ ለኢትዮጵያ ክብር መጠበቅ ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ ነው ሲሉም መልዕክታቸውን ቋጭተዋል።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# ‹‹አየር መንገዳችን ጥሩ ሥም ስላለው፤ እዚያ መሰልጠኔ ለእኔ ረድቶኛል››

ካፒቴን ነስሩ ከማል



**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

ቆፍጠን ያሉ ናቸው፤ በውትድርና ሕይወት ውስጥ ያለፉ ስለመሆናቸው የሰውነታቸው ተክለ ቁመና፣ የቢሯቸው ውበትና ንፅህና፣ የፋይል አሰዳደራቸው ይናገራል።ሁሉ ነገራቸው ጥንቅቅ ያለ ነው።ንግግራቸው የተረጋጋ፤ ጨዋታቸው የሰከነ ነው።ህይወት እንደ ገብስ ቆሎ ፍትግ፤ እንደ ሽንኮራ አገዳ ምጥጥ አድርጋ ልትተፋቸው ስትማስን፤ እርሳቸው ግን ሰንኮፎችን ሁሉ ነቃቅለው የስኬት መንገድን በራሳቸው ጥረት ተቆናጠዋል።በቤት አባወራነትም የተመሰገኑ፤ ለልጆቻቸውም አርዓያ ስለመሆናቸው ይነገርላቸዋል።ይህን ጥረታቸውንና ጥንካሬያቸውንም አብረዋቸው ለሚሰሩ የሚያካፍሉና ከሰው ጋር አብሮ ማደግን አብዝተው የሚመኙ ስለመሆናቸውም እንዲሁ።

ሰውየው የዋዛ አይደሉም ችግር ማረፊያ ሊያደርጋቸው ፈልጎ ወደ እርሳቸው ሄደ።እርሳቸው ግን በመልካም አጋጣሚ ቀይረውታል።‹‹ቅቤ እንደምን ጣፈጥሽ ቢሏት ተገፍቼ›› ይሉት ብሂል፤ እርሳቸው ከሥራ ገበታቸው መገፋታቸው፤ የተስፋ መቁረጥ ሳይሆን የጥንካሬ ምንጭ ሆኗቸው መገፋታቸው የስኬትን መንገድ የከፈተላቸው እንደ አሎሎ ብረት ያበረታቸው፤ በቀላሉ የማይረቱ ሰውናቸው ያላሰለሰ ጥረታቸው ታክሎበት ነው።ሰዎች ስለ እርሳቸው ሲናገሩ፤ በተቻለ አቅም የሚለግሱ፤ ተስፋ የማይቆርጡ፣ አገራቸውን የሚወዱና አስተዋይ ይሏቸዋል።

የዛሬ እንግዳችን ካፒቴን ነስሩ ከማል ቀጠሯችንን ቦሌ ብራዚል ኤምባሲ አጠገብ ከሚገኝ ቢሯቸው አድርገን፤ ከብዙ ሕይወታቸውና ማንነታቸው ‹‹ዓባይን በጭልፋ›› ይሉት አይነት አጫውተውናል።

**ውልደትና ዕድገት**

ካፒቴን ነስሩ ከማል የተወለዱት በቀድሞ አጠራር ሸዋ ክፍለ አገር በአሁኑ ስያሜው ጉራጌ ዞን እኖር ወረዳ ሎማ በምትባል መንደር ነው።ገና የአራት ዓመት ሕፃን ሳሉ ወደ አዲስ አበባ መጡ። ‹‹ሀ፤ ሁ›› ብለው ከፊደል ጋር የተዋወቁት በቄስ ትምህርት ነው።ከዚያ ከ1ኛ እስከ 6ተኛ ክፍል ቀለመወርቅ ትምህርት ቤት፤ አርበኞች ትምህርት ቤት ደግሞ ከ7ተኛ እስከ 9ነኛ ክፍል ድረስ የተማሩ ሲሆን፤ ከ9ነኛ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ ደግሞ በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ተምረዋል ።1973 ዓ.ም በተፈሪ መኮንን 12ተኛ ክፍል ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ባለሞያዎችን ለመቅጠር ማስታወቂያ አውጥቶ ስለነበር መስፈርቱን በሙሉ አሟልተው በመገኘታቸው ከሥመ ገናናው ተቋም ተቀላቀሉ።በወቅቱም መስፈርቱን ያሟሉ 80 የሚሆኑ ባለሙያዎች ተቀጥረው ነበር።በዚህ ተቋምም የሚጠበቅባቸውን ሲከውኑ ቆዩ፡፡

**ከአየር ኃይል ወደ አየር መንገድ**

ወደ አየር መንገድ በወቅቱ ኢትዮጵያ ጦርነት ላይ ስለነበረችም ብዙ ፓይለቶች ይፈለጉ ነበር።ሆኖም በዚያን ጊዜ አየር ኃይል በቂ አውሮፕላኖች ስላልነበሩት ምልምል አባላት የነበሩትን ባለሙያዎች ሦስት ቦታ እንዲከፋፈሉ ተወሰነ።ከዚህም ውስጥ 21 የሚሆኑት ወደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ሲቀላቀሉ ከእነዚህ ውስጥ ካፒቴን ነስሩ ከማልም አንዱ ነበሩ።ዓላማው የነበረውም በአየር መንገድ ቆይታቸው ፈቃድ ያላቸው (ላይሰንስድ) እንዲሆኑ ማስቻል ነበር።በዚህም የንግድ አውሮፕላን ሙሉ በረራ ለማድረግ የሚያበቃ ስልጠና ወሰዱ።21 ሆነው ወደ አየር መንገድ ቢላኩም በወቅቱ ዘጠኝ ብቻ ነበር የቀሩት ፡፡

ከዚህ ስልጠና በኋላ ካፒቴን ነስሩ ከማል ተመልሰው ወደ አየር ኃይል በመቀላቀል ሌላ አውሮፕላን ላይ ተመድበው ጥቂት እንደሰሩ፤ አንቶኖቭ የሚባል አውሮፕላን እንዲያበሩ ተመድበው ሦስት ዓመት ከሰሩ በኋላ ሂልኮፍተር ላይ ተመደቡ፡፡

በወቅቱ ኢትዮጵያ የራሺያ ሂልኮፕተሮችን ከውጭ አግኝታ ነበር።ቀደም ሲል የነበሩት የአሜሪካኖቹ ሂልኮፕተሮች ነበሩ።በወቅቱ ልምድ ያላቸው አብራሪዎች ወደ ራሺያ ተልከው ልምድ ቀስመው ሲመጡ ካፒቴን ነስሩ ረዳት አብራሪም ሆነው በሂደት ደግሞ ካፒቴን ሆኑ።በዚሁም አስተማሪም ሆነው ነበር፡፡

**መንግስቱ ኃይለማርያምን ሳንጉዝ...**

"በአየር ኃይል በምሰራበት ወቅት በርካታ የተከበሩ ‹‹VIP›› ሰዎችን በአውሮፕላ አጓጉዣለሁ፤ የኢትዮጵያን ፕሬዚዳንት ኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያምን ብዙ ጊዜ አጓጉዣለሁ በርካታ የጦር መኮንኖችን፣ ጀነራሎችን፣ ቱሪስቶችን ከአንዱ ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ አጓጉዣለሁ።አንድ አሜሪካዊ በየዓመቱ ቱሪስቶችን ከተለያዩ የአሜሪካ ስቴቶች ይዞ ይመጣ ነበር።እነዚህንም ወደተለያዩ ኢትዮጵያ ክፍሎች አጓጉዘዋል፤ ከሰዎችም ተዋውቄያለሁ፤ አገርም አይቻለሁ።በወቅቱ የአየር ኃይል ይህን በረራ ያከናውን የነበረው ለመተባበር እንጂ ዋና ሥራው አድርጎ አልነበረም" ይላሉ-ካፒቴን ነስሩ፡፡

**ኢህአዴግ ሲገባ...**

የደርግ ሥርዓት በኢህአዴግ ሥርዓት ሲተካ ካፒቴን ነስሩ በማዕረጋቸው ሻምበል ነበሩ።በወቅቱ በርካታ የጦር መኮንኖችንና ባለሞያዎችን ጭምር እያደኑ ያስሯቸው ነበር።ዳሩ ግን በአጋጣሚ ሆኖ ካፒቴን ነስሩ አልታሰሩም።እንዲያውም ሁለት ዓመት ሥራ ላይ ነበሩ።ምናልባትም አሁን ላይ ሆነው ሲያስቡት የሚያስመጣላቸው ሃሳብ ነው፤ ብዙው ጊዜ በትራንስፖርት አውሮፕላን አብራሪነት ስሳተፍ ስለነበርና ጦር ሜዳ ላይ ብዙም ባለመሳተፌ ኢህአዴጎች ለማሰር የፈለጉ አይመስለኝም የሚል ግምት አላቸው።ሆኖም ብዙ ጊዜ ወደ ጦር ሜዳ በማቅናት ቁስለኛ ማንሳት፣ የጦር አመራሮችን ማድረስና መመለስ፣ ስንቅ ማድረስ የሥራቸው አካል ነበር።በተጨማሪም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለባንኮች፣ ለማዕድን ሚኒስቴርና ልዩ ልዩ የሲቪል ሥራዎች፣ ለእርዳታ ሥራ፣ ዜጎችን ከጎርፍ እና መሰል አደጋዎች ዜጎችን ለመታደግ፣ ቱሪስቶችን ለማጓጓዝና ለሌሎች ተግባራትም ይበሩ ነበር፡፡

**ከአየር ኃይል ስንብት**

ኢህአዴግ እንደገባ በጣም ከሚፈልጋቸው በስተቀር የአየር ኃይል ባለሙያዎችና መኮንኖችን አላሰረም ነበር።የተወሰኑትን እያፈላለገ ወደ ሥራ እየመለሰ አየር ኃይሉን በሚፈልገው መንገድ ማደራጀት ጀመር።ካፒቴን ነስሩም ሁለት ዓመት ሰርተው ነበር።በወቅቱ በነበሩ በረራዎች የኢህአዴግ አንድ ወታደር በተለይም በመጀመሪያው አንድ ዓመት ውስጥ በእያንዳንዱ በረራ ታጥቆ አብሮ ይንቀሳቀስ ነበር፤ ጥርጣሬ ስለነበረባቸው።

ካፒቴን ነስሩም ከሁለት ዓመት በኋላ የተለያዩ ጫናዎችን ስለተፈጠረባቸው ከአየር ኃይል ለቀው ወጡ።ከዚህን በኋላ መዳረሻቸው የሆነው አድማስ የሚባልና በኢትዮጵያ አየር መንገድ ሥር የነበረ የንግድ የበረራ ድርጅት ነበር። ቀደም ብለው በኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ ሰልጥነው ስለነበር ብዙም አልተቸገሩም።የበረራ ፈቃዳቸውንም አሳድሰው ሥራ ጀመሩ።ይሁንና ከዕለታት በአንዱ ቀን ይህ ሥራ አቁም የሚል ደብዳቤ ደረሳቸው።ይህም የሆነው ከአየር ኃይል ውስጥ ጫና የፈጠሩ ሰዎች በእጅ አዙር በመምጣት ነበር።በዚህ ጊዜ ካፒቴን ነስሩ ከማል ኢትዮጵያ ውስጥ መሥራት እንደማይችሉ በመረዳታቸው ሌሎች አማራጮችን ለመመልከት ተገደዱ፡፡

**ስደት**

የፖለቲካ እና ሌሎች ተያያዥ ጫናዎችን መቋቋም ያቃታቸውና ከሥራ የተሰናበቱት ካፒቴን ነስሩ ከማል ወደ ኬንያ በጉብኝት መልክ አመሩ።በወቅቱ ቤተሰብ መስርተው ስለነበር ጫናው ቀላል አልነበረም።በእርግጥ ቀደም ብለው ኬኒያን ለመጎብኘት ሄደው ስለነበር እዚያ ያሉትን አማራጮች ለማየት ዕድሉን አግኝተዋል።በወቅቱ ኬኒያ ብዙ የግል የበረራ ካምፓኒዎችም ነበሩ።ኢትዮጵያ ውስጥ ግን አየር መንገድ እና አየር ኃይል ብቻ ስለነበሩና በሁለቱም እንዳይሰሩ ስለተከለከሉ ነበር ወደ ኬኒያ ያመሩት።በወቅቱም የበረራ ፈቃዳቸውን በኢትዮጵያ ስለነበር መስተካከል ያለበት ጉዳይ ተስተካክሎ ፈቃዳቸውን ያዙ፡፡

**ወደ ታንዛኒያ**

ኬኒያ ሁለት ወራት ከቆዩ በኋላ የተሻለ ዕድል ይኖራል ብለው ወደገመቱት ታንዛኒያ ‹‹አሩሻ›› የምትባል ከተማ አቀኑ።ኬኒያ ለጉብኝት በሄዱበት ወቅት ኤፍሬም ቡልቻ የሚባሉ ኢትዮጵያዊና የሬስቶራንት ባለቤት ጋር ድንገት ተዋውቀው ነበር።ካፒቴኑም ታሪካቸውን ለኤፍሬም አጫውተው ስለነበር እዚያው የሥራ አማራጮች እንዳሉም ጠቆሟቸው።በዚህን ጊዜ የካፒቴን ነስሩ ከማል ጓደኞች የጉብኝት ጊዜያቸውን አጠናቀው ወደየመጡበት ሲመለሱ እርሳቸው በዚያው የእንጀራቸውን መንገድ ማፈላለግ ጀመሩ።በዚህ አጋጣሚ አቶ ኤፍሬም የተባሉ ግለሰብ ለእኔ የማይረሳ ባለውታ ናቸው፤ ሁሌም ሳመሰግናቸው እኖራለሁ ይላሉ፣ ካፒቴን ነስሩ ከማል በወቅቱ የነበረውን ሁኔታ የኋሊት በትዝታ በማስታወስ።በዚህ የሥራ ማፈላለግ ውስጥ አንድ ድርጅት ፈቃደኛ ሆኖ ታንዛኒያ አሩሻ የምትባል ከተማ በሞያቸው ሥራ ቀጠራቸው፡፡

በታንዛኒያ ሥራ አግኝተው ለመሥራት ሂደቱን እንደጀመሩ በታሰበው ልክ ባለመሄዱና ባለቤቱ በሞት በመለየቱ ድርጅቱ ፈረሰ።አሁንም ሥራ ፍለጋው ቀጠለ።ከኢትዮጵያ ከወጡ ከሥምንት ወራት በኋላ በዚያው በታንዛኒያ ‹‹ሙዋንዛ›› በምትባል ከተማ ሥራ አገኙ።በወቅቱ ከውጭ ዘመዶቻቸው ያግዟቸው የነበረ ቢሆንም ጫናው ግን የዋዛ አልነበረም።የገጠሟቸውን ውጣ ውረዶች ሁሉ አልፈው የመጀመሪያ ሥራቸውን ጀምረው ደመወዝ ወሰዱ፤ ወዲያውም ቤተሰቦቻቸውን ከአዲስ አበባ ወደ ታንዛኒያ አመጡ።በወቅቱ ደመወዙም ቤተሰብ ለማስተዳደር በቂ እንደነበርም ያስታውሳሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ ሥራ ሲጀምሩም ሆነ ወደ ሥደት ሲያመሩ ደመወዙ ብዙም ማራኪ እንዳልነበረም ያስታውሳሉ፡፡

አሁን ግን ኑሮን ለመምራት መንገዱ ቀና እየሆነላቸው መጣ። በሥራቸውም ላይ ሆነው ብዙ ዓይነት አውሮፕላኖችን መብረር ጀመሩ።ለረጅም ዓመትም ድርጅቱን ሳይቀይሩ ሠሩ፤ ልምድ ቀሰሙ፤ ሥም አፈሩ። ይሰሩበት የነበረው ድርጅት ትንንሽ የጉብኝት አውሮፕላኖች ነበሩት። በአንድ ቀን ሦስት የተለያዩ አውሮፕላኖችን የሚበሩበት አጋጣሚዎች ስለነበር በዕድሜም ገና በሠላሳዎቹ መጀመሪያ ስለነበሩ በትጋትና ያለመታከት ይሠሩ ነበር።

አራት ዓመት ከሰሩ በኋላ፤ በታንዛኒያ በሚገኝና የምስራቅ አፍሪካ አገራት አባል የሆኑበት የበረሃ አንበጣ መከላከያ ትራንስፖርት ሴክተር ላይ ገቡ።ይህ ድርጅት ለትራንስፖርት የሚሆን አንድ አውሮፕላን ገዝቶ ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት ይበር ነበር።ካፒቴን ነስሩ ከማል በዚህ አውሮፕላን ላይም ሰርተዋል፡፡

አውሮፕላን የመግዛት ፍላጎት

ካፒቴን ነስሩ ከማል በሂደት ገንዘብ እየሰሩ በፈረንጆቹ አቆጣጣር 2008 አነስተኛ አውሮፕላን ገዙ።በእርግጥ ይህ ህልማቸው ገና ልጅ ሆነው ስደትን ሳያስቡት፤ ኢትዮጵያ ውስጥ እያሉ ነበር።ለዚህም እንደመነሻ የሆናቸው ሙሳ የሚባል ጅቡቲ ውስጥ የግል አውሮፕላን ሥራ የጀመረ ሰው ነበር።ሌላኛው ካፒቴን አስራት የሚባሉና በኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ እየሰሩ በግል አውሮፕላን ገዝተው ስራ ጀምረው ስለነበር እነዚህ ግለሰቦች ለካፒቴን ነስሩ ሥራ እንደ ዓይን ገላጭ አድርገው ሳሏቸው፡፡

አውሮፕላን ካምፓኒ ለመክፈት ምን ማድረግ አለብኝ፤ መስፈርቶቹስ ምንድን ናቸው? ሲሉ በወቅቱ የነበሩትን የኢትዮጵያ ጀነራል ዋና ኦዲተር አቶ ለማ አርጋው ጠየቁ።ከእርሳቸውም ጥሩ መረጃን አገኙ።ወደ አቬሽን መስሪያ ቤትም ሄደው

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

መረጃ ሰበሰቡ።ዳሩ ግን ገንዘብ ስላልነበራቸውና ሐሳባቸውን የሚጋራ ባለሃብት በመጥፋቱ በወቅቱ ሥራውን አልጀመሩም፡፡

ይህ ሁሉ ሳይሆን ቀርቶ በስደት ዓለም ለመኖር ተገደዱ።ታዲያ በስደት ታንዛኒያ እያሉም አንድ በደንብ ይተዋወቁት የነበረ ህንዳዊ ካፒቴን ለምን አውሮፕላን አንገዛም? ብሎ ያማክራቸዋል።እርሳቸው በወቅቱ ለአውሮፕላን መግዣ ገንዘብ ስለሌላቸው "በጭራሽ አልችልም ገንዘብ የለኝም" ይሉታል።በዚህን ጊዜ እኔ አለሁ ለገንዘቡ ብሎ አግባባቸው።ታዲያ በመጨረሻ ተግባብተው አራት ሰው የምትይዝ አውሮፕላን ገዙ፤ 35 በመቶ ድርሻም የካፒቴን ነስሩ ሆነ።ይህ ሁሉ ሲሆን ለአለቃቸው አልተናገሩም ነበር፡፡

ዳሩ ግን በታንዛኒያ ህግ መሰረት የአውሮፕላን ኦፕሬተር ፈቃድ ሲወጣ በግልጽ መታወቅ ስላለበት፤ ጉዳዩ የአውሮፕላን ኦፕሬተር ፈቃድ ቦርድ ላይ ቀረበ።በዚህን ጊዜ አለቃቸው የነበረ ሰው ከስብሰባው መልስ ወደ ካፒቴን ነስሩ ከማል በመሄድ እንዴት እንዲህ ታደርገኛለህ? ብሎ አፈጠጠባቸው።በዚህን ጊዜ ሁለት አማራጭ ሰጣቸው።አንደኛው ጠቅልለህ የአውሮፕላን ኦፕሬተር ፈቃድ አውጥተህ ትሰራለህ፤ ወይስ ከእኔ ድርጅት ጋር ትቀጥላለህ ሲል ጠየቃቸው።ታዲያ የቤተሰብ አስተዳዳሪ ስለነበሩና የሚቋቋመው ድርጅት አስተማማኝነቱ የተረጋገጠ ባለመሆኑ ካፒቴን ነስሩ ከማል የአውሮፕላን ኦፕሬተር ፈቃድ ትቻለሁ ብለው የቀድሞ ሥራቸውን ቀጠሉ፡፡

ከዕለታት በአንዱ ቀን ገና በታንዛኒያ አንድ ብለው ሥራ የጀመሩበት ድርጅት አውሮፕላን እንደሚሸጥ ሰሙ። ሰዎችን አማከሩ በርታ አሏቸው፤ ጨረታውን ቢሞክሩትም አልተሳካም።ግን አሁንም ልባቸው አውሮፕላን መግዛት ላይ ነው።ሌላ ጨረታ ሞከሩና አሸነፉ።ዳሩ ግን አብረን እንሰራለን በርታ ሲሉ የነበሩ ካፒቴኖች ሸርተት አሉ።ካፒቴን ነስሩ ደግሞ ብዙ ስለተጓዙና ገንዘብም በብዙ ስላወጡ ወደ ኋላ መመለስ የማይችሉበት ደረጃ ደረሱ።113ሺ ዶላር አውጥተው ከአብራሪው ጋር ስድስት ሰዎችን የምትይዝ አውሮፕላን የራሳቸው አደረጓት።

እርሳቸው እዚያው የበረሃ አንበጣ መከላከል ውስጥ እየሰሩ፤ አንድ ሲውድናዊ አብራሪ ቀጥረው መሥራት ጀመሩ።በሂደት ግን የበረሃ አንበጣ መከላከል ውስጥ ያሉ ሰዎችም ልክ እንደ ቀድሞ ድርጅት ወይ እኛን ወይንም የግል ስራህን ምረጥ የሚል ሐሳብ ቀረበላቸው።የጥቅም ግጭት አለው የሚልም አንዱ ምክንያት ነበር። ካፒቴን ነስሩ ከማል የሚሰሩትና የተባለው አይጋጭም ነበር።ዋናው ነገር ለምን አደገ የሚል የቅናት መንፈስ ነበር።በዚህን ጊዜ ካፒቴን ነስሩ ወሰኑ፤ የራሴ ሥራ ይሻለኛል ብለው በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ 2009 ወደ ራሳቸው ሥራ ጠቅልለው ገቡ ።

**ወደ ሱዳን**

ታንዛኒያ እየሰሩ ሳለ ደቡብ ሱዳን ጥሩ የገበያ ዕድል መኖሩን በሰሙ ጊዜ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2014 14 ሰው የሚይዝ ከራቫን የሚባል አውሮፕላን በሊዝ ግዥ በ 1 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዶላር ገዝተው ደቡብ ሱዳን ገቡ።በአሁኑ ወቅትም ድርጅታቸው በዚያው እየሰራ ነው፡፡

ታዲያ አሁን ላይ የደረሱበትን ሁኔታ የኋሊት ሲመለከቱ፤ "እውነቱን ለመናገር የሚያስደስተኝ ያፈራሁት ንብረት ሳይሆን ተገፍቼ ወጥቼ ጎዳና ላይ ይወድቃል ጫማው አልቆ፣ ሸሚዙ ተጨማዶ፣ ውስጡ ነዶ መንገድ ላይ እናገኘዋለን ብለው ሲያስቡኝ በሃሳባቸው ተስፋ ይቆርጣል ብለው ሲመኙ በፈጣሪ እርዳታ እዚህ መድረሴ ነው።በወቅቱ በጣም ተከፍቼ ነበር።ከዚያ ወጥቼ እዚህ መድረሴ ትልቅ ነው።ኔልሰን ማንዴላ ያሉት አባባል አለ።‹የሚያስደስተኝ ያገኘሁት ስኬት ሳይሆን ስንቴ ወድቄ ስንቴ እንደተነሳሁ ነው› "ይላሉ፡፡

የበረሃ አንበጣ መከላከል ላይ እየሰራሁ ሳለም ብዙ በድለውኛል የሚሉት ካፒቴን ነስሩ ግን ሁሉም ነገር ለበጎ ነውና አልፌዋለሁ ባይ ናቸው፡፡

"አሁን በወቅቱ እነሱ ቀጥረውኝ ሳበራቸው የነበሩት ዓይነት ሦስት አውሮፕላኖች አሉኝ።ሁለቱ እየሰሩ ነው።በቀጣይ ሁለት ተጨማሪ የመግዛት እቅድ አለኝ።በደቡብ ሱዳን ውስጥም በፋይናንስ ስም በደንበኛም ጥሩ እየሄድኩ ነው" ይላሉ፡፡

**የኢትዮጵያ አየር መንገድ ውለታ**

"እውነቱን ለመናገር አየር መንገዳችን በጣም



የምንኮራበት ነው።ለእኔም እዚህ መድረስ ተጠቃሽ ባለ ውለታ ነው፡ አየር መንገድ ያገኘነው ዲፕሎማ በጣም ዋጋ ያለው በመሆኑ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ውስጥ ነው የሰለጠንኩት ብዬ ስናገር ኦ! በጣም አሪፍ ነው ብለው ያደንቁታል።አየር መንገዳችን ጥሩ ሥም ስላለው እዚያ መሰልጠኔ ለእኔ ረድቶኛል።በዚህ አጋጣሚ አየር መንገዱን አመሰግናለሁ፤ በጣምም እኮራበታለሁ "ይላሉ፣

ኢትዮጵያ በአቬሽን ጎልታ የወጣችበትና ቀዳሚ ከሚባሉ አየር መንገዶችም አንዱ የሆነችበት አፍሪካኖቹ በቀኝ ግዛት ውስጥ ሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሥራ ላይ የነበረና በጣም ዝነኛ ነበር።ያኔ! እኔም በአየር መንገዱ ውስጥ ስሰለጥን አውሮፕላን ለማስጠገን ከብዙ አገር ወደ ኢትዮጵያ ይመጡ ነበር።ከደቡብ አፍሪካ ካለው የአፓርታይድ ሥርዓት ጋር በተያያዘ ከተጣለው ክልከላ ውጭ በርካቶች ወደ ኢትዮጵያ መጥተዋል።ለምሳሌ የግብጽ፣ የመን ሌሎችም የአፍሪካ አገራት አውሮፕላኖች ለጥገና ኢትዮጵያ ይመጡ ነበር ።ፓይለቶችም ለስልጠና ከተለያዩ አገራት ወደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ መጥተዋል በማለት የነበረውን ሁኔታ ያስታውሳሉ።

**አገራችን ያለው ዕድል**

ታንዛኒያ ውስጥ ብንሄድ ለሌላ አገር ዜጋ ምቹ አይደለም።ከኢትዮጵያ ፓይለት ጨምሮ ብዙ ባለሙያ መውሰድ እፈልግ ነበር፤ ግን ህጋቸው በጣም ጥብቅ ነው።እኔ አሁን እዚያ ቢሮ አለኝ።ወደ ደቡብ ሱዳን የሄድኩትም የስራ አማራጭ ፍለጋ ነው።

እኛ አገር ለቱሪስቶች ምቹ ሁኔታ ካመቻቸን ትልቅ ገቢ ይኖረናል ።አየር መንገዳችን አዳዲስ አሰራር ቢዘረጋ መልካም ነው።ለምሳሌ ወደ ባሌ በረራ በቀን አንድ ጊዜ ከሆነ ከዚህ ሰዓት ውጭ የሚመጣ ቱሪስት ማስተናገድ አይቻልም ስለዚህ ትንንሽ ካምፓኒዎች ዕድሉ ቢሰጣቸው በተፈለገው ሰዓትና ቦታ ሌላው ቀርቶ መንደር ውስጥ ገብተን እንሠራለን፡፡

የማዕድን አካባቢ ሥራዎች አንድ ማሽን ቢበላሽ ወይንም ተለዋጭ ዕቃ ቢፈልጉ ትልልቅ አውሮፕላኖች በዚያ ስፍራ አያርፉም። ለአርኮሎጂስቶች፣ ኢን ቨስተሮች፣ ለውጭ ጉዞ አስቸኳይ ህክምና፣ ጎብኚዎች ለማንቀሳቀስና ለመሳሰሉት አመቺ ሁኔታ መዘርጋት ያስፈልጋል። ትልልቅ ፕሮጀክቶችን መጎብኘት ቢያስፈልግ መሰል በረራዎች አስፈላጊ ናቸው። ስለዚህ ትንንሽ አውሮፕላኖችን ዕድል ሊሰጣቸው ይገባል። ይህ ቢሰራበት ለአገሪቱ ትልቅ ጥቅም ያመጣል። ታንዛኒያ እያለሁ ለቱሪዝም፣ ለማዕድን ሥራዎች፣ ትልልቅ ፕሮጀክቶች ስበር ነበር።በጣም አዋጭና አገርን የሚጠቅም በመሆኑ በእኛ አገርም ቢጀመር ለኢትዮጵያ አየር መንገድም ሆነ አገሪቱ ኢንቨስትመንት ትልቅ አቅም ይፈጥራል።

**እኔም ለአገሬ**

ከአገሬ ተገፍቼ ወደ አገሬ የተመለስኩት ‹‹ዞሮ ዞሮ ከቤት፤ ኖሮ ኖሮ ከሞት›› አይቀርምና እትብቴ ወደተቀበረባት ኢትዮጵያ ተመልሻለሁ።በመሆኑም በአገር ውስጥ ለመሥራት ‹‹ኤር ኤክስፐረስ አፍሪካ›› (Air Express Africa›) በሚል ድርጅት ፈቃድ አውጥቼ በሙያዬ ተሰማርቻለሁ።ህጋዊ ሂደቶችንና መስፈርቶችን አልፌ ፈቃድ አውጥቼ ሰዎችንም እየቀጠርኩ ነው።

"እንደ ድርጅት ብዙ መሥራት አለብን ብለን ነው የተነሳነው። ቱሪዝም ላይ መሥራት ያስፈልጋል።የጸረ ተባይ መድሃኒት በአውሮፕላን ለመርጨት እናስባለን፤ ግን አርሶ አደሩን ማላመድ ያለብን ነገር ደግሞ አለ። ትልልቅ ባለሃብቶች፣ በጣም የተከበሩ ሰዎችንና ሥራ ኃላፊዎችን ለማጓጓዝ የምንሠራ መሆናችንን ማሳወቅ እንፈልጋለን። በዘርፉ ላይም የአብራሪ (ፓይለት) ማሰልጠኛ ላይ እንሰራለን።አፋጣኝ የውጭና በአገር ውስጥ መታከም የሚፈልጉ አገልግሎት መስጠት፣ የአውሮፕላን ካርጎ አገልግሎት፣ ወደ ውጭ ምርት ለሚልኩ ነጋዴዎች አገልግሎት እንሰጣለን። በአጠቃላይ የግብርና፣ ንግድ፣ ቱሪዝም፣ ማዕድን፣ ሕክምና ዘርፍ ለመደገፍ ነው የምንቀሳቀሰው። በይበልጥ ደግሞ ማዕድንና ቱሪዝም ላይ በመሰማራት የአገሪቱን ልማት የማገዝ ፍላጎትና ምኞት አለን" ይላሉ፡፡

በዚህ ሁሉ ስራ ውስጥ መግባታችን ግን የኢትዮጵያን አየር መንገድ ጥቅም በሚፃረር መልኩ ሳይሆን ሥራዎችን በመደገፍ ነውም ይላሉ፡፡

**ቤተሰብ፣ ትምህርትና፣ እውቅና**

ካፒቴን ነስሩ ከማል አራት ልጆችን አፍርተዋል።ልጆቹ እንደ አባታቸው ታታሪና ሥራ ወዳድ ናቸው። በሥራ ይተጋገዛሉ፤ በትምህርታ ቸውም ስኬታማ የሚባሉ ናቸው።እርሳቸው ያለፉበትን ውጣ ውረድ እንደ ምሳሌ እያነሱ ያስተ ምሯቸዋል፤ ለቤተሰቦቻቸው የጥንካሬ መሠረት እንዲሆናቸው፤ በፈተና ውስጥ ማለፍና ለስኬት መብቃት እንደሚቻል የእርሳቸው ህይወት ምሳሌ እንዲሆናቸው፤ በአጋጣሚዎች ሁሉ ያወጓቸዋል። ለስኬታቸውም የቤተሰባቸው ድጋፍ ትልቁን ድርሻ እንደሚወስድም ይናገራሉ፡፡

በእርግጥ ህይወት ወደ ብዙ መንገድ ብትወ ስዳቸውም እርሳቸውም በትምህርታቸው የዋዛ ሰው አይደሉም። ከኢትዮጵያ አየር መንገድ በዲፕሎማ፣ ከአሜሪካ አገር በበረራ ደህንነት ሰርተፍኬት፣ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን ድግሪያ ቸውን ከታንዛኒያ አግኝተዋል።መስፈርቶች በሙሉ አሟልተው በመገኘታቸው ከኢትዮጵያ፣ ኬኒያ እና ታንዛኒያ የንግድ አውሮፕላን ፈቃድ አግኝተዋል። በአገር ውስጥ ደግሞ በጉራጌ ማህበረሰብ ውስጥ ለማህበረሰቡ በጎ የሰሩ፣ በብዙ ውጣ ውረዶች ውስጥ አልፈው ወደ ስኬት የመጡ ሰው በመሆናቸው በየዓመቱ በሚሰጠው ‹‹ኬር አዋርድ›› ላይ ምስጋና እውቅና ተችረዋል፡፡

**መልዕክት አለኝ**

በኢትዮጵያ ውስጥ የግል ቻርተር አውሮፕላኖች አለመስፋፋት ጎድቶናል።በቅርቡ ፈቃድ ስወስድ እኔ 12ኛ ሰው ነኝ።ወደ ሌላ አገር ስንሄድ የምንመለከተው የአገራችንን ቱሪዝም አለመጠቀማችንን እንረዳለን፡፡

ለባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሆነ ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት አጋጣሚውን አግኝቼ መናገር የምፈልገው፤ በጣም! በጣም! መሥራት ይጠበቅብናል የሚለውን ነው። ኬኒያና ታንዛኒያ ትልቁ ገቢያቸው ቱሪዝም ነው። ቱሪዝም ትልቅ አቅም አለው። በመሠረተ ልማትም ብዙ ይቀረናል። ሆቴሎች፣ ቴክኖሎጂ፣ ኤርፖርቶች በበቂ ሁኔታ አለመገንባታቸው፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖር እና ሌሎች መሠረተ ልማቶች አለመሟላት ጎድቶናል፡፡

አውሮፕላኖች በብዛት ማረፊያቸው አዲስ አበባ ነው። ትንንሽ ኦፕሬተሮች በትራፊክ መጨናነቅ ምክንያት በሚገባ እየሰሩ አይደለም ብየ አስባለሁ። ስለዚህ እነዚህ ትንንሽ አቅም ያላቸው የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በሌላ ቦታ ቢስተናገዱ ለአገርም ለባለሃብቱም ይጠቅማል። የደህንነት ሁኔታውንም ለማስጠበቅ መንግስት አሰራርና ፖሊሲዎችን መቅረጽ ይችላል። ኬኒያ ውስጥ ይህ ተሞክሮ አለ።በመሆኑም ለአነስተኛ አውሮፕላኖች ራሱን የቻለ ኤርፖርት ያስፈልጋል። በአውሮፕላኖች የሚጠገኑበትንም ‹‹ሃንጋር›› ያስፈ ልገናል። በአሁኑ ወቅት ትንንሽ ብልሽቶች ሲገጥሙን ከአገር ውጭ እየሄድን ነው ከፍተኛ ወጪ በማውጣት የምናሰራው።

መንግስት በአሁኑ ወቅት ለጉዳዩ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ የኢትዮጵያ አየር መንገድና አየር ኃይል ቅጥር ግቢ የሚገኘውን ደጀን አቬሽን ለግል አውሮፕላን ኩባንያዎች የጥገና አገልግሎት እንዲሰጡ በመፍቀዱ ወደፊት ይህ ችግር ይቃለላል የሚል ተስፋ አለኝ። በዚህም መንገድ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሊያግዘን እየሞከረ ቢሆንም በብዙ ሥራ ስለሚጠመድና በተለያዩ ምክንያቶች ያን ያህል አጥጋቢ ይሆናል የሚል ግምት የለኝም። በእኔ እይታ ደጀን አቬሽን ከሚመለከተውና ከሲቪል አቬሽን ለግል አውሮፕላን ጥገና የሚያበቁዋቸውን ፈቃድ ካገኙ አመርቂ ሥራ ይሰራል የሚል ዕምነት አለኝ።

‹‹በድርጅቴ ኤር አፍሪካ ኤክስፐረስ ውስጥ ያሉ አምስት የቴክኒክ ባለሙያዎች ወደ ደጀን አቬሽን ሄደው ያመጡልኝ ሪፖርት የሚያሳየው በጣም ተስፋ የሚጣልበት ተቋም በመሆኑ ከእነርሱ ጋር ለመሥራት እያቀድን ነው።ሌሎች ኩባንያዎችም ዕድሉን ቢጠቀሙ እመክራሉ›› ሲሉ በኢትዮጵያ ያለውን መፃዒ ተስፋ ይጠቁማሉ፡፡

ሌላው ችግር በአገሪቱ ውስጥ በቂ የአየር ማረፊያ አለመኖሩ ሲሆን ይህንን በመገንዘብ ሲቪል አቬሽን ባለስልጣን የግል አውሮፕላን ባለቤት ሆነ ማንኛውም ባለሃብት አየር ማረፊያ የመገንባት ፍላጎትና አቅሙ ካለው ፈቃድ ለመስጠት ፈቃደኝነቱን በማሳየቱ በጫካውና በቱሪስቶች መዳረሻ ሎጅ መሥራት አለብን።ቱሪስቶች አካባቢዎችን ቀን፣ ማታ፣ ሌሊት፣ ማለዳ እየተነሱ አካባቢውን መቃኘት ይፈልጋሉ። ለምሳሌ ጥዋት ብቻ የሚታዩ ወፎች ሊኖሩ ይችላሉ። በአገራችን ህጋዊ አደን የሚፈቀድ ከሆነም ይህን ሥራ መሥራት ይገባል፡፡

ታንዛኒያና ኬኒያን የመሳሰሉት አገራት ብንሄድ ብዙ ነገሮች ከእኛ የተሻሉና የተደራጀ ዘመናዊ አሰራር ዘርግተዋል።በአገራችን የሰሜኑ ጦርነት ከመጀመሩ በፊት ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ የአገሪቱ የቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎች ከቤተሰቤ ጋር ተጉዘን ነበር።አሁን ጥሩ ነገሮች አሉ፤ ቢሆንም ግን ብዙ ሥራ መሥራት ይገባል ።ጎብኚዎች ወደ አገር ውስጥ እንዲመጡ ሠላምና መረጋጋት መፈጠር አለበት። መሰረተ ልማቶችንም በተቻለ መጠን ማሟላት ያስፈልጋል፡፡

# ባህልና ቱሪዝም

# አምበርቾ ተራራ - አዲሱ የቱሪስት መስህብ

ኃይሉ ሣህለድንግል

ከሁለት ዓመት በፊት የዞኑ አስተዳደር፣ ምክር ቤት፣ ህዝብና ምሁራን በአካባቢው ያለውን እምቅ ሀብት አሟጦ መጠቀምና በራስ አቅም የመቆም እልህ አደረባቸው።ከክልሉ መንግስት በሚመደብ በጀት ብቻ የመንቀሳቀስ ጉዳይ፣ ተጨማሪ የኢኮኖሚ ምንጭ አለማማተር፣ የስራ አጥ ቁጥር በከፍተኛ መጠን እየጨመረ መምጣት በእጅጉ አሳሰባቸው።

እነዚህ የደቡብ ብሄሮች ብሄረተሰቦችና ህዝቦች ክልል የከንባታና ጠንባሮ ዞን አስተዳደር፣ ምክር ቤት፣ ህዝብና ምሁራን ኢኮኖሚው ከለመደው መንገድ ውጪ ገቢ በሌላ መንገድም መምጣት አለበት የሚል ሀሳብ ማመንጨት ጀመሩ።ለእዚህም በዞኑ የሚገኘውን አንድ ትልቅ ታሪካዊ ተራራ ማልማት አሰቡ፤ ይህን 18ሺ ሄክታር የሚሸፍን ተራራ አልምተን የተሟላ የቱሪስት መዳረሻ ብናደርግ በውስጡ ሊፈጠር የሚችለው የቢዝነስ ሰንሰለት ትልቅ ሊሆን ይችላል የሚል እምነት አደረባቸው። ለልማቱ የታጨው ተራራም ከከንባታና ጠንባሮ ዞን መቀመጫ ዱራሜ ከተማ ስምንት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው አምበርቾ ተራራ ሆነ፡፡

ይህ ልማት የተወጠነበት ወቅት 2012 ዓ.ም የኮረና ወረርሽኝ በዓለም አቀፍና በአገር ደረጃ ትልቅ ስጋት የሆነበት ነበር፤ ኮረና ስጋት ቢሆንም ዞኑ ለያዘው እቅድ ግን መልካም አጋጣሚ ሆኖ መገኘቱን በከንባታ ጠንባሮ ዞን አስተዳደር፣ ባህልና ቱሪዝም ትብብር የሚለማው የአምበርቾ ተራራ ኤኮቱሪዝም ስፍራና አረንጓዴ ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ስራ አስኪያጅ አቶ ዘመዴ ሄራሞ ይገልጻሉ።

አቶ ዘመዴ እንደተናገሩት፤ ዞኑ እጅግ በርካታ ምሁራን የወጡበት ነው፤ ኮሮናውን ተከትሎ በርካታ የዞኑ ምሁራን ወደ ዞኑ ይመጡ ነበር፤ 42 ዶክተሮችና ፕሮፌሰሮች ወዶ በዞኑ ተገኝተው የዞኑን እምቅ አቅም ለማጥናት በአካባቢው ለሶስት ወራት ቆይተዋል፤ በወቅቱም ወደ 200 ገጽ ያለው አንድ እናት ሰነድ ተዘጋጀ።


ሀሳቡ ሲጠነሰስ በመጀመሪያውም አምበርቾን ወደ ቀደመው ማንነቱ መመለስ አለብን የሚል አቋም ተይዞ፤ ተራራው የምንጮች፣ የወንዞች፣ የፏፏቴዎች ተራራ መሆን አለበት፤ ስለዚህ ባህር ዛፎችንና ሌሎች ጎጂ ነገሮችን እያስወገድን ውሃ የሚያፈልቁትን ማበረታት አለብን የሚል ሀሳብ መጣ። ሁለተኛው ደግሞ ተራራው የቀደምት የከምባታ ህዝቦች መጥተው የኖሩበት የመጀመሪያው ተራራ እንደመሆኑ መጠን ይህን ታሪኩንና ባህሉን፣ ቅርሱን በዚህ ላይ በመጨመር ጎብኚዎችን ይበልጥ መሳብ ይቻላል በሚል ታሳቢም ወደ ማልማቱ መገባቱን አቶ ዘመዴ ያብራራሉ፡፡

የደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም ገበያ ባለሙያ አቶ ኢያሱ ሰለሞን በቱሪዝም ዘርፍ ላይ ለ18 ዓመታት ሰርተዋል።የአምበርቾ ተራራ ደረጃ ሲሰራ ጀምሮ ያውቁታል፤ የዞኑ አስተዳደርና ምክር ቤት እንዲሁም የዞኑ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ በመጀመሪያ ደረጃ ይህን ጉዳይ ለማሰራትና አጠቃላይ የዚህን አካባቢ የኢኮኖሚ ትስስር ከመፍጠር አንጻር ቱሪዝም አንዱ የመልማት እድል እንደሆነ ሲያስቡ ምን እናድርግ የሚል አጠቃላይ የምክክር መድረክ ማድረጋቸውን ያስታውሳሉ።እሳቸውም በምክክር መድረኩም ተሳትፈዋል።ከዚያም በአገር ውስጥም በውጪም ያሉ የዞኑ ምሁራን ተሰባስበው ይህ ጅምር ካለ እንዴት አርገን አስተሳስረን የሕዝቡን የኢኮኖሚ የመልማት የዞኑን ማህበራዊ ችግር የምንፈታው የሚል ትልቅ ፕሮፋይል ሰነድ አዘጋጅተዋል፤ ይህን ሰነድ መነሻ በማድረግ ነው ወደ ስራ የተገባው።

ይህን ሁሉ ተከትሎ በተከናወኑ ተግባሮች በዚህ ተራራ ላይ 777 ደረጃዎች ተገንብተዋል።እንደ አቶ ዘመዴ ገለጻ፤ ተራራውም የ777 ደረጃዎች ተራራ በመባልም መጠራት ጀምሯል፤ የደረጃዎቹ ብዛት ሲሰላም ከዓለም ሁለተኛ ከአፍሪካ አንደኛት በመባልም እየተጠራ ነው፡፡

እነዚህን 777 ደረጃዎች ለመገንባት አራት ነጥብ ሁለት ሚሊየን ብር ወጪ ተደርጓል።ይህን ስራ የግል ተቀቋራጭ በ50 ሚሊየን ብር አይሰራውም ያሉት አቶ ዘመዴ፣ አንድ ሺ ወጣቶች፣ የዞኑ ምሁራን ኢንጂነሮች፣ አስተባባሪዎች ተሳትፈውበት መገንባቱን ተናግረዋል።

አቶ ኢያሱም ወደ ስራ ሲገባ የደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቴክኒክ ድጋፍ ሲያደርግ መቆየቱን ጠቅሰው፣ በገንዘብ ደረጃ የዞኑ አስተዳደር የዞኑን ህዝብ አስተባብሮ ሰራተኞች ከደሞዛቸው ቀንሰው፣ ማህበረሰቡ በጉልበቱ በገንዘቡ ማቴሪያል በማቅረብ በማህበረሰቡ የደቦ ስርአት በመቀባበል የአምበርቾ ተራራ ፕሮጀክት መገንባቱን አረጋግጠዋል።





የአምበርቾ ተራራ 777 ደረጃዎች ተገንብተዋል

ፕሮጀክቱ የፌዴራል መንግስትም ይሁን የሌሎች ለጋሽ ድርጅቶች ፋይናንስ ድጋፍ አልተደረገለትም ይላሉ፤ አሁን የህግ ማእቀፍ ተዘጋጅቶለታል፤ የዞኑ አስተዳደር በጀት ይመድባል፤ ከዚህ በተጨማሪ ከህዝብ የሚሰበሰብ ገንዘብ ይኖራል፤ ከቱሪዝም የሚሰበሰብ ገንዘብ ይኖራል ሲሉ ስራ አስኪያጁ ይገልጻሉ።

ስራ አስኪያጁ እንዳሉት፤ ከተራራው ግርጌ ያለው ሜዳማ ስፍራ ከባህር ወለል በላይ 2ሺ 600 ሜትር ከፍታ ላይ የሚገኝ ሲሆን፣ የተራራው አናት ደግሞ ከባህር ወለል በላይ ሶስት ሺ 58 ላይ ይገኛል።በዚህ ከፍታ ላይ መሆኑ እጅግ ቀዝቃዛ ያደርገዋል ተብሎ ቢታሰብም የሚቀዘቅዝ አይደለም፤ ጉም ይመጣል ይሄዳል እንጂ ያን ያህል ቀዝቀዛ የሚባል ቦታ አይደለም።ኢትዮጵያውያን በእዚህ አይነቱ ውብ ስፍራ ላይ ሆነው የሚደሰቱበት ስፍራ ነው።የአካባቢው ማህበረሰብም እንግዳን የማክበር ባህል ያለው ሲሆን፣ ጎብኚዎችም በፈረስ፣ በመኪና፣ ወዘተ. ሆነው ሊጎበኙት የሚችሉበት ስፍራ ነው፡፡

ቦታው ማራኪ እና በተፈጥሮ ሀብቱ የታደለ ነው፤ ተራራው ላይ 777 ደረጃዎች ሲገነቡለትም በርካታ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና ታሪካዊ መልእክቶችን ታሳቢ ተደርገዋል።ጥንት በዚህ ቦታ ላይ የከንባታ ህዝብ ሲመጣ ሰባት ጎሳዎች ነበሩት፤ የተራራው ላይ ደረጃ አንዱ ሰባት የእነሱን ውክልና ይይዛል፤ ደረጃዎቹ በአምበርቾ ተራራ ላይ ቢገነቡም ተራራው አናት ላይ ሲደርስ ሌሎች ስድስት ተራራዎች ይታያሉ።አምበሪቾን ጨምሮ አካባቢው ላይ ሰባት የተለያዩ ተራራዎች ይገኛሉ።ሁለተኛው ሰባት እነዚህን ሰባት ተራራዎች ይወክላል።ሶስተኛው ሰባት ደግሞ ከተራራው ላይ ፈልቀው ቁልቁል የሚወርዱ በከንባትኛ ‹‹ሰመለ ሊጋ›› ተብለው የሚጠሩትን ወይም ሰባት ምንጮችን እንዲወክል ተደርጓል።

ስራ አስኪያጁ እንዳሉት፤ ‹‹አምበርቾ›› የሚለው ቃል የሁለት ቃላት ውህድ ነው።አንደኛው ‹‹አምባ›› የሚለው ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ‹‹አሪቾ›› የሚለው ነው።በከንባትኛ ‹‹አሪቾ›› ማለት ጸሀይ ማለት ነው፤ አምባ ደግሞ መገኛ ወይም ቦታ ማለት ነው።ስለዚህ አንድ ሰው ተራራው አናት ላይ ከወጣ በምስራቅም ይሁን በምእራብ ጸሀይን ማየት ይችላል።አምበሪቾ ላይ የተገኘ ሰው ጸሀይ ስትወጣም ስትጠልቅም ማግኘት ይችላል፤ በከንባትኛ አምበሪቾ ማለት ‹‹አሪቾ አምባ›› ወይም ‹‹የጸሀይ መገኛ›› ማለት ነው ሲሉ አቶ ዘመዴ ያብራራሉ።

ቀደምት የከንባታ ህዝቦች መጀመሪያ የመጡትና የኖሩት እዚህ ተራራ ላይ እንደመሆኑ ባህላዊ፣ ሃይማኖታና ታሪካዊ ቅርሶችና ኩነቶች ነበሯቸው፤ ንጉሶቻቸውን ሾመውበታል፤ ለንጉሶቻቸው ተገዝተው ኖረዋል፤ የሚያስፈልጋቸውን ግብር ከፍለዋል፤ ጥሩ የሰራ ተሸልሞበታል፤ ወንጀለኛ ተቀጥቶበታል፤ ንጉስ ተቀያይሮበታል፤ ስለዚህ አካባቢው የንጉስ ሹመት ስርዓት አለበት።ከዚህም ታሪካዊ ፋይዳዎች እንዳሉት መረዳት ይቻላል፡፡

ተራራው ሌሎች በርካታ ሀብቶችም አሉት፤ ሰው ያልተከለው 200 ሄክታር የሚጠጋ ጥብቅ የተጥሮ የቀርከሃ ደን፣ በውስጡም አቦ ሸማኔና ሌሎች የዱር እንስሳት አሉት፤ ከ350 የሚበልጡ ለመዳህኒትነት ሊውሉ የሚችሉ እጽዋት ያለበትም ነው፤ ዋሻዎች፣ ሜዳዎች፣ ወዘተ እንዳሉት ያብራራሉ።

በአምበርቾ ተራራ ላይ እስከ አሁን የተከናወነው ልማት የተራራው ልማት የመጀመሪያ ምእራፍ ነው።ተራራው ሰባት ዋና ዋና ተራሮችን የያዘም ነው።ሌሎቹን ተራራዎች መመልከት የሚቻለው ተራራው አናት ላይ ሲደረስ መሆኑን ስራ አስኪያጁ ይጠቁማሉ።

በቀጣይ ሌሎች በርካታ ፕሮጀክቶች መቀረጻ ቸውንም አቶ ዘመዴ ይጠቁማሉ። እያንዳንዳ ቸው ከ10 እስከ 20 ሚሊየን ብር በላይ የሚያንቀሳቅሱ ከሶስት በላይ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በዚህ ዓመት በአካባቢው ስራቸውን እንደሚጀምሩም ጠቅሰው፣ ለአብነትም የቼክ ሪፐብሊክ በአረንጓዴ ልማት፤ አይአርአር የተባለ ድርጅትም እንዲሁ ፕሮፖዛል ማቅረባቸውን ይገልጻሉ፡፡

በተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩ የከንባታ ምሁራን እንዳሉ ጠቅሰው፣ በዚህም በዓለም አቀፍ ደረጃ ፕሮፖዛል ማቅረብ የሚያስችል አቅም እንዳለም አመልክተዋል።ይህን ሁሉ ተከትሎም የአምበሪቾ ተራራ የተሟላ አስፈላጊ ነገሮችን የያዘ የቱሪስት መስህብ ይሆናል ብለን እንጠብቃለን ይላሉ።

በመስህብ ስፍራው መንገድ፣ መብራት፣ ሻይ ቡና የሚጠጣባቸውና ሰዎች የሚዝናኑባቸው ቦታዎች እንደሚያስፈልጉም ተናግረው፣ ከእነዚህ መካከልም በዚህ ዓመት የተወሰኑትን እንደሚሰሩ ጠቁመዋል።ሰዎች እዚህ አካባቢ ማደር ሊፈልጉ ይችላሉ፤ ድንኳን የሚያድሩ አሉ፤ ቤት ማደር እፈልጋለሁ የሚል ሊመጣ ይችላል፤ ለእዚህም የጎጆ ቤት ቅርጽ ያላቸው ቤቶችን እንሰራለን ሲሉ ገልጸዋል።

ማህበረሰብ ተኮር የቱሪዝም ስራ ነው የምንሰራው፤ እዚህ ቦታ ላይ አብዛኛውን ግንባታ አናደርግም፤ ፈረስ አናረባም፤ ይህን ማቅረብ የሚችሉትንና የሚፈልጉትን ግን ለማገናኘት እንሰራለን ሲሉ ይገልጻሉ።ማህበረሰብ ተኮር ቱሪዝም ጎብኚው አርሶ አደሩ የሚኖረውን እየኖረ ጉብኝት የሚያደርግበት መሆኑን ጠቅሰው፣ አካባቢው የእንሰት ነው፤ ቆጮ እየፋቀ፣ እያረደ፣ እየበላ ማህበረሰቡን ተጠቃሚ እያደረገ እንዲጎበኝ ማድረግ ያስፈልጋል፤ ይህን ሁሉ በሰነዱ በሚገባ ተቀምጧል፤ ስለዚህ ማህበረሰቡ ዋና ተሳታፊ ሆኖ ይቀጥላል ነው ያሉት፡፡

የፌዴራል መንግስት የቱሪዝምን ጉዳይ እንደ ትልቅ ጉዳይ መያዙ የኛ ዞን በቱሪዝም ጉዳይ ላይ ይበልጥ እንዲሰራ አድርጎታል፤ የዞኑ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ እያለ ሌላ ቱሪዝም የሚያለማ ተቋም አቋቁሞ እየሰራ ያለውም ከዚሁ አኳያ እንደሚታይ ይገልጻሉ።‹‹ከመንግስት እቅድ ጋር ተቀራርበናል፤ ለምሳሌ እኔ ስራ አስኪያጅ ሆኜ የምመራው ፕሮግራም አብዛኞቹ ስራዎች በባህልና ተሪዝም መምሪያ ላይ የሚሰሩ ናቸው።ዞኑ ይህን ጉዳይ ለብቻ የሚሰራ ተቋም እስከ ማቋቋም የደረሰበት ዋናው ምክንያት የመንግስት አገራዊ አቅድ ነው ይላሉ፡፡

አረንጓዴ ልማትን በሚመለከት በአምበርቾ ተራራ ልማት እናት ሰነድ ላይ በግልጽ ሰፍሯል ያሉት አቶ ዘመዴ፣ 18 ሺ ሄክታር የሚሆነውን የአምበርቾ ተራራ ሙሉ በሙሉ በአገር በቀል ዛፍ የመሸፈን ዓላማ እንዳለም ይናገራሉ፤ አገር በቀል ዛፎች ብለን ለአኮኖሚው የሚጠቅሙትን ወደ ጎን አንተውም ያሉት ስራ አስኪያጁ፣ ለምሳሌ ቀርከሃ በብዛት እንዲለማ እንደሚደረግ ይጠቁማሉ።ለአፈር ይጠቅማል ብለን ኮርች ብቻ አንተክልም፤ ቀርከሃ ካልተከልን ስራ አጥነትን አንቀንስም ነው የሚሉት፤ ስለዚህ አረንጓዴ አሻራን በሚመለከት አንዱ ትልቁ ክንፍ/ ሀምሳ በመቶ በሚባል ደረጃ/ የአረንጓዴ ልማት ስራችን ይሆናል ያሉት ስራ አስኪያጁ፣ ለእዚህም ችግኝ ጣቢያዎችን እያቋቋምን እየሰራን ነው ይላሉ።መንግስታዊ ድርጅቶችን ከዚህ ጋር እያስተሳሰርን ነው።አብዛኛዎቹ ስራዎቻችን ከጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ጋር የሚገናኙ ናቸው ይባላል፡፡

ቦታው ለኢትዮጵያ አዲስ የቱሪዝም መዳረሻ ይሆናል ሲሉም ጠቅሰው፣ በእዚህ ተራራ ላይ የተገኘ ሰው 3ሺ 58 ሜትር ከፍታ ላይ ሲወጣ በጣም እንደሚቀዘቅዘው ይጠብቃል፤ ይሁንና ግን ተራራው አይቀዘቅዝም፤ በዚህ ክረምት እንኳ ጉም ከመምጣቱና ከመሄዱ ውጪ ያን ያህል ቅዝቃዜ ያለበት ስፍራ አይደለም ሲሉ ያብራራሉ።

ተራራው በበርካታ ኢትዮጵያውያንና የውጪ ዜጎች እየተጎበኘ እንደሚገኝም አቶ ዘመዴ ይጠቁማሉ፤ እሳቸው እንዳሉት፤ ከ2013 ጀምሮ እስከ አሁን ከ300ሺ በላይ ሰዎች ጎብኝተውታል፤ እጅግ በርካታ ሰዎች ተራራው አናትም ሜዳውም ላይ ድንኳን እየተከሉ ጭምር አድረዋል፤ ካምፕፋይር አርገዋል፤ ተደስተዋል፤ የተለያዩ ጎዞዎች ተደርገዋል፤ ከእነዚህ ጎብኚዎች መካከል 570 የሚሆኑት ደግሞ ዳያስፓራዎች ናቸው፤ ከ90 በላይ ደግሞ የውጭ አገር ቱሪስቶችም ጎብኝተውታል ሲሉ ይገልጻሉ።ጎብኚዎቹ ተራራውን የጎበኙት ተራራውን በዩቲዩቦች፣ በመገናኛ ብዙሃን ማስተዋወቅ በመቻሉ መሆኑን ይናገራሉ።የጎብኚዎች ምርጫ እየሆነ መምጣቱንም ጠቁመዋል። ጎብኚዎች ይህን ቦታ ሲጎበኙም ሆነ ለጉብኝት ሲመጡ ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆኑንም አቶ ዘመዴ በመጥቀስ መላ ኢትዮጵያውያን መስህቡን እንዲጎበኙት ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በከንባታና ጠምባሮ ዞን አስተዳደር፣ በዞኑ ምክር ቤት፣ ህዝብና ምሁራን ርብርብ እንዲለማ የተደረገው የአምበርቾ ተራራ ምእራፍ አንድ ፕሮጀክት ሌሎች ክልሎችና ዞኖቻቸውም ተሞክሮ መቅሰም የሚችሉበት አርአያነት ያለው ተግባር ነው።ዞኑ የዞኑ ብሄረሰቦች የመኖሪያ ቤቶች አሰራር፣ የባህላዊ ምግብ አዘጋጃጀት፣ ባህላዊ ዘፈኖችና ውዝዋዜዎች ፣ ዋሻዎች፣ ፏፏቴዎች፣ ፍል ውሃዎች፣ ወዘተ. ያሉበት ስለመሆኑ በቅርቡ በዞኑ ባደረግነው ጉብኝት የበለጠ መገንዘብ ችለናል።ዞኑ በጀመረው መንገድ አሁንም ህዝቡን ሌሎች የልማት ሀይሎችን ማስተባበሩን አጠናክሮ በመቀጠል ለቱሪዝም መስህብ ሊውሉ የሚችሉ የተፈጥሮ፣ የባህልና የታሪክ ሀብቶቹን በማልማት የተነሳበትን ዓላማ ለማሳካት መስራት ይኖርበታል፡፡

# ሳምንቱን በታሪክ

## ደራሲ አርበኛና ዲፕሎማቱ ክቡር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁ

ተገኝ ብሩ



መምህር ሆነው የተማሪዎቻቸውን የቀለም ጥማት አርክተዋል።አርበኛ ሆነው አገራቸውን ከጠላት ለመታደግ ተዋግተዋል።ዲፕሎማት ሆነው ስለአገራቸው ኢትዮጵያ ብዙ ሰርተዋል፣ ሚኒስትር በመሆን በተለያየ ዘርፍ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችን ለውጠዋል። ደራሲ ሆነውም በአገሪቱ ውስጥ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ የሆነ ስነ ፅሁፋዊ ስራ አበርክተዋል።የተለያዩ ሙያዎች ባለቤትም ነበሩና በልዩ ልዩ አለማቀፍ ተቋማት ውስጥ አገልግለዋል።አንድ ሆነው ብዙ ቦታ የተገኙ ብርቱ ሰው ናቸው።

በፈጠሩት ምዕናባዊ ዓለም ውስጥ በእውን የሚታየውን ዓለም የገለጡ ታላቅ የስነፅሁፍ ሰው።ጉዱ ካሣን አሳብደው በነፃነት እውነትን ያስለፈለፉ፣ ሰብለወንጌልን በፍቅር አሸፍተው የመውደድን ሀያልነት ያመላከቱ፣ በዛብህን አሳምፀው የሰው ልጅ ግለዊ ነፃነት ምን ያህል እንደሚሻ ለፍቅርና ለሰብዓዊነት ምን ያህል ዋጋ እንዳለው የገለፁ ድንቅ ብዕረኛ።

ያኔ የነበረውን የፊውዳሉ ዘመን ባህል፣ አስተሳሰብ እንዲሁም የአኗኗር ዘይቤ በዘመኑ ያልተፈጠረና ዛሬ ላይ ያለውን አንባቢን ጭምር በምናቡ ዘመኑን እየሳለ ያልኖረበትን ዘመን ጣእም እንዲያጣጥም ያስቻሉ የምንጊዜም ሀያል ፀሐፊ የ “ፍቅር እከ መቃብር” አባት ክቡር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁ ልደት በዚህ ሳምንት ነበረና እሳቸውን መዘከር ወደድን፡፡

በኢትዮጵያ ስነ ፅሁፍ ውስጥ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ የሆነ፤ የአገሪቱን ስነ ፅሁፍ በአንድ እርምጃ ወደፊት ያራመዱ ታለቁ ልቦለድ “ፍቅር እስከ መቃብር” የእርሳቸው ምዕናባዊ ዓለም ፍሬ ነው።ዛሬ ድረስ ከ ግማሽ ምዕተ ዓመተ በላይ ተደጋግሞ ከሚነሳው “ፍቅር እስከ መቃብር” ከተሰኘው መፅሀፍ ባሻገር በርካታ ድርሰቶችን አበርክተዋል።በተለያዩ ሀላፊነቶች አገራቸውን አገልግለዋል፡፡

በተለይ በወቅቱ በኢትዮጵያ የነበረው ንጉሳዊ ስርዓትና አንዳንድ አስተዳደራዊ ገፅታን ፍንትው አድርገው የገለፁ ታላቅ የስነ ፅሁፍ ሰው ነበሩ።ክቡር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁ የተወለዱት ጥቅምት 7 ቀን 1902 ዓ.ም በደብረ ማርቆስ አውራጃ በጎዛምን ወረዳ በእንጾር ኪዳነ ምኅረት ቀበሌ ነው።

ዲፕሎማት፣ መምህርና ደራሲ ሀዲስ አለማየሁ ደራሲ አባታቸው ከቄስ ዓለማየሁ ሰለሞን እናታቸው ከወይዘሮ ደስታ ዓለሙ ይባላሉ።ገና በጨቅላ እድሜያቸው በቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን ትምህርት በቤተሰባቸው አጠገብና ባባታቸው አገር ደብረኤልያስ ሄደው የግእዝ ትምሕርት ቤት ቅኔ ተቀኙተዋል። የተለያዩ ሀይማኖታዊ ትምርቶችን ተምረዋል፡፡

በቅኔ ዘረፋ የተዋጣላቸው የነበሩት ሀዲስ አለማየሁ ልጅ ሆነውም በብዙ ተማሪዎች ዘንድ በፈጣንነታቸው ይታወቁ ነበር።በእርግጥ አባታቸው ቄስ አለማየሁ የቅኔ ሊቅ ነበሩ።በእርሳቸው የበዙ የቅኔ ተማሪዎች ፈርተዋል።በተለይ ቅኔን በዜማ በመቀኘት በብዙዎች የታወቁ ነበር።ሀዲስ ለአባታቸው አንድ ልጅ ሲሆኑ በኋላ ላይ ከአባቱ የተፋቱት እናቱ ግን ከሌላ ሁለት ልጆችን ወልደዋል።

የቤተክርስቲያን ስርዐታትንና መንፈሳዊ ትምህርትን በጎጃም ገዳማት በደብረ ኤልያስ፣ በደብረ ወርቅና በዲማ በመማር አጠናቀቁ።በ1917 ዓ.ም. አስተማሪያቸው ከነበሩት ጋር ተከትለው አዲስ አበባ በመሄድ በስዊድን ሚሽነሪ ትምህርት ቤት ገብተዋል።እዚያ የቋንቋና ሌሎች ትምህርቶችን እስከ ሶስተኛ ክፍል ተከታትለዋል፡፡

ከሶስተኛ ክፍል ጀምሮ ደግሞ ራስ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ቤት ትምህርታቸውን ተከታተሉ። በዚያ ትምህርት ቤት ሳሉ ነበር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁ ልዩ የሆነው የስነፅሁፍ ክህሎታቸው መገለጥና ለስነጥበብ ልዩ ትኩረት መስጠት የጀመሩት።በተለይ በትምህርት ማብቂያ ላይ ይቀርቡ የነበሩ የተለያዩ የኪነ ጥበብ ዝግጅቶች ላይ በመሳተፍ ጥበብን ሀ ብለው ጀመሩ።በወቅቱ በንጉሱ ፊት ይቀርቡ የነበሩ የመድረክ ተውኔቶች ላይ የመካፈል እድልም ገጥሟቸው ነበር።ለዚህ የሚሆን ተውኔትም አዘጋጅተው ነበር።ይህ ቃለ ተውኔት፤ በኢትዮጵያ ስነ ፅሁፍ ታሪክ ውስጥ ከቀዳሚዎቹ ቃለ ተውኔቶች የሚጠቀስ መሆኑን በመስኩ ላይ ጥናት ያደረጉ ሙህራን ይገልፃሉ። በዚህ የተውኔት ስራና በስነፅሁፍ እንቅስቃሴያቸው ከንጉስ ሀይለስላሴ የእጅ ሰዓትና 50 ብር የተበረከተላቸው ዶክተር ሀዲስ ሽልማቱ እጅግ ብርቱ እንዲሆኑ ረዳቸው፡፡

ከትምህርት ቆይታቸው በኋላ የመምህርነት ስልጠናበመውሰድአዲስአበባላይለዓመታትለበርካታ ተማሪዎች የቀለም አባት ሆነዋል።ተማሪዎቻቸውን ፊደል በማስለየት ከመሀይምነት አላቀዋል፤ አዳዲስ እውቀትና እሳቤዎችን የማውረስና የማስገብየት ስራን በትጋት ሰርተዋል፡፡

ወደ ጎጃም ሄደውም ዳንግላ ላይ በእርሰ መምህርነት አገልግለዋል።በአስተማሪነት ሥራ ተሰማርተው እንዳሉ የፋሽስት ጣሊያን ወረራ ተከሰተ። የኢጣልያ ወረራ ሲከሰት ከልዑል ራስ ዕምሩ ኃይለ ሥላሴ ጦር ጋር በምዕራብ ኢትዮጵያ በአርበኝነት ሲዋጉ፤ አገራቸውን ከዚህ ወራሪ ጠላት በመከላከል ቆዩ።በየቦታው ህዝብ ለአገሩ እንዲዋጋ አነሳስተዋል።በዚያ ወቅት ቀስቃሽን አነሳሽ የሆኑ ተውኔቶችን በመፃፍም ህዝቡ ለአገሩ እንዲዋደቅ በሙያቸውም አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡

ሙሉ ለሙሉ ወደ ውጊያ በመግባት ትግራይ አካባቢ ሽሬና አካባቢዋ ላይ ከጠላት ጋር ተፋልመዋል።በጦር ሜዳም ሆነው ጊዜ ሲያገኙ የተለያዩ ግጥሞችን በተለይም አርበኞች የሚያነሳሱ ግጥሞች ያዘጋጁ ነበር።ሽሬ አካባቢ የነበረው ጦርነት በድል ተወተው ወደ ጅማ በማቅናት ላይ ሳሉ ጅማ በጣሊያን እጅ መውደቅዋ ሰምተው ከጉዞዋቸው ተገቱ።ወደ ኋላ በማፈግፈግም ለጥቂት ጊዜ ቆዩ።በኋላ ላይ በወራሪው የኢጣሊያ መንግስት በመያዛቸው ከልዑል ራስ እምሩ ጋር በግዞት ለሰባት ዓመታት ጣሊያን በሚገኘው በፖንዛ ደሴትና በሊፓሪ ደሴት ታስረው በእስር አሳልፈዋል።

በተለይም በዚያ እስር ላይ በነበሩበት ወቅት ሀይለኛና ስር የሰደደ የሳንባ ምች በሽታ ተይዘው ተሰቃይተዋል። ይህ በሽታ ለዓመታት ፀንቶባቸው ቆይቷል። ከዚያም የተባባሪ ኃያላት ማለትም በእንግሊዝ ወታደሮች በ1935 ዓ.ም. ከእስር ቤት አስመለጡዋቸው፡፡

ከእስር ቤት ከወጡ በኋላ ለትምህርት ልዩ ፍቅርና አዲስ ነገር ለማወቅ ልዩ ፍቅር የነበራቸው ክቡር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁ በኦክስፎርድ ትምህርታቸው ከገፉ በኋላ በተለያዩ የመንግስት ተቋማት ውስጥ ወደማገልገሉ ተመለሱ።ትጉህና ታታሪ የነበሩት እኚህ ድንቅ የብዕር ሰው በተለይም በትምህርት ሚኒስቴር ለረጅም ጊዜ አገልግለዋል።

በመንግስት መስሪያ ቤቶችና በተለያዩ ተቋማት የቆዩባቸው የስራ እና የሀላፊነት ቦታዎች ለመግለፅ ያህል፡- 1936 የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሠራተኛ፣ 1937 እስከ 1938 የኢትዮጵያ ቆንሲል በኢየሩሳሌም፣ 1938 - በ International Telecommunications Conference አትላንቲክ ከተማ የኒው ጀርሲ ወኪል፣ 1938 እስከ 1942 በተባበሩት መንግሥታት ቢሮ ኒው ዮርክ ሠራተኛ፣ 1942 እስከ 1948 የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ዳይሬክተርና ምክትል፣ 1948 እስከ 1952 የተባባሩት መንግሥታት ድርጅት የኢትዮጵያ አምባሳደር፣ 1952 የትምህርት ሚኒስትር በመሆን፣ 1952 እስከ 1957 የኢትዮጵያ አምባሳደር በእንግሊዝና ሆላንድ፣ 1957 እስከ 1958 የልማት ሚኒስትር፣ 1960 እስከ 1966 ሴናተር በመሆን አገራቸውን እና የተለያዩ ዓለማቀፍ ተቋማት ላይ በማገልገል ለአገራቸው አስተዋፅዖ አበርክተዋል።

በተለይም በዓለማቀፍ ደረጃ ኢትዮጵያ ድምፅዋ ጎልቶ እንዲሰማና ተፅዕኖ ፈጣሪ ትሆን ዘንድ በተለያ መድረኮች ኢትዮጵያን በመወከል ተሟግተዋል፤ ስለ አገራቸው አቅማቸው በፈቀደው ሁሉ ሰርተዋል።እኚህ ዘርፈ ብዙው ሙያተኛና የስነፅሁፍ እንቁ ያኔ ፕሬስና ፕሮፓጋንዳ መምሪያ ይባል በነበረው መስሪያ ቤት (ያሁኑ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት) ውስጥ አገልግለዋል፡፡

አብዛኛ የስነፅሁፍ ቤተሰብ የሚያውቀውን “ፍቅር እስከ መቃብር” የተሰኘው በአቀራረቡና በስነ ፅሁፋዊ ይዘቱ ከፍ ያለው የረጅም ልቦለድ መፅሀፋቸው በተጨማሪ ቁጥራቸው በርከት ያሉ መፅሀፎችን፣ ተውኔቶችን፣ ግጥሞችና የተለያዩ ፅሁፎችን ለተደራሲው አድርሰዋል።ክቡር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁ እስራኤል እያሉ ያገቡዋቸው ባለቤታቸው ወይዘሮ ከበበ ፀሀይ በመሞታቸው ትልቅ ሀዘን ውስጥ ለዓመታት ቆይተዋል።አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አካባቢ የነበረው መኖሪያ ቤታቸው በባለቤታቸው ስም በመሰየም ለህፃናት ማሳደጊያ ይሆን ዘንድ ለአዲስ አበባ መስተዳድር አስረክበዋል።ባለቤታቸው ከሞቱ በኋላ ሌላ ባለማግባት ለባለቤታቸው ያላቸው ታላቅ ፍቅር በተግባር ያሳዩም ሰው ነበሩ፡፡

የክቡር ዶክተር ሀዲስ ዓለማየሁ በርካታ ከስነጽሑፍ ሥራዎቻቸው መካከል፡- ከነዚህም ውስጥ ታላቅ አድናቆትንና እውቅናን ያተረፈው ሥራቸው “ፍቅር እስከ መቃብር” (1958) የተሰኘው ረጅም ልቦለድ ሲሆን በሁለት የተለያዩ መደቦች ውስጥ የሚገኙ የሁለት ሰዎች የፍቅር ታሪክ ላይ ሲያተኩር፤ በጊዜው የነበረውን ወግና ልማድ ይገልጻል።

ሌላኛው በ1970 “ወንጀለኛው ዳኛ” የተሰኘ የረጅም ልቦለድ መፅሀፍ ሲያበረክቱ በ1980 ደግሞ ስለ ማህበራዊ ጉዳዮችና ስለ ጣሊያን ውርስ የሚዳስሰውን “የልም እዣት” የተሰኙትን ልብ ወለድ ታሪኮች ለንባብ አቅርባዋል። ከታተሙ ስራዎቻቸው ይልቅ ሳይታተሙ የቀሩት እጅጉን እንደሚበልጡ ደራሲው በአንድ ወቅት የሰጡት አስተያየት ያስረዳል።

ከረጅም ልቦለድ መፅሀፎቻቸው በተጨማሪም በሌላ ዘርፍ የስነ ፅሁፍ ስራዎቻቸው ዛሬ ድረስ የሚነሱት እኚህ ታላቁ ብዕረኛ “የአበሻና የወደኋላ ጋብቻ” የተሰኘ ተውኔት ፅፈው አዘጋጅተውም ነበር።መፅሀፍም “ተረት ተረት የመሰረት” የተሰኘ መፅሀፍና “ትዝታ” የተሰኘ በራሳቸው ህይወት ላይ የተመሰረተ መፅሀፍም አበርክተዋል።በእርግጥ እነዚህ ህዝብ ጋር የቀረቡ በመሆናቸው ተጠቀሱ እንጂ ሀያሉ የብዕር ሰው ክቡር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁ ከትምህርት ቤት ጀምረው በብዕራቸው የጥበብ ዓለም በተለያየ መልኩ ሲያስዳስሱ ኖረዋል፡፡

ሀዲስ ዓለማየሁ በኢትዮጵያ የስነ ጽሑፍ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ በማበርከታቸው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የዶክተርነት ማዕረግ ተሰጥቷቸዋል። ደራሲው በኅዳር 26 ቀን 1996 ዓ.ም. በ94 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ይህንን ፅሁፍ ስናዘጋጅ በደራሲ ሀዲስ አለማየሁ የተዘጋጀው “ትዝታ” የተሰኘው ስለራሳቸው ህይወት የሚተርከው መፅሀፍ፣ ደራሲውን የተመለከቱ ልዩ ልዩ ፅሁፎችንና ድህረ ገፆችን ተጠቅመናል።

# የዝነኞች ገጽ

# ፍቅር እስከመቃብርን በህይወት የኖሩት ሰው

**አቤል ገ/ኪዳን**

የክብር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁ የተወዳጁ ፍቅር እስከ መቃብር ልቦለድ ደራሲ ናቸው። ነገር ግን ከፍቅር እስከ መቃብር ድርሰታቸው ባልተናነሰ ፍቅራቸውን እስከ መቃብራቸው ይዘው የዘለቁ እውነተኛ የፍቅር መምህርም ናቸው። ይህ ወር የተወለዱበት ወር ነውና ይህንን መነሻ በማድረግ ታሪካቸውን ወደ ማውሳት እንሻገራለን።

የሀዲስ የትዳር አጋር የነበሩት ወይዘሮ ክበበጸሀይ ያረፉት ገና በተጋቡ በአፍላ እድሜ ላይ ነበር። ይሁንና ያኔ ወጣት የነበሩት ሀዲስ ሀዘናቸውን ውጠው ሌላ ትዳር ሳይመሠርቱ ነበር የኖሩት። በአንድ ወቅት ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ ክብር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁን እንዲህ አላቸው፡-

"ለምን ሌላ ትዳር ሳይመሰርቱ ከ50 ዓመታት በላይ ቆዩ? ልጅም እንኳን አልወለዱም?" እሳቸውም የጣት ቀለበታቸውን አሳዩትና እንዲህ አሉት "ይሔን ቀለበት ያሰረችልኝ ክበበጸሀይ ናት። እኔም አስሬላታለሁ። እሷ የኔን ሣታወልቀው ነው ያረፈችው። እኔም የእሷን አላወልቀውም። ማንም አያወልቀውም። እሷ ነች ያሰረችልኝ" ሲሉ መለሱለት።

ከጻፉት በላይ ሆኖ እንደመገኘት የሚያረካ ነገር ይኖር ይሆን? ጋዜጠኛ ጥበቡ እንዳለው "ፍቅር እስከ መቃብር የሚባለው ታሪክ ከሀዲስ ህይወት ሌላ ምን አለ? ለትዳራቸው እስከ መጨረሻው ድረስ ታማኝ የሆኑ ክስተት ናቸው።"

ለመሆኑ ሀዲስ አለማየሁ ማን ናቸው? ሀዲስ ከአለቃ ዓለማየሁ ሰለሞን እና ከወይዘሮ ደስታ ዓለሙ በ1902 ዓ.ም ጎጃም ውስጥ ተወለዱ። አያታቸው (የእናታቸው አባት) አለቃ ዓለሙ ስዩም በእንዶዳም ኪዳነ ምኅረት ገዳም የዜማ መምህር ስለነበሩ ስድስት ዓመት ሲሞላቸው የግዕዝ ፊደሎችን ማጥናት ጀመሩ። ከእንዶዳም ኪዳነምኅረት በተጨማሪ በደብረ ኤልያስ፣ በደብረ ወርቅና በዲማ ጊዮርጊስ ገዳማት ተዘዋውረው የድጓ፣ የቅኔና የመጻህፍት ቤት (ትርጓሜ) ትምህርቶችን ተማሩ። በትምህርታቸውም ከጓደኞቻቸው ሁሉ የላቁ ነበሩ። በ1918 ዓ.ም ሀዲስና ሌሎች ጓደኞቻቸው ከመምህራቸው መሪጌታ በላይ ጋር በመሆን ወደ አዲስ አበባ አቀኑ።

አዲስ አበባ ደርሰው ጥቂት ጊዜያትን ካሳለፉ በኋላ አቶ አያሌው ንጉሤ ከተባሉና በስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት ያስተምሩ ከነበሩ ግለሰብ ጋር ተዋወቁ። አቶ አያሌውም ሀዲስና ጓደኞቻቸው ወደ ስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት ገብተው ዘመናዊ ትምህርት እንዲማሩ መከሯቸው። ሀዲስ ትምህርት ቤቱ ሀይማኖቴን ሊያስለውጠኝ ይችላል ብለው በመፍራታቸው ጥቂት አመነቱ። በመጨረሻ ግን ወደ ስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት ገብተው ትምህርቱን ጀመሩ። በሂደትም የዘመናዊ ትምህርትን ጥቅም በማወቃቸው የመንግስት ትምህርት ቤት መግባት እንዳለባቸው ወስነው ተፈሪ መኮንን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤትን ተቀላቀሉ። ከራስ ኃይሉ ተክለሃይማኖት ግምጃ ቤት ባገኙት ወርሃዊ የገንዘብ ድጋፍም ከሶስተኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ድረስ ያለውን ትምህርት በተፈሪ መኮንን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታተሉ።

በወቅቱ በትምህርት ቤቱ ውስጥ አመጽ ተቀስቅሶ ነበር፤ «... የአመጹ ጠንሳሾች በእድሜያቸው በሰል ያሉት ተማሪዎች ናቸው ... » ተብሎ በመታመኑ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ ተማሪዎች ማደሪያቸው ከትምህርት ቤቱ ውጭ ሆኖ እንዲማሩ ተወሰነ። ይህ ውሳኔ አዲስ አበባ ውስጥ ቤተሰብና የቅርብ ዘመድ ለሌላቸው የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች አስደንጋጭ ነበር። ሀዲስ አዲስ አበባ ውስጥ ቤተሰብም ሆነ የቅርብ ዘመድ ስላልነበራቸው ትምህርቱን ለማቋረጥ ተገደዱ።

በወቅቱ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ይሰጥ የነበረውን የመምህርነት ስልጠና ወስደውም በስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት ማስተማር ጀመሩ። ከዘጠኝ ወራት የመምህርነት ስራ በኋላ ዳንግላ አካባቢ በነበረው የብሪታኒያ ቆንስላ ውስጥ እንዲሰሩ ተመደቡ። ዳንግላ አካባቢ የነበረው የብሪታኒያ ቆንስላ ከተዘጋ በኋላ ሀዲስ በአካባቢው የነበረው ጉምሩክ ተቆጣጣሪ ሆነው መስራት ጀመሩ። በዚህ ስራቸውም ላይ ብዙም አልቆዩም። በወቅቱ በአካባቢው የባሪያ ንግድ ይካሄድ ስለነበር የባሪያ ንግድ እንዲቆም የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት ያወጣቸውን ድንጋጌዎችን የማስፈጸምና የመከታተል ኃላፊነት ተሰጥቷቸው ኃላፊነቱን አከናወኑ። ከዚያም በዳንግላም ሆነ በመላው አገው ምድር የመጀመሪያ የሆነውን የዳንግላ ትምህርት ቤትን እንዲያቋቁሙ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ተወጡ። ሀዲስ የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተርና መምህር ሆነውም አገልግለዋል።

በ1928 ዓ.ም ወደ ደብረ ማርቆስ ተዘዋውረው በንጉስ ተክለሃይማኖት ትምህርት ቤት የእንግሊዝኛና የሂሳብ መምህር ሆኑ። የወቅቱ የጎጃም ገዢ የነበሩትን የልዑል ራስ እምሩ ኃይለስላሴ ልጆችንም ያስተምሩ ነበር። እስከ ፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ጊዜ ድረስም በዚያው በደብረ ማርቆስ ቆዩ።

ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮያን በወረረችበት ወቅት ሀዲስ ከመንግስት ሳይጠብቁ ራሳቸው ጠመንጃ ገዝተው፣ የራስ እምሩን ጦር ተቀላቅለው በአርበኝነት መዋጋት ጀመሩ። የህዝቡንና የአርበኛውን ስሜት የሚቀሰቅሱ የኪነ ጥበብ ስራዎችንም እየሰሩ አቀረቡ። በ1929 ዓ.ም ጎጀብ ወንዝ አካባቢ በተደረገ ውጊያ ላይም ተማርከው ፖንዞ እና ሊፓሪ ወደሚባሉና በሳርዲና አካባቢ (ደቡባዊ ኢጣሊያ) ወደሚገኙ የሜዲትራኒያን ደሴቶች ተወስደው ታሰሩ። ከሰባት ዓመታት የእስራት ጊዜ በኋላም አርበኛው ሀዲስ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ።

ከስደት መልስ ሀዲስ በተለያዩ ዘርፎች ያገለገሉ ሲሆን በተለይም በፖለቲካው ረገድ ሚኒስትር ዴኤታ እና ዲፕሎማት ሆነው አገራቸውን ብዙ አገልግለዋል። ይሁንና ሀዲስ በተለይ ዲፕሎማት ሆነው አዳዲስ ልምዶችን ቀስመው ከመጡ በኋላ ከንጉሰ ነገስቱ ጋር የነበራቸው ግንኙነት ብዙም የሰመረ አልነበረም። በተለይም ለውጥን አስመልክተው ለንጉሱ የጻፉት መልእክት አስከፍቷቸው ነበር። በዚህ መልዕክታቸው በ1953 ዓ.ም የተሞከረው መፈንቅለ መንግሥት መንስዔና ወደፊትም የመንግስት አሰራር ካልተሻሻለ የከፋ ችግር ሊያጋጥም እንደሚችል በመጥቀስ ኋላ ቀር የሆነው የኢትዮጵያ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መዋቅር ሊሻሻል እንደሚገባ ገልጸዋል። ይህ መረር ያለ የሀዲስ ምክረ ሃሳብ ስልጣናቸውንና ክብራቸውን እንደዓይናቸው ብሌን ለሚጠብቁት ንጉሰ ነገስቱ ምቾትን አልሰጠም። በዚህም ንጉሰ ነገስቱ ሀዲስን ቢሯቸው አስጠርተው ‹‹ድፍረት ስለተሞላበት›› ደብደቤያቸው ገሰጿቸው። ሀዲስ ግን በንጉሰ ነገስቱ ሃሳብ ባለመስማማት በመልዕክታቸው ካሰፈሩት ሃሳብ በተጨማሪ ሌሎችንም ምክረ ሃሳቦችን ለንጉሰ ነገስቱ ተናገሩ። መልዕክቱ ለንጉሱ በደረሳቸው በስምንተኛው ቀንም ሀዲስ የትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ እንዲሆኑ ተደረገ። ንጉሰ ነገስቱ ራሳቸው የትምህርት ሚኒስትር ስለነበሩ ሹመቱ ከፍተኛ ትችት የሰነዘሩባቸውን ደፋሩን፣ በግልፅ ተናጋሪውንና ትሁቱን ሀዲስን ከጎናቸው አድርገው ለመቆጣጠር እንደሆነ ግልጽ ነበር። በኋላ ላይ ሀዲስ በገዛ ፈቃዳቸው ከትምህርት ሚኒስቴርነት ሲነሱ ዲፕሎማት ተደርገው ከአገር ራቅ እንዲሉ ተደረገ ባለቤታቸውም ያረፉት በዚህ ወቅት ነበር።



የክብር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁ

ሀዲስ በህዝብ ዘንድ በተለይ የታወቁት በደራሲነታቸው ሲሆን በኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እንደ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰደው ፍቅር እስከ መቃብርን ጨምሮ ሌሎች መጻህፍትንም ጽፈዋል። ከጻፏቸው መጻህፍት መካከል በተረት ብዙ ፍልስፍናዎችን ብዙ ትልልቅ ነገሮችን የተናገሩበትና ያስተማሩበት በ1948 ዓ.ም የጻፉት ተረት ተረት የመሰረት በሚለው መጽሀፋቸው ነው። ከዚያ በመለጠቅ በ1948 ዓ.ም የትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም በሚል ስለትምህርት የጻፉ የመጀመርያው ሰው ናቸዉ። ሌላው ላለፉት 50 ዓመታት በኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ ውስጥ ትልቅ ማስተማርያ የሆነና የኢትዮጵያን ስነ ጽሁፍ ከፍ ብሎ እንዲታይ ያደረገ መጽሀፋቸው «ፍቅር እስከ መቃብር» የተሰኘው ልብወለድ 1958 ዓ.ም የታተመ ነው። በኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ ውስጥ አዲስ ክስተት አዲስ አስተሳሰብ ያመጣ ትውልድን ያነቃነቀ፤ ለለውጥ በብዙ ፍልስፍናዎች ብዙ ጥያቄዎችን ያነሳሳ መጽሀፍ ነው። ሌላው ኢትዮጵያ ምን ዓይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል በሚል በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ተጽፎ የቆየ ነው። ሀዲስ አለማየሁ ይህንኑ ጽሁፋቸውን ለጃንሆይም አሳይተዋቸው ይታተማል ብለዋቸው ግን እሳቸዉም ያላሳተሙላቸው፤ በኋላም የደርግ አስተዳደር 1966 ዓ.ም ላይ ከመጣ በኋላ ለደርግ ሰጥተውት አይታተምም ተብሎ ያልታተመ መጽሀፋቸው ነው። ሌላው በኢትዮጵያ ስነጽሑፍ ውስጥ እንደዚሁ ተጠቃሽ የሆነው በ1974 ዓ.ም ያሳተሙት ወንጀለኛው ዳኛ የተሰኘው መጽሀፋቸው ነው። የጥንታዊውን የኢትዮጵያ የጋብቻ ሁኔታ ያሳዩበት በ1980 ዓ.ም ያሳተሙት የልምዣት የተሰኘው ትልቁ መጽሀፋቸውም ይጠቀሳል። ወደ መጨረሻ ላይ የጻፉትና የሳቸውንም ሆነ በሳቸው የዕድሜ ዘመንተኛ የሆኑ የሌሎችን ኢትዮጵያውያን የህይወት ታሪክ እና የኢትዮጵያን ታሪክ የዳሰሱበት ትዝታ የተሰኘው መጽሀፋቸው በ1985 ዓ.ም ያሳተሙትና ያስነበቡት ግሩም መጽሀፍም የቀዳሚነት ቦታን የሚይዝ ነው።

ከእለተ ሞታቸው ሁለት ዓመታት ቀደም ብሎ ቃለመጠይቅ ያደረገላቸው ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ ስለ ፍቅር እስከ መቃብር ያጫወቱትን ጉዳይ በአንድ ወቅት ለጀርመን ድምጽ ራዲዮ እንዲህ ብሎ ተናግሮ ነበር። «ደራሲ ሀዲስ አለማየሁን በ1994 ዓ.ም አዲስ ዜና ለተሰኘው ጋዜጣ ቃለመጠይቅ አድርጌላቸው ነበር። የዚያን ጊዜ እንደነገሩኝ ፍቅር እስከ መቃብር መጽሀፍ እንደታተመ ሰዎች መጽሀፉን ይዘው ለጃንሆይ አሳይዋቸው። ይኸው አዲስ አለማየሁ ከኛ ጋር እየኖረ በኛ ተሹሞ የዚሁ የኛው መንግስት ባለስልጣን ሆኖ እንዲህ ዓይነት መጽሀፍ አዘጋጅቶ መንግስታችንን አዋረደ ብለው ለጃንሆይ ሰጧቸው። ጃንሆይም ተቀብለው መጽሀፉን ሲያዩ ርዕሱ ፍቅር እስከ መቃብር ይላል ከስሩ ልብ ወለድ ታሪክ ይላል እና ወድያው ሳያነቡ መለሱላቸው። ምንድን ነው የምትሉት እናንተ ሰዎች፤ ይሄ ሰው ፍቅር እስከ መቃብር ልብ ወለድ ታሪክ ብሎ ነው የጻፈው፤ ልቡ የወለደውን ነው የጻፈው ምን አድርግ ነው የምትሉት? ብለው ጃንሆይ መለሱት ስለዚህ ያ መጽሀፍ ተጽኖም አልፈጠረብኝም በጃንሆይ በኩል እንደውም ከሚወድዋቸው መጽሀፍት አንዱና ዋናው እሱ ነበር። ምክንያቱም እሳቸው የሚያስቡት እኔ የጻፍኩበትን ስርዓተ ማህበር እሳቸው ካሉበት በፊት የነበረ ብለው ነው ያሰቡት›› ብለዋል።

ሀዲስ በስነ ጽሁፍ ስራዎቻቸውም የቀዳማዊ ኃይለስላሴ የስነጽሁፍ ሽልማትን አሸንፈዋል። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሰጥቷቸዋል። ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ያሰራላቸው ከነኀስ የተቀረጸ ሃውልት በ2009 ዓ.ም በደብረ ማርቆስ ከተማ ቆሞላቸዋል። የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበርም በ2002 ዓ.ም ለክብር ዶክተር ሀዲስ ዓለማየሁ ያዘጋጀው የፖስታ ቴምብር በኢትዮጵያ የፖስታ ድርጅት ታትሞ ተሰራጭቷል። የደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲም ሀዲስ አለማየሁ የባህል ጥናት ተቋም የሚል ተቋም በስማቸው አቋቁሟል።

በኢትዮጵያ የፖለቲካና የስነጽሁፍ ዘርፎች ላይ ገናና ስም የነበራቸው ደራሲ፣ መምህር፣ ፖለቲከኛ፣ አርበኛ፣ ባለቅኔ፣ ... የክብር ዶክተር ሀዲስ ዓለማየሁ በ1996 ዓ.ም በ94 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ስርዓተ ቀብራቸውም በአዲስ አበባ፣ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ስላሴ ቤተክርስቲያን ተፈጽሟል።

# ዓለም አቀፍ



## በሽሮፕ ምክንያት እየጨመረ ያለው አሳሳቢው የሕጻናት ሞት

**ዋቅሹም ፈቃዱ**

በህንድ ሰራሹ የሳል ሽሮፕ ምክንያት በጋምቢያ የተከሰተው የሕጻናት ሞት በብዙ የዓለም አገራት እየተስተዋለ ነው፡፡ ሽሮፕ በኢንዶኔዥያ የ133 የሕጻናት ሞት ማስከተሉን አልጀዚራ ዘግቧል፡፡

ሰሞኑን በጋምቢያ የተስተዋለው በሳል ሽሮፕ የሕጻናት ሞት ቀስ በቀስ ወደ ዓለም እየተስፋፋ መሆኑ በብዙዎች ዘንድ ድንጋጤን ፈጥሯል፡፡ የህንድ ባለሥልጣናትም ችግሩን ለማጣራት የመድኃኒቱን አምራች ካምፓኒው ዘንድ መርማሪ የጤና ባለሙያዎች መላኩ የሚታወስ ነው፡፡

የሳል ሽሮፑ በኩላሊት ላይ ከፍተኛ የመቁሰል አደጋ በማስከተል ለሞት የሚያበቁ ኤቲሊን ግላይኮል እና ዲኢታይሊን ግላይኮል የሚባሉ አደጋኛ ንጥረ ነገሮችን በውስጡ የያዘ ሲሆን ቀደም ሲል ለመጀመሪያ ጊዜ በጋምቢያ ለ69 ሕጻናት ሞት ምክንያት መሆኑ ይፋ ተደርጎል፡፡

የኢንዶኔዥያ የጤና ባለሥልጣናት በዚህ ሳምንት ከጥር ወር ጀምሮ በሽሮፑ የሕፃናት ሞት ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እየጨመረ ከመምጣቱ ጋር ተያይዞ ባካሄዱት ምርመራ የሞት ምክንያቱ የሳል ሽሮፕ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ የመድኃኒቶችን ሽያጭ እና ማዘዣ ለጊዜው አግደዋል።

የአገሪቱ የምግብና የመድኃኒት ኤጀንሲ ከምርቶቹ ውስጥ ከመጠን በላይ የሆነ የኢትሊን ግላይኮልን የያዙ አምስት ምርቶችን ከገበያ አውጥቶ አምራቹን ከስርጭት አውጥተው የቀሩትን ምርቶች እንዲያወድሙ ትእዛዝ ሰጥቷል።

የጤና ጥበቃ ሚኒስትሩ ቡዲ ጉናዲ ሳዲኪን አርብ ዕለት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ "በ22 ግዛቶች ውስጥ 241 ከፍተኛ የኩላሊት ጉዳት የደረሰባቸውን ለይተናል" ካሉ በኋላ አብዛኞቹ ታካሚዎች ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት መሆናቸውን ጠቁመዋል።

የአገሪቱ የጤና ጥበቃ ባለስልጣናት በተጎዱ ህጻናት ቤት ውስጥ ሽሮፕ ንጥረ ነገሮቹ የያዙት ጉዳት ተጨማሪ 102 መድኃኒቶች ማግኘታቸውን ገልጸው፣ ብለዋል ሚኒስትሩ ረቡዕ እገዳው በሁሉም ሽሮፕ እና ፈሳሽ መድኃኒቶች ላይ የመድኃኒት ማዘዣ እና ሽያጮች እንደሚቀንሱ ተናግረዋል ።

ከሲንጋፖር ባስገቡት የሽሮፑ ፀረ-መድሃኒቶች ጤና ሚኒስቴሩ በህመምተኞች ዘንድ ማሻሻያ መታየቱን ተናግረው፣ ፀረ-መድሃኒቶች በመላው ኢንዶኔዥያ ለማሰራጨት ተጨማሪ ግዢ እንደሚፈጸም አክለው ገልጸዋል፡፡



## የቻድ መንግስት ሰባት ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችን አገደ

**በዋቅሹም ፈቃዱ**

ሰሞኑን በአገሪቱ የተከሰተውንና ከ60 ሰዎች በላይ ሞት ያስከተለውን ህዝባዊ ተቃውሞ ጋር ተያይዞ የቻድ መንግስት የሰባት ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎችን እንቅስቃሴ ለሶስት ወራት ማገዱ አሶሼትድ ፕሬስ ዘግቧል፡፡

ታዋቂው የተፎካካሪ ፓርቲ መሪ ሳሴስ ማስራ በትዊተር ገጹ ሌስ ትራንስፎርማታስ የተባለው የፓርቲው ብሔራዊ ዋና መሥሪያ ቤት ጸጥታ ኃይሎች መወረሩን አስፍረዋል። አክለውም፣ የጸጥታ ሀይሎቹ 70 ሰዎችን በጥይት ሲመቱ ከአንድ ሺህ በላይ ሰዎችን ካሰሩ፣ ካቆሰሉ እና ካሰቃዩ በኋላ ህንፃዎችን እና ሰነዶችን ጉዳት ማድረሳቸወን ገልጿል፡፡

የማሳራ ፓርቲ በቻድ መንግስት ለሶስት ወራት ከታገደባቸው ሰባት ፓርቲዎች መካከል

ሌስ ትራንስፎርማታስ የተባለው ተፎካካሪ ፓርቲ የቻድ መንግስት ካገዳቸው ፓርቲዎች መካከል አንዱና ዋነኛ መሆኑ ተገልጿል፡፡

ባሳለፍነው ሐሙስ የአገሪቱ ጊዜያዊ መሪ መሐማት ኢድሪስ ዴቢ የስልጣን ዘመናቸውን ለሁለት ተጨማሪ ዓመታት ማራዘማቸውን ተከትሎ ለመቃወም በቻድ ዋና ከተማ ኒጃሜና እና ሌሎች በርካታ ከተሞች ሰልፈኞች አደባባይ ወጥተዋል።

መሐማት ኢድሪስ የሽግግር መንግስት መሪ የሆነው አባቱ የቀድሞ የቻድ ፕሬዚዳንት ሆነው ከ30 ዓመታት በላይ ካገለገሉ በኋላ ባሳለፍነው ሚያዝያ ወር መሞታቸውን ተከትሎ ነው። የተቃውሞ መንስዔ የመሐማት ኢድሪስ የ18ቱ የሽግግር ወራት ሐሙስ እለት ማብቃት ሲገባው ፕሬዚዳንቱ ግን እንደገና ለሁለት ዓመታት በማራዘማቸው ምክንያት ነው፡፡ ተቃውሞ ከቁጥጥር ውጪ በመሆኑ የጸጥታ ሃይሎች በሰልፈኞች ላይ ከአስለቃሽ ጭስ በተጨማሪ የተኩስ እሩምታ በመክፈት ጉዳት ማድረሳቸው ተነግሯል፡፡ በአንድ ቀን ብቻ 30 ሰዎች መሞታቸውን የመንግስት ምንጮች ቢገልጹም የሰብዓዊ መብቶች ድርጅት ግን ቁጥር ከዚያ በላይ እንደሚሆን ገልጸዋል፡፡

የቻድ ጠቅላይ ሚኒስትር ሳሌህ ከበዛቦ በበኩላቸው መንግስታቸው የሃይል እርምጃ እንዳልወሰደ ተናግረው፣ ጉዳዩ ተቃውሞ ሳይሆን የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ሆኖም ግን በሰልፈኞቹ ላይ የተወሰደ የሀይል እርምጃ መሆኑን ፈረንሳይ፣ አሜሪካ እና የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ሊቀመንበር ሙሳ ፋኪ ማሃማት ጨምሮ እርምጃውን አጥብቀው አውግዘዋል።


EXPRESSION OF INTEREST FOR THE PROVISION OF MANUFACTURING AND INSTALLING TANKERS

EAST AFRICAN LION BRANDS MANUFACTURING S.C

East African Lion Brands Manufacturing S.C is seeking supplier(s) to manufacture and installing of different capacity tankers. Raw material tanks Terms of Reference (TOR)
Interested and capable tanker manufacturers may submit their Expression of Interest by providing the list of information specification and additional specification as listed below:

| No | Capacity (liter ) | Qt. | Specifications | Additional Specifications |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 300,000 liters | 2 | -Material: Mild steel<br>-Tanker Orientation: Vertical<br>-Plate thickness for bottom plate: 8mm<br>-Plate thickness for shell plate:6mm<br>-Plate thickness for top plate :4mm<br>-Bottom &Top manhole Made from: 10mm mild steel sheet& bolted withM20x60<br>- External surface is two coated of anti-rust & two coated of final synthetic paint | -Manufacturing &installation of vertical coil heating, internally it have 2 seamless steam pipe and elbow<br>- Installations of mechanical number counting level gauge<br>-Manufacturing & Installations of top tank part hand rail(RHS 40x40x2mm) & spiral stair ladder(RHS 30x30x2mm &3mm chequred plate) for the tank Inlet, Outlet, Drainage, safety valve, over flow flange |
| 2 | 100,000 liters | 1 | -Material: Mild steel<br>-Tanker Orientation: Vertical<br>-Plate thickness for bottom plate: 8mm<br>-Plate thickness for shell plate:6mm<br>-Plate thickness for top plate :4mm<br>-Bottom & Top manhole Made from: 10mm mild steel sheet& bolted withM18x60 | - Installations of mechanical number counting level gauge<br>-Manufacturing & Installations of top tank part hand rail (RHS 40x40x2mm)& vertical ladder for the tank(RHS40x40x2mm)<br>-Inlet, Outlet, Drainage, safety valve, over flow flange<br>-External surface is two coated of anti-rust & two coated of final synthetic paint |

**Statement Of compliance**

| # | Item Description |
|---|---|
| A | Legal company Registration in Ethiopia |
| B | Registration with relevant authorities to deliver the service |
| C | A minimum of 5 years of experience in delivering the services required |
| D | Demonstrate the experience of the Project team delivering the services required |
| E | Demonstrate the relevant experience in the services required and the value of current contracts and with whom |
| F | Details of the location of your premises within Ethiopia and contact details |
| G | Past consecutive 3 years of audited financial statements |
| H | Company Prole outlining the Directors names and Identity numbers to facilitate Due Diligence |

**SUBMISSION OF RESPONSES**

Interested suppliers should submit their response with stamped & sealed post in person in our office located at BISHOFTU beside Easter industry zone within 10 days from the date announced on the news papers.

**NEXT STEPS**

- Once the responses are received the further process will follow the steps below;
- Review of submitted Expressions of Interest
- Prequalification of shortlisted suppliers
- Issuing of 'Request for Proposal' to prequalified suppliers

**NOTE**

- Only the suppliers who meet our minimum requirements will be considered for further discussions.
- The receipt of response shall not bind East African Lion Brands Manufacturing S.C to any contractual agreements with the prospective bidder. Such arrangements shall only come in place once a tender process has been completed and an award issued to a successful bidder after technical and commercial evaluation.
- Any costs associated with the preparation and submission of the response to this tender shall be borne by the tender respondent.

**NOTE**

East African Lion Brands Manufacturing S.C reserves, at its sole discretion; the right to select or reject. either in totality or partially, any or all proposals made in the context of this tender.

**East African Lion Brands Manufacturing S.C**

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## በአገሬ ፤ በእናቴ ፤ በሚስቴ ፤ በእህቴና በሴት ልጄ ላይ ነው የተፈጸመው ፤

ዘ-ሀበሻ በቴሌግራም ገጹ " ሽብርተኛው ትህነግ የማረካቸውን የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት አባላት ሲያሰቃይና ግፍ ሲፈጽም የሚያሳይ ቪዲዮ ደርሶናል። ከደቂቃዎች በኋላ 'በረብል' አካውንታችን የምንለቀው ሲሆን የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችና ቡድኑን የምታጋልጡ አካላት እንድትመለከቱት እንመክራለን። "የሚለውን የዜና ፍንጭ*

/newsflash/አይነት ነገር ስመለከት፤ ወዲያው የጥቅምት 24 ፣ 2013 ዓ.ም የሰሜን ዕዝ ክህደትና ጭፍጨፋ ፤ በአፋርና በአማራ ክልሎች የተፈጸሙ ሰቆቃዎችንና ግፎችን ሳስታውስ ሆዴ ይታወክና ይታመም ጀመር። ወደ መጸዳጃ ክፍል መሔድ አስፈለገኝ። ወዲያው ያቺ ክፉ ሌሊት ወደ አእምሮዬ ከች አለች ። በወገኔ መሐል ነኝ ብሎ ትጥቁን ፈትቶ በተኛበት በውድቅ ሌሊት ለማየት የሚዘገንን ፣ ለመስማት የሚሰቀጥጥ ጭፍጨፋ የተፈጸመበት ጽልመተ ሌሊት ጥርሷን አግጥጣና ጥፍሯን አሹላ መጣችብኝ ። ሴት የመከላከያና የፌደራል ፖሊስ አባላት ላይ ለዛው የሰው ልጅ በ21 ኛው መክዘ በገዛ ዜጋውና መከታው ላይ ይፈጽመዋል ተብሎ የማይታሰብ ዘግናኝ ግፍ ተፈጸመ ። ይሄ ከሀዲና አረመኔ የተወለደበትን መህጸን በስለት ወጋ ፤ የጠባውን ጡት በሳንጃው ቆረጠ ። ሁለት ዓመታት ወደኋላ በሀሳብ ሄጀ ይሄን አስታውሸ ነው የዘ-ሐበሻ ኒውስፍላሽ ያውከኝ የያዘው ።

ሰሞኑን በማህበራዊ ሚዲያዎች በስፋት እየተዘዋወረ ብዙዎች በተቀባበሉት/viral/በሆነ በዚህ ቪዲዮ በጥላቻና በጭካኔ የታወሩ የሽብርተኛው ታጣቂዎች በሰደፍ እያዳፉና በዱላ እየከተከቱ ፤ ከምርኮኛ አያያዝ አለማቀፍ ሕግ ባፈነገጠና ፍጹም ኢሰብዓዊ በሆነ አግባብ እንደ ከብት ከሚነዷቸው የመከላከያ የደንብ ልብስ ከለበሱና ምርኮኛ ከሚመስሉ መካከል (ያው በእርግጥ የመከላከያ አባላት መሆናቸው በሚመለከተው አካል ስላልተረጋገጠ ነው የሚመስሉ ያልሁት፤) በሴቷ ላይ በተፈጸመ ድብደባ አፍንጫዋ ደምቶ ፣ አካሏ ተጎሳቁሎና ተዳክሞ የምትታይን ፤ ምን አልባትም ለበርካታ ቀናት በባዶ እግሯ በርሀብና በውሃ ጥም የተዳከመች ሴት ላይ የሚያዘንቡት ዱላና ጸያፍ ስድብ በእርግጥ እነዚህ አረመኔዎች ከሴት የተፈጠሩ ፣ እህት ያላቸው ፣ ሴት ያገቡና ሴት የወለዱ ናቸው !? ።

"የልጅ እናት ነኝ ፣"እያለች እንዲያ ስትማጸናቸው ቅንጣት ታህል ርህራሄ የማያሳዩት ምን ያህል በጭካኔና በጥላቻ ቢታወሩ ነው ፤ መልሱን ለማግኘት ገና ብዙ ስራ ይጠብቀናል ። እንግዲህ እነዚህ ግፈኞች ናቸው ሲማረኩ ተገደን ነው የሚሉን ፤ አፈግፍገው እንደ ሰላማዊ ሰው ማህበረሰቡ ውስጥ መልሰው የሚቀላቀሉት ። ይሄን ባሰብሁ ቁጥር ጦርነቱን በድል ከመቋጨት ወይም በድርድር ከመደምደም በላይ ገና ብዙ ስራ እንዳለብን ይሰማኛል ። በዚህ ጉዳይ አንድ ቀን በሌላ መጣጥፍ የምመለስበት ሆኖ ፤ በቪዲዮው የተመለከትኋት እህቴ ግን ለአገሬ ሉዓላዊነትና ቀጣይነት ፤ ለእኔ ነጻነት ዋጋ የከፈለች ወታደር ብቻ ሳትሆን ፤ የተፈጸመባት ግፍ በአገሬ ፣ በእናቴ ፣ በሚስቴ ፣ በእህቴና በሴት ልጄ ላይ የሆነ ነው ።

እዚህ በቅጡ ሊጤን የሚገባው ነገር ግፈኞች ሲፈጽሙት ያላፈሩበትን እኛ ሰለባዎች ልናፍርበትና ልንሸፋፍነው አይገባም ። የሩዋንዳውንና የደቡብ አፍሪካውን ጭፍጨፋዎችና ግፎችን የሚዘክሩ ሙዚየሞችን ከአህጉራችን የናዚን ግፎች ማስታወሻዎችን ከአውሮፓና ከአሜሪካ መመልከት በቂ ነው ። መደበኛው ሚዲያ ባላየና ባልሰማ ማለፉም ተገቢ አይደለም ። ፍርጥርጥ አርገን ልናወግዘውና ልንነጋገርበት ይገባል ። በዚህ ዘግናኝ ቪዲዮ ላይ ይሄን ያህል ካልሁ ፤ ነገርን ነገርን ያነሳዋልና በነካው ብዕሬ ከሚዘገንነውና ሞልቶ ከፈሰሰው የሽብርተኛው ትህነግ የጭካኔ ጥግ መለስ ብለን በስሱ እንቃኝ ።

የካቲት 11 ቀን ፣ 1967 ዓ ም በ11 ሰዎች በምዕራብ ትግራይ ቆላ በሽሬ አውራጃ ልዩ ስሙ ደደቢት በተባለ ስፍራ የተመሰረተው እና የቀዳማይ ወያኔ ቅርሻ የሆነው " ተጋድሎ ሓርነት ህዝቢ ትግራይ " / ተሓህት / ወደ አማርኛ ሲመለስ የትግራይ ሕዝብ አርነት ግንባር ፤ የዛሬው አሸባሪው ትህነግ ስንክሳር ሲገለጥ ደምቀው ከሚታዩት አሪዎስነት ፣ ክህደት ፣ ሴረኝነትና እስስታዊነት ይገኙበታል ። ስለከሀዲነቱ፣ ሴረኝነቱ ፣ መርህ አልባነቱ ስለሚገለጥበት እስስታዊነቱ በዚሁ ጋዜጣ በተደጋጋሚ ስለጻፍሁበት የዛሬው መጣጥፌ ትኩረት በአሪዎስነቱ ፣ በአረመኔነቱ ፣ በጨካኝነቱ ፣ በጭራቅነቱ/በቡልቡልነቱ/ላይ ነው ።

አሸባሪው ትህነግ ርህራሄና ሰብዓዊነት የሚባል ነገር ያልፈጠረበት ጨካኝ አረመኔ ነው ። የጭካኔው ጥግ የሰው ልጅ ይፈጽመዋል ተብሎ የማይታመን ነው ። በተለይ በአቦይ ስብሀትና በመለስ የሚዘወረው ቡድን የፖለቲካና የወታደራዊ ትርፍ እስካስገኘለት ድረስ ምንም ከማድረግ አይመለስም ። ይህ በላኤ ሰዕብነቱ ዛሬ ወይም ትላንት የተጀመረ ሳይሆን አብሮት ያደገና ጥርሱን የነቀለበት ነው ። የጋዜጠኛ አርዓያ ተስፋማርያም ፣ "ከሕወሓት ጓዳ"መጽሐፍ ይሄን ማንነቱን ፍንትው አርጎ ያሳያል ።

አሸባሪው ትህነግ ገና ከጅምሩ በአቋምና በአመለካከት የተለዩትን ፤ ለስልጣኔ ያሰጉኛል ያላቸውን እንደ ድመት እየበላ ያደገ ጨካኝ አረመኔ ነው ። እነ ገሠሠው አየለ/ስሁል/ ፣ ዮሐንስ ገብረመድህን/ዋልታ/ ፣ ዘርኡ ገሰሰ/አግአዚ/ እና ሌሎች በሴራ ገድሎ በመቃብራቸው የተረማመደ አሪዎስ ነው ። በተለይ በትግራይ ክልል ፊውዳል ብሎ የፈረጃቸውን ከ40ሺህ በላይ ትግራዋይን ደመ ከልብ አድርጎ ያስቀረ ጭራቅ ነው ። አምነውት ለድርድርና ለእርቅ የቀረቡትን በውድቅት ሌሊት በተኙበት የጨፈጨፈ አውሬ ነው ። በትግራይና በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ባቋቋማቸው ዘግናኝ ከምድር በታች እስር ቤቶች "ሀለዋ ወያኔ" ወይም "ባዶ ስድስት" ያለቁ ኢትዮጵያውያንን ብዛትማ ቤቱ ይቁጠረው ። ከ1971/72 አንስቶ በወልቃይት ፣ በጠገዴና በጸለምት አማሮች ላይ የተፈጸመ ግፍ ለመስማት ይሰቀጥጣል ፤ ለማየት ይዘገንናል ።

ማንነታችን የአባቶቻችን አገር ርዕስት ይከበር ባሉ በግፍ ተገድለዋል ። ተሰቃይተዋል ። በጅምላ ተግዘዋል ። ተሰደዋል ። ጭው ባለ በርሀ በተሰሩ የምድር ቤት እስር ቤቶች ወገን በወገኑ ላይ ይፈጽመዋል ተብሎ ለማሰብ በሚከብድ ህልቆ መሳፍርት የሌለው ግፍ ተፈጽሞባቸዋል። በቁማቸው ተቀብረው ከብት ተነድቶባቸዋል። እስከ አንገታቸው ተቀብረው ራሳቸው ላይ ጨው ተነስንሶ ከብት እንዲልሳቸው ተደርጓል። እነሱን ገለውና አስረው ሚስቶቻቸውን ልጅ በማስወለዶ ዘር ለማጽዳት ጥረዋል። በማንነቱ እንዲሸማቀቅ በገዛ አገሩ ሁለተኛ ዜጋ እንዲሆን ተደርጓል። ዜጎችን ኦነግ በሚል የፈጠራ ክስ ፈርጆ ለማሰር የደህንነት መዋቅሩን ተጠቅሞ በፒያሳው ትግራይ ሆቴል፣ በሚኒባስና ሕዝብ በሚሰበሰብበት አደባባይ ፈንጂ የሚያፈነዳና ንጹሐንን የሚፈጅ እፉኝት ነው።

የቀድሞ የሕወሓት ነባር ታጋይ አይተ

ገብረመድህን አርአያ በአንድ ወቅት ከ" ኢትዮጲስ " ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ መጠይቅ ስለ ጌታቸው አሰፋ ተጠይቀው "...ጌታቸው ስለ ፈፀመው ግፍና ያጠፋው የንፁሀን ነፍስ ላይ በግልፅ ጥናት ቢደረግ ፤ ...ከሂትለር ባለሚሎች ተርታ የሚሰለፍ ነው።በአንድ ወቅት ከፍየል ውሃ ሁለት ገበሬዎችን አፍኖ ወደ ሀዋላ ወያኔ አስገባቸዋለሁ ብሎ መንገድ ላይ ገሎ ጥሏቸው አስከሬናቸው በጅብ ተበልቶ የራስ ቅላቸው ወድቆ ተገኝቷል ::

የጌታቸው አሰፋ ደስታ የሚመነጨው ከሰው ልጆች ስቃይና መከራ ነው ። በጭካኔያዊ ድርጊት የሚደሰት SADIST ነው ።ከቀድሞው የወያኔ የደህንነት ኃላፊ ጋር በመሆን ብዙ ሰላማዊ ሰዎችን የጨረሰ ወንጀለኛ ነው ። ከመነሻው አንስቶ እጁ በንፁህን ደም የጨቀየ ነው ። የትግራይ መሪዎች በትግራይ ሕዝብ መካከል የበቀሉ አረሞች እንጅ ከትግራይ ሕዝብ አብራክ የወጡ አይደለም።አሸባራ ትህነግ ፀረ ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን ፤ ፀረ ትግራይም ነው ::... ይላሉ ። ዛሬ አሸባሪው ትህነግ ሸለቆ ለሸለቆ እየተሽሎከለከ የሚፈጽመው ግፍ አብሮት ያደገ እንጂ ዛሬ የተጀመረ አይደለም ። ስለጌታቸው አሰፋ አረመኔያዊ ማንነት የተገለጸው የአሸባሪው ትህነግ መገለጫ ነው ።

አሸባሪው ትህነግ አገዛዝ ላይ እያለም ሆነ በመማጸኛ ከተማው መቐሌ መሽጎ ያልጣሰው የሰብዓዊ መብት ጥሰት የለም ። ገልብጦ ገርፏል ። አካል አጉድሏል ። ዘር እንዳይተኩ አድርጓል ። ወንድ ልጅ ሳይቀር እንዲደፈር አድርጓል ። ጥፍር ነቅሏል ። በወንድ ልጅ ብልት የሁለትና የሶስት ሌትር የላስቲክ ውሀ አንጠልጥሏል ። በደረሰባቸው ስቃይ ብዙዎቹ ለአእምሮ ህመም ተዳርገዋል ። ሽባ ሆነዋል ። እግራቸው ተቆርጧል ። በማዕከላዊ ፣ በቃሊቲ ፣ በቅሊንጦ ፣ በሽዋ ሮቢትና በሌሎች "ማረሚያ" ቤቶችና ስውር ማሰቃያ ቦታዎች ህልቆ መሳፍርት የሌለው ግፍ ፈጽሟል ። አስፈጽሟል ።

በእስክንድር ነጋ ፣ በአንዷለም አራጌ ፣ በሀብታሙ አያሌው ፣ በከፍያለው ፣ በዳባ ገሬ ፣ በወልቃይት ሕዝብ ፣ በዋልድባ አባቶች እና በሙስሊም ወንድሞቻችን ላይ ለመስማት የሚሰቀጥጥና ለማየት የሚዘገንን ግፍ ፈጽሟል። ለሶስት ዓመታት በፊት"የፍትሕ ሰቆቃ"በሚል በኢቲቪና በሌሎች ቴሌቪዥኖች የተላለፈው ዘጋቢ ፊልም ፤ የጌታቸው ሽፈራው"የሰቆቃ ድምጾች"፤ የአንዳርጋቸው ጽጌ"የታፋኙ ማስታወሻ"፤ የአንዷለም አራጌ ፤ የሀብታሙ አያሌው ፤ ወዘተረፈ ግለ ማስታዎሻዎች ዛሬም ህያው እማኝ ናቸው ።

ከስቃዩ ሰለባዎች አንዱ የሆነው ዳባ ገሬ በዚሁ ዘጋቢ ፊልም ፤ በዜጎች ላይ ይፈፀም የነበረው ግፍ ወገን በወገኑ ላይ ይፈፅመዋል ተብሎ የማይታመንና ልጅ ሆነን ወላጆቻችን ያስፈራሩበት በነበረው ጭራቅ/ቡልቡል/ የሚፈፅም ይመስለኝ ነበር ያለው ይሄን ያረጋግጣል። የትህነግ መራሹን ግፍ በ"የፍትሕ ሰቆቃ"የተመለከትሁ እለት ማንባቴን አስታውሳለሁ ። ለእራሴ እውን እነዚያ አረመኔዎች ፣ አውሬዎች ከሰው ዘር የተፈጠሩ ናቸው ? ብያለሁ ። መልሱ የስቃዩ ሰለባ ዳባ እንዳለው ጭራቆች ናቸው ። ሕገ መንግስቱን ለሸንት ቤት ተጠቀምበት እያሉ ይሄን ዘግናኝ ስቃይ በወገናቸው ለፈፀሙ አረመኔዎች ነው እንግዲህ እነ አንቶኒዎ ጉተሬዝ ፣ ሱዛን ራይስና አንቶኒ ብሊከን ጠበቃ ሆነው ብቅ ያሉት !? በዛ ዘጋቢ ፊልም የስቃዩ ሰለባ ሆነው የቀረቡ እህት ወንድሞቼን ባሰብሁ ቁጥር አለማቀፉ ማህበረሰብና ምዕራባውያን በሀሰተኛና ሆን ተብሎ በተዛባ መረጃ ዛሬም ከትህነግ ጭፍራና ርዝራዥ ጎን መቆማቸውን ስመለከት በእነሱ ቁስል ላይ እንጨት እየሰደዱ እንደሆነ ስለሚሰማኝ ህመማቸው ያመኛል ።

በሮማውያን ዘመን የነበሩ ገዥዎች ሰውን ከአንበሳ ፣ ከነብር ጋር እያታገሉ በሰው ልጅ ስቃይ ይዝናኑ እንደነበር ከታሪክ ድርሳናት አንብበን እንዳልተደነቅን ፤ በአገራችን አብዲሌ በሶማሊያ ክልል ጅግጅጋ በ" ጄል ኦጋዴን " ! ዜጎች ከአንበሳ ፣ ከነብር ፣ ከጅብ ጋር ይታሰሩበት የነበረ ምን አልባት በአለማችን በ21ኛው ክ /ዘ የመጀመሪያም ፣ የመጨረሻም የሆነ ማሰቃያ አዘጋጅቶ ህልቁ መሳፍርት የሌለው ግፍ ይፈጸም የነበረው በአሸባሪው ትህነግ ቡራኬ መሆኑን ያስተዋለ በዜጎች ይፈጸም የነበረ ግፍ ተቋማዊ እንደነበር ያረጋግጣል ። ሆኖም ከሀዲውና እፉኝቱ አሸባሪው ትህነግ የጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም የሰሜን ዕዝ ጥቃት እና የጥቅምት 30ን የማይካድራን ፣ የጭናን ፣ የአጋምሳን ፣ የአንጾኪያ ገምዛን ፣ የደባርቅን ፣ የጋሊኮማን ፣ ወዘተረፈ ትውልድና ታሪክ ይቅር የማይለውን የክፍለ ዘመኑን ታላቅ ክህደትና ጭፍጨፋ ለመፈጸም ዝግጅቱንና ልምምዱን የጀመረው ከደደቢት ውልደቱ ከየካቲት 11 ቀን 1967 ዓ.ም አንስቶ ነው ። ለግማሽ ክፍለ ዘመን በዝግ የተዶለተበት የክህደት ደባ ። የጭካኔ ልምምድና ዝግጅት ውጤት ነው ።

### እንደ መውጫ

አዎ አሸባሪው ሕወሓት ጭራቅ ፣ ቡልቡል ወይም ዞምቢ እንጂ በፈጣሪ አምሳል የተፈጠሩ ሰዎች ስብስብ አይደለም ። ዞምቢ ሲመለከቱት አስፈሪ ፤ ባህሪው ደግሞ ጨካኝ አረመኔ ነው ። በላዔ ሰብዕና ደም መጣጭ ነው ። የአሸባሪው ሕወሓት በገዛ ዜጎቹ ላይ ለ27 ዓመታት ይፈፅመው በነበረ ግፍና ስቃይ የተነሳ እንደ ዞምቢና ጭራቅ መፈራት ጀምሮ ነበር ።በገዛ እህት ወንድሞቹ ላይ የፈፀማቸው ለመስማት የሚሰቀጥጡ ፣ ለማየት የሚዘገንኑ ግፎችን መለስ ብለን ባሰብን ቁጥር በአምላክ አምሳል የተፈጠረ የሰዎች ስብስብ ያደረጋቸው ሳይሆን የሰውነትና የኢትዮጵያዊነት ባህሪ ባልነበረው ዞምቢ ቡድን የተፈጸሙ ነበሩ ። በገዛ ወገኑ ስቃይ ፣ ግፍ ፣ በደል ፣ ርሀብ ፣ እርዛት ፣ ቸነፈር፣ እልቂት ፣ ግጭት ፣ ወዘተረፈ እንጀራውን የሚያሰፋና የሚደሰት የአሸባሪው ትህነግ ዞምቢ ብቻ ነው ።

አንዱን ብሔር ከሌላው ብሔር ፤ አንዱን ሀይማኖት ከሌላው ሀይማኖት በማጋጨት የደም ምሱን የሚያገኝ ። ዛሬም ለዚህ የደም ምሱ ርዝራዡ ቀን ከሌት እዚህም እዚያም እየዛከረና እየተንቀዠቀዠ ነው። በአጠቃላይ የአሸባሪው ትህነግ ባህሪም ሆነ መልክ ከኢትዮጵያውያን የስነ ልቦና ውቅርና ማንነት ያፈነገጠ መሆኑን የሴራ ፣ የደባ ፣ የጭካኔና የግፍ ጥጉ ጥሩ ማሳያ ነው። ባለፈው በሰሜን እዝ ላይ የፈጸመው ትውልድም ሆነ ታሪክ ይቅር የማይለው ክህደትም ሆነ እስከዛሬ የቀጠሉት ኅልቆ መሳፍርት የሌላቸው ግፎች ፤ በአገሪቱ የዘመናዊ ፖለቲካ ታሪክ ታይቶና ተሰምቶ እንደማያውቅ አፍን ሞልቶ መናገር ይቻላል። ወደፊትም በኢትዮጵያ ሰማይ ስር ይፈጠራል ተብሎ አይታሰብም::

አገራችን ኢትዮጵያ በሀቀኛና ጀግኖች ልጆቿ ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር !

አሜን ።

# ስፖርት




## ጥቁሮች ሁሌም የሚገፉበት ታሳቁ የእግር ኳስ ሽልማት

**ቦጋለ አበበ**

ዝነኛው የፈረንሳይ የእግር ኳስ መጽሔት በየዓመቱ ለምርጥ የአውሮፓ እግር ኳስ ተጫዋቾችና አሰልጣኞች የሚያበረክተው የባልን ድ ኦር ሽልማት ባለፈው ሰኞ ተከናውኗል። ከአስር ዓመታት በላይ በሁለቱ ከዋክብት ሊዮኔል ሜሲና ክርስቲያና ሮናልዶ ፍፁም የበላይነት ተይዞ የቆየው ይህ ሽልማት ወደ አዳዲስ ኮከቦች ፊቱን አዙርዋል።ነገር ግን ዘንድሮም ወደ አፍሪካውያን ወይም ጥቁር ተጫዋቾች ሳይመጣ ቀርቷል።ፈረንሳዊው የሪያል ማድሪድ ኮከብ ካሪም ቤንዜማ ለመጀመሪያ ጊዜ ሽልማቱን ሊወስድ ችሏል።

ሽልማቱ እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ አጨቃጫቂ ሆኖ ባያልፍም የቆዳ ቀለማቸው ጥቁር በመሆኑ ብቻ ይህን ታላቅ ሽልማት ማሸነፍ ሲገባቸው ያላሸነፉ ተጫዋቾች ጉዳይ ሁልግዜም አነጋጋሪ ነው። ለአብነት ያህል ያለፈው ዓመት ሽልማት መስፈርቱ ከዘረኝነት የፀዳ ቢሆን ኖሮ የሴኔጋል ብሔራዊ ቡድንና የቼልሲው ግብ ጠባቂ ኤድዋርድ ሜንዲ የምርጥ ግብ ጠባቂዎችን ሽልማት ማሸነፍ ይገባው እንደነበር በርካቶች በብዙ ማሳያዎች ይከራከራሉ።

ሜንዲ የአውሮፓ ቻምፒዮንስ ሊግ ዋንጫን በውድድር ዓመቱ ከቼልሲ ጋር አሸንፏል፣ የሱፐር ካፕ ዋንጫን አንስቷል፣ በዚህም የአውሮፓ ምርጥ ግብ ጠባቂ ሽልማትን ማሸነፍ ችሏል። በብዙ ጨዋታዎች ጎል ሳይቆጠርበት በመውጣት ቀዳሚ ነው፣ በእንግሊዝ ፕሪሚየር ሊግም በብዙ ጨዋታዎች ጎል ሳይቆጠርበት በመውጣት ሁለተኛው ግብ ጠባቂ ነው፣ በቻምፒዮንስ


ካሪም ቤንዜማ ያሸነፈው የዘንድሮው የባሎን ድ ኦር ሽልማት በርካቶችን አስማምቷል፣

ሊግ ሶስት ጎል ብቻ ተቆጥረውበታል፣ የባሎን ድ ኦርን ሽልማት ያሸነፈው ግን ይህን ሁሉ ስኬት በውድድር ዓመቱ የተጎናጸፈው ሜንዲ ሳይሆን ከጣሊያን ብሔራዊ ቡድን ጋር የአውሮፓ ዋንጫን ያሳካው ዶናሮማ ነው። እውነታው ግን አፍሪካውያን በእግር ኳሱ ዓለም እውቅና የላቸውም፣ አፍሪካውያን ተጫዋቾች ጥቁር በመሆናቸው ብቻ ብዙውን ጊዜ ማግኘት ያለባቸውን ነገር እንደማያገኙ ማሳያ ነው። ይህም በበርካቶች ዘንድ ጥያቄ ማስነሳቱ የተለመደ ነው።

አፍሪካውያን ወይም ጥቁር ተጫዋቾች ይህን ሽልማት እኤአ በ1995 ላይቤሪያዊው ኮከብ ጆርጅ ዊሃ ካሸነፈ ወዲህ ማሸነፍ አለመቻላቸው የሁልጊዜም ጥያቄ ነው። በተለይም አፍሪካውያን ተጫዋቾች ከሌሎች ተጫዋቾች በተሻለ ስኬታማ በነበሩባቸው በርካታ ዓመታት ይህን ሽልማት አለማግኘታቸው በአፍሪካውያን ዘንድ ቁጭት እንደፈጠረ ነው። ለአብነት ያህል በቅርቡ 2019 ላይ ከሊቨርፑል ጋር አስደናቂ የውድድር ዓመት ያሳለፉት ሴኔጋላዊው ሳዲዮ ማኔና ግብጻዊው ሞሐመድ ሳላህ ሽልማቱን የማሸነፍ ትልቅ እድል እያላቸውና እየተገባቸው ለሊዮኔል ሜሲ መሰጠቱ በርካቶችን ያበሳጨ የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው።

አፍሪካውያን ተጫዋቾች ከጆርጅ ዊሃ በኋላ ለዚህ ሽልማት አለመብቃታቸው የተለያየ መላምትና ምክንያት ይደረደራል። የቀድሞው ሴኔጋላዊ ኮከብ ፈርዲናንድ ኮሊ በአንድ ወቅት አፍሪካውያን ይህን ሽልማት ማሸነፍ ከማይችሉበት ምክንያት አንዱ ብሔራዊ ቡድኖቻቸው በዓለም አቀፍ ደረጃ ውጤታማ ባለመሆናቸው መሆኑን ጠቅሷል። ይሁን እንጂ ይህ ለብዙዎች አሳማኝ አይደለም። ምክንያቱም ሊዮኔል ሜሲ ከአርጀንቲና ብሔራዊ ቡድን ጋር የዓለም ዋንጫን ሳያነሳ ሰባት ሽልማቶችን ጠራርጎ ወስዷል።

ባለፉት በርካታ ዓመታት ከክለቡ ሊቨርፑል ጋር አስደናቂ ጊዜን ያሳለፈው አሁንም ግብፃዊው ኮከብ ሳላህ፣ የባሎን ድ ኦር ሽልማት ከዓለም ዋንጫ ጋር መቆራኘቱን እንዲህ ሲል ይቃወማል ‹‹በአፍሪካ ተጫዋቾች ማሸነፍ የነበረባቸው ብዙ የባሎን ዶር ሽልማቶች አሉ፣ ነገር ግን አልተሸለሙም። ካልተስማማችሁ እባካችሁን በአንድ ፕሪሚየር ሊግ ውስጥ ከ20 በላይ ግቦችን ያስቆጠረና ሊጉን ያሸነፈ አፍሪካዊ ተጫ ዋች እንደነበር ላስታውሳችሁ። እንዲሁም በመጨረሻ አንድ አፍሪካዊ ተጫዋች በቻምፒዮንስ ሊግ ፍፃሜ ያልደረሰበትን አንድ ወቅት ይጥቀሱ። የዓለም ዋንጫን ስለማሸነፍ እየተናገራችሁ ከሆነ ይህ ማለት ባሎን ድ ኦር በየዓመቱ በሚባል ደረጃ በስህተት ተሸልሟል ማለት ነው፣ ምክንያቱም የዚህ ሽልማት አብዛኞዎቹ አሸናፊዎች የዓለም ዋንጫ የላቸውም።››

ታሪካዊው የካሜሩን ኮከብ ሮጀር ሚላም በዚህ ረገድ የተለየ እይታ ወይም አስተያየት አለው። እንደ ሚላ እምነት ሽልማቱን የሚሰጠው ተቋም አፍሪካውያን እንዲያሸንፉ አይፈልግም፣ ሊዮኔል ሜሲ ይህን ሽልማት ደጋግሞ የሚያሸንፍበት መሰረትም ከስፖርታዊ ብቃት ይልቅ ከንግድ ጋር የተቆራኘ ነው። ሚላ ጆርጅ ዊሃ ብቸኛውን ሽልማት ባሸነፈበት ዓመት ሸላሚዎቹ ዊሃ የነበረውን በግልጽ የሚታይ ብቃት መሸሸግ ስለማይችሉ ነገሮች አስገዳጅ ሆነውባቸው ነው ይላል።

አንድ ቀን ግን ነገሮች ተቀይረው አፍሪካውያን ተጫዋቾች ይህን ዝነኛ ሽልማት ደጋግመው እንደ ሚያሸንፉ ሮጀር ሚላ ተስፋ አለው። ‹‹ነገሮች የሚለወጡ ይመስለኛል፣ ግብጻዊው ኮከብ ሳላህ አስደናቂ ነገር እያሳየ ነው፣ ሴኔጋላዊው ማኔ የሚሰራው ድንቅ ነገርም ያልተለመደ ነው፣ ሽልማቱና ሰዎች የመርህ ተገዢ መሆን አለባቸው፣ የባልን ድ ኦር ሽልማት ለአፍሪካ እግር ኳስ የሚጨምረው ነገር አለ›› የሚለው ሚላ የእግር ኳስ ዓለም አቀፋዊ እድገት እንደ አፍሪካ ባሉ አህጉራት እንዲቀጥል ከተፈለገ እግር ኳሱን የሚመሩ አካላት በሃቅ መስራት እንዳለባቸው ይመክራል።




## ጎበዞቹ የካራ አሎ ትምህርትቤት ተማሪዎች

**ጽጌረዳ ጫንያው**

ልጆች እንዴት ናችሁ፤ ትምህርት እንዴት ይዟችኋል? በደንብ እያነበባችሁ ነው አይደል? ከመጀመሪያው ጀምሮ ማንበብን ልምምድ ካደረጋችሁ ውጤታማ ትሆናላችሁ። ስለዚህም ጎበዝ ተማሪ ለመሆን ከፈለጋችሁ ዛሬ የተማራችሁትን ዛሬውኑ አንብቡ።ተጨማሪ ነገሮችን በማከልም አቅማችሁን ማጎልበት አለባችሁ። ልጆች ዛሬ ይዤላችሁ የመጣሁት በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት ሚኒስትሪ ተፈታኝ የሆኑትን የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎችንና ዝግጅታቸውን ነው።ስለ አዲሱ ስርዓተ ትምህርት ጥቅምም በደንብ ነግረውኛልና ከእነርሱ ተሞክሮ እንደምትወስዱ እምነት አለኝ።

መጀመሪያ ያነጋገርኳት ልጅ ማን መሰለቻችሁ? ደራርቱ ድሪባ ትባላለች።ከላይ እንዳልኳችሁ የዘንድሮ የስምንተኛ ክፍል ተፈታኝ ናት። በትምህርቷ ደግሞ በጣም ጎበዝና ጥንቁቅ ልጅ ነች። በትምህርት ቤቷ ስርዓተ ጾታ ክበብ ውስጥ፤ የጤና ክበብ ውስጥና የሚኒሚዲያ ክበብ ውስጥ ትሳተፋለች። በዚህም በርካታ ለውጦችን በራሷ ላይ አምጥታለች። በተለይ ልዩ ተሰጥኦዋን አውቃ እንድትቀጥልበት ሆናለች።ለዚህም በአብነት ያነሳችልን የቴአትር መስራት አቅሟን ማየቷን ነው።

ልጆች ደራርቱ የስምንተኛ ክፍል ተፈታኝ በመሆኗ ከዚህ ቀደም ሲመቻት እንጂ ጊዜ ወስዳ ሳታጠና የቆየችበትን የአጠናን ዘዴ ቀይራለች።አሁን ዛሬ የተማረችውን ዛሬ እንጂ ለነገ አትተውም። ጎን ለጎን ለፈተና ያግዙኛል ብላ የምታስበውን ታነባለችም።ለዚህ ደግሞ አዲሱ ሥርዓተ ትምህርት ድጋፍ እንደሆነላት ታነሳለች። የትምህርቱ ዝግጅቱና የመማር ማስተማሩ ሥራ ብዙ ምቹ ሁኔታን የፈጠረላት እንደሆነም ታምናለች።ከስር ከስር የሚሰጣቸውን ትምህርት ለማጥናት ትሞክራለች።

በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት ነገሮች እንደቀለሉም ትናገራለች። ታችኛው ክፍል ድረስ ወርዶ ከማጥናት ገላግሎናል። በዚያ ላይ ለትምህርት ደረጃው የሚመጥን ተደርጎ ስለተዘጋጀ ትምህርቱ ከዚህ ቀደሙ የሚቀል


ተማሪ ደራርቱ ድሪባ


ፎቶ በአሸናፊ ጌደታ

ተማሪ ፍሬጽዮን የሺጥላ

ነው።እናም ስናጠናና ለፈተና ስንዘጋጅ አንቸገርበትም ትላለች። አሁን ገና ትምህርት ከመጀመሩ ጀምሮ አጠናኗን እያስተካከለች በመሆኑም ደስተኛ ሆናለች።

ደራርቱ የእናቷን ህልም ለመኖር እየሰራች ትገኛለች። ይህም እናቷ ጎበዝና የተማረች ብትሆንም ዶክተር የመሆን ህልሟ ጋር በችግር ምክንያት ልትደርስ አልቻለችም።እናም ደራርቱ ይህንን ህልሟን መመለስ ትሻለች።በህክምና ሙያው ተመርቃ ማህበረሰቡን በማገልገል ውስጥ እናቷን ማስደሰት ትፈልጋለች። ለዚህም ገና ከውጥኑ ጠንካራ ተማሪ ለመሆን እየተጋች ነው።

ልጆች ደራርቱ ለእናንተ የምትመክረው ነገር አላት።የመጀመሪያው ትምህርታችሁን ትኩረት አድርጉ የሚለው ነው። በትምህርት ማንኛውንም ነገር መለወጥ ይቻላል። ማንም ሰነፍ ሆኖ አልተፈጠረም።የመጠቀምና የመስራት ጉዳይ ነው ልዩነቶችን የሚያመጣው።እናም በርትታችሁ የምታነቡና ትምህርታችሁን ወደ ተግባር የምትለውጡ ልጆች ከሆናችሁ የማትደርሱበት ነገር አይኖርም። የማትፈቱት ችግርም እንዲሁ ትላለች።

ሌላው የመከረችው ነገር እንደ አገር ለተማሪዎች የተሰጠው ነገር እጅግ የሚያስደስት ነው።ቤተሰቦቻችን አርፈው፤ እኛም ሳንጨናነቅ የምገባ ስርዓት ተጀምሮልን እንድንማር ሆነናል። የደንብ ልብስና የትምህርት ቁሳቁስም ተሟልቶልናል። ለእኛ የሚያስፈልገው ደግሞ ይህ ብቻ ነው። ስለዚህ ለቤተሰቦቻችን ደስታ ለአገራችን ውለታ ለመክፈል በጣም ጎበዝ ተማሪና አትራፊ መሆን ይገባናል የሚለው ነው። በተለይም እምቅ ችሎታ ያላቸው ልጆች ይህንን እድል መጠቀምና ለማህበረሰቡም ሆነ ለራሳቸው ሕይወት ለውጥ መስራት እንዳለባቸው ታሳስባለች።

እንደ ደራርቱ ሁላ በካራ አሎ ቅድመ መደበኛና መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የምትማረው ፍሬጽዮን የሺጥላ ስትሆን፤ እርሷም የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ናት። በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት የሚጀመረውን የስምንተኛ ክፍል ፈተና ትወስዳለችም።ስለዚህም ገና ከአሁኑ ራሷን ለፈተናው እያዘጋጀች ትገኛለች።በዋናነት ዝግጅቷን እያደረገች ያለችውም ፕሮግራም አውጥታ በማጥናት ነው።ጎን ለጎን ባላት ጊዜ ከተማሪዎች ጋር በመሆን ታነባለች።

አዲሱ የትምህርት ስርዓትን በጣም ወዳዋለች። ምክንያቱም በእርሱ ውስጥ አገሯን ማየት ጀምራለች። ስለውጪው ባህልና ወግ ሳይሆን ስለ አገራችን ማንነትና ምንነት በሚገባ ያሳውቃልና የማታውቀውን ነገር እንድታይ አድርጓታል።በዚያ ላይ በስነምግባር ተኮትኩተው እንዲያድጉ፤ ባህላቸውን ያወቁ ዜጎች እንዲፈጠሩ ለማድረግ እንደ አንድ ትምህርት የሚሰጠው ነገር ብዙ ነገሮችን እንደሚቀይር ታስባለች። ከሁሉም በላይ ግን ልዩ ተሰጥኦዋቸውን አውቀው እንዲጓዙና የሥራ ባህላቸውን እንዲያዳብሩ ስለሚያግዛቸው ደስተኛ አድርጓታል።

ልጆች በእነ ፍሬጽዮን ትምህርት ቤት ልዩ የመማር ማስተማር ሥራ መከናወኑም ለፈተና ዝግጅታቸው እጅጉን እንደሚያግዝ ፍሬጽዮን ትናገራለች።ለአብነት የጠቀሰችውም ትምህርት ቤቱ ለተማሪዎች በማሰብ የቅዳሜ ትምህርትን ማስጀመሩን ነው።ትምህርቱ ሲሰጥ ከሰኞ እስከ አርብ የተማሩትን የሚከለስበት በመሆኑ ለጥናት ነገሮችን ያቀልላቸዋል። በዚያ ላይ ምን ያህል እውቀት እንደጨበጡ ያረጋግጥላቸዋል።

ሌላው ከትምህርትቤታቸው የወደደችው ነገር ተማሪዎች በህብረትም ሆነ በተናጠል ሳይጨናነቁ እንዲያጠኑና እንዲሰሩ ለማድረግ የተፈጠረላቸው ምቹ ሁኔታን ነው። ይህም « የንባብ ፓርክ» ጉዳይ ሲሆን፤ በአጸድ የተሸፈነና ለማንበብ የሚማርክ እንደሆነ ታነሳለች። ስለዚህም ተማሪዎች የተፈጠረላቸውን መልካም አጋጣሚ ሁሉ ተጠቅመው ውጤታማ መሆን አለባቸውና ይህንን ያድርጉ ስትል ትመክራለች።እኔም ተሞክሯቸው በተለይም ለተፈታኞች ይጠቅማልና ሁኑበት እያልኩ ለዛሬ አበቃሁ። መልካም ሰንበት ይሁንላችሁ !!